የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልዕክት ፡
ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡

ትርጓሜ ።

መልእክቱ ። ሀ) ዘመኑ ። መልእክቱ፣ በተጻፈበት ፣ ወቅት ፣ ጳውሎስ ፣ እስረኛ ፣ ነበር ። [7] ታሰሮ ፣ ወደ ፣ ሮም ፣ የደረሰው ፣ በ፷፪ ፣ ዓ. ም. ነውና ፣ የታሰረም ፣ ፪ ፣ ዓመት ፣ ነውና ፣ መልእክቲቱ ፣ የተጻፈች ፣ በ፷፪ ፣ ዓ ፣ ም ፣ እና ፣ በ፷፬ ፣ ዓ. ም. መካከል ፣ ነው ፤ ይህም ፣ ማለት ፣ ክርስቶስ ፣ ሞቶ ፣ ከተነሣ ፣ አንድ ፣ ፴ ፣ ዓመት ፣ በኋላ ፣ ነው ።

ለ) በአማርኛ ፣ ትርጕማችን ፣ (እንዲሁም ፣ በግዕዝ) ፣ በቊጥር ፣ ፩ ፣ ላይ ፣ «በኤፌሶን ፣ ላሉት» ይላል ። መልእክቱ ፣ ግን ፣ የተጻፈው ፣ ለኤፌሶን ፣ ብቻ ፣ ነውን ? አይመስልም ። ምክንያቱም ፣ ጳውሎስ ፣ በኤፌሶን ፣ ክተማ ፣ ፫ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ እንደ ፣ ተቀመጠ ፣ አይተናል ። እርሱ ፣ በቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ የነበሩትን ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ፣ አውቆአል ፣ እነርሱም ፣ አውቀውታል ።

በም. ፩ ፣ ፲፭ ፣ ላይ ፣ ግን ፣ ሐዋርያው ፣ «ስለ ፣ እናንተ ፣ ሰምቼ ፣ » ይላል ፤ በም. ፫ ፣ ፪ ፣ ላይ ፣ ደግሞ ፣ «ስለ ፣ እኔ ፣ ሰምታችኋል ፣ » ይላል ። ምነው? አብረው ፣ ተቀምጠው ፣ አብረው ፣ ከርመው ፣ አብረው ፣ ሠርተው ፣ የለ ምን ? ሁለተኛ ፣ አሳብ ፤ በሐዋ ፣ ም. ፳ ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ተተች ፣ ጳውሎስ ፣ ሚሊጢን ፣ ወደሚባል ፣ ወደብ ፣ ቢደርስ ፣ ወደ ፣ ኤፌሶን ፣ ልኮ ፣ የቤተ ፣ ክርስቲያንን ፣ ሽማግሌዎች ፣ አስጠራ ፤ ከእነርሱም ፣ ጋር ፣ በእንዴት ፣ ያለ ፣ መግባባትና ፣ ፍቅር ፣ እንደ ፣ ተናገረ ፣ እናውቃለን ። ታዲያ ፣ ወደ ፣ ኤፌሶን ፣ ሰዎች ፣ ዘንድ ፣ መልእክት ፣ ሲጽፍ ፣ ስም ፣ ስማቸውን ፣ እየ ጠቀሰ ፣ ሞቅ ፣ ያለ ፣ ሰላምታ ፣ አያቀርብላቸውምን ? በኤፌሶን ፣ መልእክት ፣ ላይ ፣ ግን ፣ ለማንም ፣ ሰው ፣ ሰላምታ ፣ አላቀረበም ። ሦስተኛ ፣ አሳብ ፣ ደግሞ ፣ በመልእክቲቱ ፣ በመጀመሪያ ፣ ረቂቆች ፣ ላይ ፣ በቊጥር ፣ ፩ ፣ ላይ ፣ በአድራሻው ፣ ቦታ ፣ ክፍት ፣ ስፍራ ፣ ነበረ ፣ እንጂ ፣ «በኤፌሶን» ፣ የተ ባለ ፣ ቃል ፣ አልነበረም ።

በእነዚህ ፣ ሁሉ ፣ አሳቦች ፣ ምክንያት ፣ ብዙዎች ፣ መምህራን ፣ «መል እክቱ ፣ የተጻፈው ፣ በኤፌሶን ፣ አቅራቢያ ፣ ለተገኙት ፣ ለእስያ ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ሁሉ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ለኤፌሶን ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ብቻ ፣ አልተጻፈም ፣ » ይላሉ ። ይህም ፣ የእውነቱ ፣ ሊሆን ፣ ይችላል ። ለኤፌሶን ፣ በእርግጥ ፣ ተጽፎአል ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ለኤፌሶን ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ በኤፌ ሶን ፣ ዙሪያ ፣ ለነበሩት ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ጭምር ፣ ተጽፎአል ። [8] ጳውሎስ ፣ መልእክቱን ፣ ጻፈ ፤ ከጻፈም ፣ በኋላ ፣ እኛ ፣ ዛሬ ፣ በማራቢያ ፣ መኪና ፣ ወረቀታችንን ፣ አባዝተን ፣ በእያንዳንዱም ፣ ላይ ፣ አድራሻው ንና ፣ የምንልክለትን ፣ ሰው ፣ ስም ፣ እየጻፍን ፣ ወደ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ስፍራ ዎች ፣ እንደምንልከው ፣ ሁሉ ፣ እንዲሁም ፣ ጳውሎስ ፣ ጸሐፊውን ፣ ሲያ ዝዝ ፣ «አድራሻውን ፣ ክፍት ፣ አድርገህ ፣ ተወው ! » ብሎ ፣ መክሮት ፣ ይሆናል ። ቀጥሎም ፣ ወረቀቶቹን ፣ ለቲኪቆስ ፣ አደራ ፣ ሲሰጥ ፣ በሚደ

7. ኤፌ. ፫ ፣ ፩ ፤ ም. ፬ ፣ ፩ ፤ ም. ፮ ፣ ፳ ። 8. ራእይ ፣ ፩ ፣ ፲፩ ።

ርስበት ፣ ከተማ ፣ ሁሉ ፣ የከተማውን ፣ ስም ፣ በክፍቱ ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ እን ዲሞላ ፣ እዝዞት ፣ ይህንኑ ፣ መልእክትና ፣ ወደ ፣ ቈላስይስ ፣ የተጻፈውን ፣ መልእክት ፣ ወደ ፣ ራልሞናም ፣ የተጻፈውን ፣ ፫ቱንም ፣ መልእክቶች ፣ አስይዞት ፣ ይሆናል ። [9] እንደዚህ ፣ ከሆነ ፣ «ሰምቻለሁ ፣ ሰምታችኋል ፣» የተባለውን ፣ ነገር ፣ የአድራሻንና ፣ የሰላምታንም ፣ መታጣት ፣ ነገር ፣ ለመ ረዳት ፣ ይቀላል ።

ሐ) በሐዋርያው ፣ ዘመን ፣ በአይሁዶችና ፣ በአሕዛብ ፣ ወገን ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ታላቅ ፣ ልዩነት ፣ ነበረ ። አይሁዶች ፣ ታላቅ ፣ ተስፋ ፣ የተሰ ጣቸው ፣ ምርጥ ፣ የሆኑ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ሰዎች ፣ መሆናቸውና ፣ እግዚ አብሔር ፣ በተለይ ፣ የእነርሱ ፣ አምላክ ፣ መሆኑ ፣ ሲታሰብ ፣ የአሕዛብ ፣ ወገን ፣ ሰዎች ፣ ደግሞ ፣ ባዕዳን ፣ ከማኅበር ፣ ውጭ ፣ የሆኑና ፣ ከእግዚአ ብሔር ፣ ተለይተው ፣ ተስፋ ፣ የሌላቸው ፣ ሰዎች ፣ መሆናቸው ፣ ታስቦአል ። ነገር ፣ ግን ፣ በዚህች ፣ መልእክት ፣ ላይ ፣ ሐዋርያው ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተሠውሮ ፣ የነበረውን ፣ አንድ ፣ ታላቅ ፣ ምሥጢር ፣ ይገልጣል ፤ ይኸውም ፣ ሁሉም ፣ ማለት ፣ በሰማይና ፣ በምድር ፣ ያለ ፣ ሁሉ ፣ በክርስቶስ ፣ ታርቆ ፣ አንድ ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ የዘላለም ፣ የእግዚአብሔር ፣ አሳብ ፣ መሆኑን ፣ ነው ። ይህ ፣ ነገር ፣ ተሠውሮ ፣ ምሥጢር ፣ ሆኖ ፣ ቈይቶ ፣ ነበር ፣ አሁን ፣ ግን ፣ በክርስቶስ ፣ ተፈጸመ ፣ ለጳውሎስም ፣ በራእይ ፣ ተገለጠ ። [10]

ክርስቶስ ፣ በመስቀሉ ፣ ማስታረቅን ፣ አድርጎአልና ፣ አሁን ፣ ሁለት ፣ ጉባኤዎች ፣ (ወይም ፣ ሁለት ፣ አካሎች ፣) ማለት ፣ አይሁዶችና ፣ የአሕ ዛብ ፣ ወገን ፣ ሰዎች ፣ የሉም ፤ አሁን ፣ ያለችው ፣ አንዲት ፣ ጉባኤ ፣ አን ዲትም ፣ አካል ፣ ብቻ ፣ ናት ። እርስዋም ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ናት ። በዚ ህችም ፣ አካል ፣ እኛ ፣ ምእመናን ፣ አባሎች ፣ (አካላት) ፣ ነን ። [11] ለዚህች ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያንና ፣ ለአባሎችዋ ፣ ታላቅ ፣ መብትና ፣ ታላቅ ፣ ተግባር ፣ ተሰጥቶአታል ፣ ተሰጥቶናልም ። እርሱስ ፣ ምንድር ፣ ነው ? ቢሉ ፣ ፍለጋ ፣ የሌለውን ፣ የክርስቶስን ፣ ባለ ፣ ጠግነት ፣ በመስበክ ፣ ሰውን ፣ ሁሉ ፣ በእ ርሱ ፣ ለማስታረቅና ፣ በሰማያዊ ፣ ስፍራም ፣ ውስጥ ፣ ላሉት ፣ አለቆችና ፣ ሥልጣናት ፣ ታላቅ ፣ የሆነውን ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ጥበብ ፣ ለማስታወቅ ፣ መብት ፣ ተሰጥቶአታል ፣ ተሰጥቶናልም ። [12] እንዲህም ፣ ያለ ፣ መብትና ፣ ተግባር ፣ ከተሰጣት ፣ ከተሰጠንም ፣ እኛ ፣ እንዴት ፣ እንደምንመላለስ ፣ (እንደምንኖር ፣) እጅጉን ፣ መጠንቀቅ ፣ ያሻናል ። [13]

ይህች ፣ መልእክት ፣ ስለ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ስለ ፣ ክብርዋም ፣ ትና ገራለች ። ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ስትባል ፣ መቸም ፣ ሕንጻ ፣ ወይም ፣ በአንድ ፣ መንደርም ፣ ሆነ ፣ ከተማ ፣ አገርም ፣ የምትገኝ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ሳት

9. ኤፌ. ፮ ፣ ፳፩ ። ቈላ. ፬ ፣ ፯—፱ ። 10. ኤፌ. ፩ ፣ ፱ ፣ ፲ ። ም. ፮ ፣ ፲፰—፲፯ ። ም. ፫ ፣ ፫—፱ ።
11. ኤፌ. ፪ ፣ ፲፯ ። ፩ቆሮ. ፲፪ ፣—፴ ። 12. ኤፌ. ፫ ፣ ፰—፲፩ ። ፪ቆሮ. ፭ ፣ ፲፰—፳ ።
13. ኤፌ. ፭ ፣ ፩ ። ም. ፭ ፣ ፩ ፣ ፮ ።

ሆን ፡ በሞላ ፡ ዓለም ፡ ዘንድ ፡ የምትሆን ፡ ሐዋርያት ፡ የሰበሰቡአት ፡ አን
ዲት ፡ ቅድስት ፡ የምእመናን ፡ አንድነት ፡ ጉባኤ ፡ (አቅሌስያ ፡) ናት ። መል
እክቲቱ ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ስለ ፡ ክብርዋ ፡ ስለ ፡ ሥራዋም ፡ ትናገራለች ፤
ስለ ፡ እኛም ፡ ስለ ፡ ምእመናን ፡ አባሎችዋ ፡ (አካላቶችዋ ፡) ስለ ፡ መሆና
ችንና ፡ አባሎች ፡ (አካላት ፡) ከመሆናችን ፡ የተነሣም ፡ ስለሚገባን ፡ አመ
ላለስ ፡ ትናገራለች ። የምትለውን ፡ እንስማ !

መ) ክፍሎቹ ። የመልእክቱ ፡ ክፍሎች ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡
፪ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ፩ኛው ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ዶክትሪን ፡ ፪ኛውም ፡
በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ሥራ ።

፩ኛ ፡ ክፍል ። ም. ፩ ፡ ም. ፪ ፡ ም. ፫ ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ዶክተርን ።

ም. ፩ ፡ ፩—፪ ። መቅድም ።
፫—፲፬ ። በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ሁሉን ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅ
ለል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዘላለማዊ ፡ አሳብ ።
፲፭—፳፫ ። ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ ያላቸውን ፡ ታላቅ ፡
እድል ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያው ፡ ጸሎት ።
ም. ፪ ፡ ፩—፲ ። ወደ ፡ መዳን ፡ ምልዓት ፡ ያደረሰን ፡ አስደናቂ ፡
የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ።
፲፩—፳፪ ። እውቁ ፡ የነበሩት ፡ የእሕዛብ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡
ጭምር ፡ እንደ ፡ ዳኑና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡
አባሎች ፡(አካላት ፡) እንደ ፡ ሆኑ ።
ም. ፫ ፡ ፩—፲፫ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡
አሳብ ፡ ለጳውሎስ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ።
፲፬—፳፩ ። ምእመናን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጠንክረው ፡
የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማወቅ ፡
ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያው ፡ ፪ኛ ፡ ጸሎት ።

፪ኛ ፡ ክፍል ። ም. ፬ ፡ ም. ፭ ፡ ም. ፮ ፡ በገቢር ፡ የሚገለጥ ፡ ሥራ ።

ስለ ፡ ምእመናን ፡ አንድነትና ፡ ልዩነት ።
ም. ፬ ፡ ፩—ም. ፭ ፡ ፳ ። የምእመናን ፡ አዲስ ፡ አመላለስና ፡
አነጋገር ።
ም. ፭ ፡ ፳፩—ም. ፮ ፡ ፱ ። የምእመናን ፡ የግል ፡ ግንኙነት ።
ም. ፮ ፡ ፲—፳፬ ። ምእመናን ፡ በተጋድሎአቸው ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡
የሐዋርያው ፡ መጨረሻ ፡ ምክር ።

ሠ) ለዛሬ ፡ የሚሆን ፡ ጥቅሙ ። «እኔን ፡ መልእክቱ ፡ ምን ፡ ያስተም
ረኛል ?» ቢሉ ፡ መልእክቲቱ ፡ እድልዎን ፡ እንዲያስተውሉና ፡ እንዲፈ
ጽሙት ፡ ትጠራዎታለች ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ ግለት ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡

ዘመን ፡ ምስጋናውን ፡ እንዲናገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለራሱ ፡ የፈጠረው ፡
ሕዝብ ፡ እስራኤል ፡ ነበረ ። [14] ማለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፍራት ፡ ዓለ
ምን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ እደራ ፡ የተሰጡአቸ
ውና ፡ ለእርሱ ፡ የተመረጠ ፡ ሕዝብና ፡ የካህናት ፡ መንግሥት ፡ የተቀደ
ሰም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተመደቡ ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። [15] እስ
ራኤል ፡ ግን ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ነበረች ። ይህንኑ ፡ ለመሆን ፡ ይህንኑም ፡ ሥራ ፡
ለመሥራት ፡ ከዘላለም ፡ ጀምሮ ፡ የታቀደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ እንድትሆን ፡ ነበረ ። ፍለጋ ፡ የሌለውን ፡ የክርስቶስን ፡ ባለ
ጠግነት ፡ ለአሕዛብ ፡ እንድትሰብክ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ጥበብ ፡ በሰ
ማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አለቆችና ፡ ሥልጣናት ፡ እንድታስታ
ውቅ ፡ መብቱ ፡ ዛሬ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ። [16] እኛም ፡ ምእመናን ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ (አካላት ፡) መሆናችንን ፡ የኤፌሶን ፡ መል
እክት ፡ ታስተምረናለች ። ያለ ፡ እኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በልክ ፡ ልት
ሠራ ፡ ልታድግም ፡ አትችልም ። ያለ ፡ እኛ ፡ የማትበቃና ፡ አካል ፡ ሆና ፡
የራስን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍላጎትና ፡ አሳብ ፡ ልትፈጽም ፡ የማትችል ፡
ናት ። እኛ ፡ እኮ ፡ አባሎችዋና ፡ አካላቶችዋም ፡ ነን ! ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በዓለም ፡ ውስጥ ፡ የተሰጣትን ፡ አደራ ፡ የምትፈጽም ፡ ከሆነች ፡ እኛ ፡
እያንዳንዳችን ፡ በተሰጠን ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ እየተረዳን ፡ ከሥራዋ ፡ መሳ
ተፍ ፡ አለብን ።

«እኔን ፡ ምን ፡ ያስተምረኛል?» ብለዋልን? ይስሙ ። እጅም ፡ ሆነ ፡
እግር ፡ ጆሮም ፡ ሆነ ፡ ጣት ፡ እንዲያው ፡ በሥጋ ፡ አካል ፡ ውስጥ ፡ አል
ገባም ። እዚያ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ለምክንያት ፡ ነው ። አንድ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡
እንዲሠራ ፡ ነው ። ያለ ፡ እርሱም ፡ አካሉ ፡ ጐደሎ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡
እርሰዎ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ እርስዎ ፡ ብቻ ፡ ሊሠሩ ፡ የሚችሉት ፡
አንድ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ አለዎ ።

እርስዎ ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ተጠሮተዋል ። ሆነዋ
ልን? እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ጠራዎ ፡ ምኑንም ፡ ነገር ፡
እደራ ፡ እንደ ፡ ሰጠዎ ፡ አስተውለዋልን ? [17] አስተውለው ፡ እንደ ፡ ሆነስ ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ፋንታዎን ፡ ይፈጽማሉን?

ይህች ፡ «በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የምትሆን ፡ ሐዋርያት ፡ የሰበሰቡአት ፡
እንዲት ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ » ታላቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መጣ
ሪያ ፡ ናት ። እርስዎ ፡ በእርስዎ ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ ነዎት ። «በታላቅ ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ መጥራት ፡ ተጠርቻለሁ ፡» እያሉ ፡ «መብትና ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡
አደራም ፡ ተሰጠኝ ። በመብቴ ፡ ልጠቀም ፡ እድሌን ፡ ላስተውል ! »
ብለው ፡ ለታላቅ ፡ ሥራ ፡ ይታጠቁ !

---

14. ኢሳ. ፵፫ ፡ ፳፩ ። 15. ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፮ ። ዘጸአ. ፲፱ ፡ ፭ ፡ ፮ ።
16. ፩ኤጥ. ፮ ፡ ፱ ። 17. ኤፌ. ፩ ፡ ፲፯—፲፱ ፡ ም. ፫ ፡ ፲፩—፲፱ ።

ምዕራፍ ፡ አንድ ።

በዚህ ፡ በመጀመሪያ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ከሐዋርያው ፡ ሰላምታ ፡ ቀጥሎ ፡ የምናነበው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ በክርስቶስ ፡ ለመባረክ ፡ ስላቀደው ፡ ዕቅድና ፡ እኛ ፡ «በእርሱ ፡» በክርስቶስ ፡ ስላገኘነው ፡ ጸጋ ፡ ነው ። በምዕራፉ ፡ ሁለተኛ ፡ እኩሌታ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በኤፌሶን ፡ መልእክት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ከሁለቱ ፡ ታላላቅ ፡ ጸሎቶች ፡ መጀመሪያውን ፡ እና ገኛለን ፡ እርሱም ፡ በክርስቶስ ፡ ያለንን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

መቅድም ። ቁ. ፩ ፡ ፪ ።

በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የሆነ ፡ ጳውሎስ ፡

በኤፌሶን ፡ ላሉት ፡ ቅዱሳን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ ላሉት ፡ ምእመናን ፤

ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ።

ጸሐፊው ፡ ጳውሎስ ፡ ነው ። ፲፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመርጠው ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ የተላኩ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እንዲሁም ፡ ጳውሎስ ፡ በክርስቶስ ፡ ተመርጦ ፡ ተልኮአል ። [1] ይህም ፡ የሆነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። [2] እንግዲያውስ ፡ መልእክቲቱ ፡ የምትመጣው ፡ በሐዋርያዊ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። የሚጽፍላቸውም ፡ ሰዎች ፡ በኤፌሶን ፡ ክተማና ፡ በአቅራቢያዋ ፡ የሚኖሩና ፡ በክርስቶስ ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ። ለእነርሱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ሰላምታን ፡ ያቀርባል ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «በኤፌሶን ፡ ላሉት ... በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ ላሉት ። (ቁ. ፩ ።) ይኸውልዎ ፡ እነኝህ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ በሁለት ፡ ስፍራዎች ፡ ናቸው! በኤፌሶን ፡ ናቸው ፡ በክርስቶስም ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ የምንማረው ፡ የትም ፡ ዘንድ ፡ ብንገኝና ፡ ሁኔታችን ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ በክርስቶስም ፡ ልንሆን ፡ እንደምንችል ፡ ነው ። «በዓለም ፡ ሳላችሁ ፡ መከራ ፡ አለባችሁ ፡ በእኔ ፡ ግን ፡ ሰላም ፡ ይሆንላችኋል ፡» እንደ ፡ ተባለው ፡ ነው ። [3]

ለ) «በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ላሉት» ። (ቁ. ፩ ።) «በክርስቶስ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው?» ቢሉ ፡ በኤፌሶን ፡ ወይም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ያስቡ ። የሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ፤ የዚያችን ፡

1. ማር. ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። የሐዋ. ፱ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ። 2. የሐዋ. ፳፪ ፡ ፲፱ ።
3. ዮሐ. ፲፮ ፡ ፴፫ ።

ከተማ ፡ አየር ፡ ይተነፍሳሉ ፡ ሕይወትዎን ፡ በዚያች ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሳልፋሉ ። ለከተማው ፡ የሚደርሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስታም ፡ ሆነ ፡ መከራ ፡ ለእርስዎ ፡ ደግሞ ፡ ይደርሳል ። እርስዎ ፡ የዚያች ፡ ከተማ ፡ ቊራጭ ፡ ወይም ፡ ክፍል ፡ ነዎት ፤ ሥር ፡ በመሬት ፡ ቅርንጫፍ ፡ በግንድ ፡ ክንድ ፡ በእካል ፡ ዓሣ ፡ በባሕር ፡ እንዲሁም ፡ አማኝ ፡ በክርስቶስ ፡ ነው ። ያመነ ፡ ሰው ፡ በክርስቶስ ፡ ነው ፡ ያለ ፤ በክርስቶስ ፡ ያልሆነም ፡ አማኝ ፡ (ክርስቲያን ፡) አይደለም ።

ሐ) «ቅዱሳን» ። (ቁ. ፩ ።) መቀደስ ፡ የተባለው ፡ ግሥ ፡ መለየት ፡ ማለት ፡ ነው ። የተቀደሰ ፡ ዕቃም ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ ከዓለም ፡ ግልጋሎት ፡ ተለይቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ነው ። «ቅዱሳን ፡» የተባሉቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ የተለዩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ። [4]

ቁ. ፫—፲፬ ።

በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ሁሉን ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዘላለማዊ ፡ አሳብ ።

፫ ፡ በክርስቶስ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ሁሉ ፡ የባረከን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡
፬ ፡ ይባረክ ። ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በፊቱ ፡ ቅዱሳንና ፡ ነውር ፡ የሌ
፭ ፡ ለን ፡ በፍቅር ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ መረጠን ። በበጎ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥራ ፡ ለእርሱ ፡
፮ ፡ ልጆች ፡ ልንሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ወሰነን ። በውድ ፡ ልጁም ፡ እን
ዲያው ፡ የሰጠን ፡ የጸጋው ፡ ክብር ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡
፯ ፡ አደረገ ። በውድ ፡ ልጁም ፡ እንደ ፡ ጸጋው ፡ ባለጠግነት ፡ መጠን ፡
በደሙ ፡ የተደረገ ፡ ቤዛነታችንን ፡ አገኘን ፡ እርሱም ፡ የበደላችን ፡
፰ ፡ ስርየት ። ጸጋውንም ፡ በጥበብና ፡ በአእምሮ ፡ ሁሉ ፡ አበዛልን ።
፱ ፡ በክርስቶስ ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ እንደ ፡ አሳቡ ፡ የፈቃዱን ፡
፲ ፡ ምሥጢር ፡ አስታውቆናልና ፤ በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡
ያለው ፡ አሳቡም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በክ
፲፩ ፡ ርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ፡ ነው ። እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ምክር ፡ ሁሉን ፡
የሚሠራ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ አሳብ ፡ አስቀድመን ፡ የተወሰንን ፡
፲፪ ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ርስትን ፡ ተቀበልን ። ይኸውም ፡ በክርስ
ቶስ ፡ አስቀድመን ፡ ተስፋ ፡ ያደረግን ፡ እኛ ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡
፲፫ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እናንተም ፡ ደግሞ ፡ የእውነትን ፡ ቃል ፡
ይኸውም ፡ የመዳናችሁን ፡ ወንጌል ፡ ሰምታችሁ ፡ ደግሞም ፡
በክርስቶስ ፡ አምናችሁ ፡ በተስፋው ፡ መንፈስ ፡ በመንፈስ ፡

4. የሐዋ. ፱ ፡ ፲፫ ፡ ፴፪ ። ም. ፳፯ ፡ ፲ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ም. ፲፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ።
ፊጢሞ. ፩ ፡ ፲ ።

፲፬ ፤ ቅዱስ ፡ ታተማችሁ ፤ እርሱም ፡ የርስታችን ፡ መያዣ ፡ ነው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ እስኪዋጅ ፡ ድረስ ፡ ይህም ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ ይሆናል ።

በታላቅ ፡ በረከት ፡ የባረከን ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ይባረክ ፡ ይመስገንም ፡! በእምነት ፡ በተቀመጥንበት ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ በምንና ፡ በምን ፡ ያለ ፡ በረከት ፡ በክርስቶስ ፡ ባርኮናል! ዓለም ፡ ሳይፈጠር «እስቀድሞ ፡» ከተባለ ፡ ዘመን ፡ [5] ጠልቀው ፡ ገብተው ፡ መርምረው ፡ ሁሉን ፡ በሚያዩ ፡ ዓይኖቹ ፡ ፊት ፡ ቅዱሳንና ፡ ለመሥዋዕት ፡ እንደተመረጡት ፡ በጎች ፡ ሆነን ፡ ነውር ፡ የሌለን ፡ እንድንሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ መረጠን ። [6] ቅዱሳንና ፡ ነውር ፡ የሌለን ፡ እንድንሆን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ የእርሱ ፡ ልጆች ፡ እንድንሆን ፡ ወሰነን ። ይህንም ፡ ያደረገው ፡ በተወደደ ፡ ልጁ ፡ በክርስቶስ ፡ እንዲያው ፡ የተሰጠን ፡ ጸጋው ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። [7] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቀጠለና ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ የበደላችንን ፡ ስርየት ፡ አስገኝልን ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ በደሙ ፡ ሲቤዠን ፡ (ሲዋጀን ፡) ነው ። [8] ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገው ፡ በጸጋው ፡ ነው ፤ ያም ፡ ጸጋ ፡ ምንኛ ፡ ታላቅ ፡ ነው! ጸጋውንም ፡ እያበዛ ፡ አእምሮአችንን ፡ ከፈተ ፡ በክርስቶስም ፡ ለማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰነውን ፡ አሳብ ፡ ለማወቅ ፡ አስቻለን ። ይኸው ፡ አሳብ ፡ አስክ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ምሥጢር ፡ ሆኖ ፡ ቈይቶ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ተገልጠአል ። አሳቡስ ፡ ምንድር ፡ ነው! ቢባል ፡ አሳቡማ ፡ በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ፡ ነው! እግዚአብሔር ፡ ያሰበውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ግብ ፡ ለማድረስ ፡ ችሎታ ፡ አለውና ፡ እኛ ፡ ልጆቹ ፡ ለመሆን ፡ አስቀድመን ፡ የተወሰንን ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ርስትን ፡ ተቀበልን ። [9] የወረስነውም ፡ እኛ ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ የሆንን ፡ ሰዎች ፡ ሰታላቁ ፡ አምላካችን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ እናንተ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ የሆናችሁ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ያችን ፡ ርስት ፡ ለመቀበላችሁ ፡ ተስፋ ፡ በሚሰጥ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታትማችኋል ፤ ይህም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሁላችን ፡ አይሁድም ፡ አሕዛብም ፡ ያችን ፡ ርስት ፡ እንደምንቀበል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ ለእርሱ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ እስክሚዋጅበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ መያዣችን ፡ ነው ። [10]

ማሰገንዘቢያ ። ሀ) «በክርስቶስ» (ቊ. ፫ ።) ሁሉም ፡ «በክርስቶስ» ነው ። ማለት ፡ የተደረገልን ፡ በክርስቶስ ፡ ሥራ ፡ የሚመጣልን ፡ በክርስቶስ ፡ አማካይነት ፡ የሚገኘውም ፡ በክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። የተባረከን ፡ በክ

5. ዘፍጥ. ፩ ፡ ፩ ። 6. ዘሌዋ. ፳፪ ፡ ፲፱—፳፩ ። 7. ማቴ. ፫ ፡ ፲፯ ። ዘዳግ. ፯ ፡ ፮—፰ ። 8. ዘዳግ. ፲፭ ፡ ፲፭ ። ራእይ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ዘጸአ. ፲፭ ፡ ፲፫ ። 9. ቊ. ፭ ። ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፫—፭ ። ቈላ. ፩ ፡ ፲፱ ። 10. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፫ ። ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፭ ። ኤፌ. ፩ ፡ ፴ ።

ርስቶስ ፡ ነው ፡ (ቊ. ፫) ፡ የተመረጥን ፡ በክርስቶስ ፡ (ቊ. ፬) ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የሆንን ፡ በክርስቶስ ፡ ነው ፡ (ቊ. ፭) ። በክርስቶስ ፡ ቤዛ ነታችንን ፡ አገኘን ፡ (ቊ. ፯) ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለእኛ ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ አቅዶአል ፡ (ቊ. ፱) ፡ በመጨረሻ ፡ ዘመንም ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በክርስቶስ ፡ ይጠቀልላል ። (ቊ. ፲) ። አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ለአንተ ፡ በክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ተገን ዝበሃልን?

ለ) «በሰማያዊ ፡ ስፍራ ።» (ቊ. ፫ ።) እኛ ፡ ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ብንኖርም ፡ በሰማይ ፡ ደግሞ ፡ እንኖራለን ። አገራችን ፡ በሰማይ ፡ ነው ። [11] እግዚአብሔር ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ሁሉ ፡ የባረከን ፡ እዚያ ፡ ነው ። «በክርስቶስ» ያገኘነው ፡ በረከት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ ግዙፍ ፡ በረከት ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ይባርከናል ፤ ሆኖም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ደካማዎችና ፡ ድኾች ፡ የተናቅንም ፡ እንሆን ፡ ይሆናል ። [12] የተባረክን ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ነው ፡ የምንባረክም ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋር ፡ በተቀመጥንበትና ፡ ያች ፡ ርስት ፡ ባለችበት ፡ በሰማይ ፡ ነው ። [13] ክርስቶስ ፡ «መዝገብህ ፡ ባለበት ፡ ልብህ ፡ ደግሞ ፡ እዚያ ፡ ይሆናል» እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ሕይወታችን ፡ በሰማይ ፡ ነው ፡ በሰማይ ፡ ያለውን ፡ እናስባለን ፡ የምንመለከተውም ፡ ወደዚያ ፡ ነው ፡ ተስፋ ፡ የምናደርገውም ፡ ከዚያ ፡ ነው ። [14] እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ሁሉ ፡ በጸጋና ፡ በሰላም ፡ በተትረፈረፈ ፡ ሕይወትና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ስጦታ ፡ ሁሉ ፡ የባረከን ፡ በሚባርከንም ፡ በዚህ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ነው ። [15] እዚያ ፡ እንደ ፡ ሆንን ፡ እንኑርና ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ እንጠቀም ።

ሐ) «የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ » (ቊ. ፫ ።) እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ጌታችን ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ ማሰብ ፡ ለእኛ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። «ምነው ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለምን?» እንላለን ። ነው! ቢሆንም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ሳለ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ «አባቴ ፡» «አምላኬም ፡» ብሎታል ። [16] ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ እንደሆነ ፡ እናያለን ፡ እንጂ ፡ ምሥጢሩን ፡ ልንፈታ ፡ አንችልም ። ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ነው ።

መ) «ዓለም ፡ ሳይፈጠር ...መረጠን ።» (ቊ. ፬) ። እግዚአብሔር ፡ የመረጠን ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ነው ፡ እንዴ? የሚመርጥ ፡ እንደ ፡ ሥራችን ፡ አይደለምን? አይደለም! መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ስለዚህ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመራረጥ ፡ ይናገራል ፡ ምርጫ ፡ የተደረገውም ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠርና ፡ እንደ ፡ ግል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡

11. ፊልጵ. ፫ ፡ ፳ ። 12. ፩ቆሮ. ፩ ፡ ፳፯—፳፱ ። 13. ም. ፪ ፡ ፮ ። ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፫—፭ ። 14. ማቴ. ፮ ፡ ፳፩ ። ቈላ. ፫ ፡ ፩—፫ ። 15. ዮሐ. ፲ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ፡ ፳፯ ። 16. ዮሐ. ፲፯ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፳፪ ። ማቴ. ፳፯ ፡ ፵፮ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፲፯ ።

ብቻ ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘባለን ። [17] እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ መርጦአል ፡ የተመረጡትም ፡ ወንጌልን ፡ ሰምተው ፡ ያምናሉ ፡ ይድናሉም ። ይሁን ፡ አንጂ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ «የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡» ተባለ ፡ ከርስቶስም ፡ ዓለምን ፡ በሞላ ፡ ወዶአል ፡ ለዓለምም ፡ ለው ፡ ሁሉ ፡ ሞቶአል ። [18] እዚህ ፡ ደግሞ ፡ ልንረዳ ፡ የማንችለው ፡ ምሥጢር ፡ ተገኘ! በአንድ ፡ በኩል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመርጣል ፡ ተባለ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እንደየሰው ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ተባለ ። ምሥጢር ፡ በየጊዜው ፡ በመገኘቱም ፡ አንጨነቅ ። እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እኛም ፡ ሰዎች ፡ ነን ። እኛ ፡ የአምላክን ፡ አሳብና ፡ ድርጊት ፡ ሁሉ ፡ ልናስተውል ፡ አንችልም ። [19] የእኛ ፡ አእምሮ ፡ የተወሰነ ፡ ጽንፍ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ያልተወሰነ ፡ ጽንፍ ፡ የሌለው ፡ ነው ። ነገሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደሚገልጥልን ፡ መሆኑን ፡ እንመን ፡ ምሥጢሩንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንተወው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነውና ፡ ከፍርድም ፡ በታች ፡ ነውና ፡ የሚያስገርመው ፡ ከእንዳንዶቹ ፡ ምህረትን ፡ መከልከሉ ፡ ሳይሆን ፡ ለአንዳንዶቹ ፡ ጸጋ ፡ መስጠቱ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የተመረጥን ፡ በፊቱ ፡ ቅዱሳንንና ፡ ነውር ፡ የሌለን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ እንደሆነ ፡ እንገንዘብ ።

ሠ) «በውድ ፡ ልጁ ፡ እንዲያው ፡ የሰጠን ፡ የጸጋው ፡ ክብር ፡ ...እንደ ፡ ጸጋው ፡ ባለጠግነት ፡ መጠን ፡ ...» (ቊ. ፮ ፡ ፯ ፡) ጸጋ ፡ እንዲያው ፡ የተሰጠ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ እንዲያው ፡ በጸጋው ፡ እንደ ፡ መረጣቸው ፡ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ ልጆቹ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ በጸጋው ፡ ወሰነን ። የበደላችንን ፡ ስርየት ፡ ያገኘንም ፡ እንዲያው ፡ በጸጋው ፡ ነው ። [20] እኛ ፡ ተገቢዎች ፡ ስለ ፡ ሆንን ፡ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲያው ፡ በጸጋው ፡ ምህረቱን ፡ ስላፈሰሰልን ፡ ነው ።

ረ) «በጥበብና ፡ በአእምሮ ፡ ሁሉ ።» (ቊ. ፰ ።) መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየጊዜው ፡ ይነግረናል ፡ መምህራንና ፡ ለባኪዎችም ፡ ይነግሩናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ አእምሮአችንን ፡ ካልከፈተልን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋው ፡ ያደረገልንን ፡ ልናስታውል ፡ አንችልም ። [21] ልዑል ፡ አምላክ ፡ ይህን ፡ መንፈሳዊ ፡ ጥበብና ፡ አእምሮ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰጠን ፡ እንለምነው ! [22]

ሰ) «የፈቃዱ ፡ ምሥጢር ።» (ቊ. ፱ ።) ምሥጢር ፡ የተባለው ፡ ቀድሞ ፡ የተሰወረው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የተገለጠው ፡ ነገር ፡ ነው ። ጳውሎስ ፡ በዚህ ፡ በኤፌሶን ፡ መልእክት ፡ ላይ ፡ ስለዚህ ፡ ምሥጢር ፡ አያሌ ፡ ጊዜአት ፡ ይናገራል ። (ም. ፩ ፡ ፱ ። ም. ፫ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፱ ።) ምሥጢሩስ ፡ ምንድር ፡ ነው? ምስጢሩ ፡ ፩ኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ፡

17. ዘዳግ. ፯ ፡ ፮—፰ ፡ ፱ ፡ ፲—፲፭ ። የሐዋ. ፲፫ ፡ ፵፩ ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፱—፲፯ ። ኤፌ. ፩ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ። ፪ተሰ. ፪ ፡ ፲፫ ። ፪ጢሞ. ፩ ፡ ፱ ። ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፪ ። 18. ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ዮሐ. ፫ ፡ ፲፯ ። 19. ኢሳ. ፶፭ ፡ ፰ ፡ ፱ ። 20. ዘዳግ. ፯ ፡ ፮—፰ ። ኤፌ. ፪ ፡ ፬—፱ ። 21. ሉቃ. ፳፬ ፡ ፵፭ ። 22. ቈላ. ፩ ፡ ፯ ። ኤፌ. ፩ ፡ ፲፯ ።

(ለማዋሐድ ፡) ማቀዱ ፡ ነው ፤ ፪ኛውም ፡ ይህን ፡ የሚያደርገው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አማካይነት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ሸ) «በዘመን ፡ ፍጻሜ ።» (ቊ. ፲ ።) ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ አልፈዋል ፡ ምናልባትም ፡ ያልፋሉ ። [23] በእነዚያም ፡ ዘመናት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ አሳቡን ፡ ወደ ፡ ግብ ፡ ሰማድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ ቈይቶአል ። አብ ፡ በኃላ ፡ ሥልጣኑ ፡ ያደረጋቸው ፡ ወራትና ፡ ዘመናት ፡ ባለፉና ፡ ባለቁ ፡ ጊዜም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አሳቡን ፡ ወደ ፡ ግብ ፡ ያደርሳል ፡ ሁሉንም ፡ በክርስቶስ ፡ ይጠቀልላል ። ክርስቶስ ፡ የሚመለስበት ፡ ፍጥረት ፡ የሚናፍቀው ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ልጆች ፡ የሚገለጡበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሁሉም ፡ በክርስቶስ ፡ የሚጠቀለልበት ፡ ዘመን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። [24]

ቀ) «በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያሰውን ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ።» (ቊ. ፲ ።) ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ መለያየት ፡ አብሮ ፡ ገባ ። ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለይቶ ፡ ወጣ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ኖረ ። ይህም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ተለያየ ፡ ሰው ፡ ከእንስሶች ፡ ተለያየ ፡ ፍጥረትም ፡ በሞላ ፡ ተነጣጠለ ፡ ተቈራረጠ ፡ ሁሉም ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ፡ ለሁሉም ፡ ፍች ፡ መቃረቢያም ፡ (መገናኛም ፡) ጠፋ ። [25]

ሁሉን ፡ በክርስቶስ ፡ እቅንቶ ፡ ለመመለስ ፡ ለማዋሃድ ፡ ደምሮም ፡ በእርሱ ፡ ለመጠቅለል ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ እግዚአብሔር ፡ ቈረጠ ። ለውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ አስታርቆ ፡ የድሮውን ፡ አንድነት ፡ (ጎብረት ፡) የመሰለው ፡ ለውንም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ አይሁድን ፡ ከአሕዛብና ፡ ጥቈርን ፡ ከነጭ ፡ ጋር ፡ አሠሪን ፡ ከሠራተኛውና ፡ ሀብታምን ፡ ከድኃ ፡ ጋር ፡ አስታርቆ ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደረገ ፡ ስማያትን ፡ ከምድር ፡ ያገናኘ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ እንዲኖር ፡ ያበጀ ፡ ከርስቶስ ፡ ነው ። በሰማይና ፡ በምድር ፡ ክርስቶስ ፡ ጠቅላይና ፡ መጠቅለያ ፡ ነው ፡ ሁሉ ፡ በሁሉም ፡ ነው ። [26]

በ) «ርስትን ፡ ተቀበልን ።» (ቊ. ፲፩ ።) የእግዚአብሔርን ፡ አሳብ ፡ ሊከለክል ፡ የሚችል ፡ አንዳች ፡ የለም ። ያለበው ፡ ነገር ፡ ያሰ ፡ ጥርጥር ፡ ወዳሰበው ፡ ዘንድ ፡ ይደርሳል ። [27] ይደርሳልና ፡ እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ ርስትን ፡ ተቀበልን ። «ምን ፡ ርስት ፡ ነው?» ቢሉ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ከብር ፡ ነው ፡ ታድለን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ለዘላለም ፡ መኖር ፡ ነው ። [28] የቅዱሳን ፡ ርስት ፡ ነው ፡ የሚገኝበትም ፡ በብርሃን ፡

3. የሐዋ. ፩ ፡ ፯ ። 24. ገላ. ፬ ፡ ፬ ። ፩ቆሮ. ፲፭ ፡ ፳፬ ፡ ፳፰ ። የሐዋ. ፫ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፱—፳፪ ። 25. ዘፍጥ. ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፳፬ ። ዘጸአ. ፳፭ ፡ ፴፩—፴፫ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፩ ። መክ. ፩ ፡ ፩—፲፬ ። 26 ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ። ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ቈላ. ፫ ፡ ፲፩ ። ራእይ ፡ ፳፩ ፡ ፪—፯ ። ቈላ. ፫ ፡ ፲፩ ። 27. ፊልጵ. ፩ ፡ ፮ ። ፩ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፫—፶፮ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴ ። ፪ቆሮ. ፬ ፡ ፲፯ ። ቈላ. ፫ ፡ ፬ ። ፩ተሰ. ፪ ፡ ፲፪ ። 28 ዕብ. ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ።

ወይም ፡ በሰማይ ፡ ነው ። [29] የምንቀበልበትም ፡ ጊዜ ፡ በቤዛ ፡ ወይም ፡ በመዋጀት ፡ ቀን ፡ ነው ። [30]

ተ) «እኛ ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ።» (ቊ. ፲፪ ።) ወን ድሜ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ አይተሃልን? ተገንዝበሃልን? እኛ ፡ እኮ ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ እንሆን ፡ (እንኖር ፡) ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ ተወስ ነናል! እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ በእኛም ፡ በኩል ፡ ያደረገውን ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ አይተው ፡ ሰውና ፡ መልአክም ፡ ተገርመው ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ክብርን ፡ ይሰጣሉ! (ም. ፪ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ም. ፫ ፡ ፲ ።) ምንናምን ፡ የነበ ርን ፡ እንዲህ ፡ ሆንን ፡ በፍጹም ፡ ዓቅመ ፡ ቢሶች ፡ የነበርን ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሠራን ። ያንተ ፡ ሕይወት ፡ የእኔም ፡ በጣም ፡ ለክብሩ ፡ ይሁን ፡ ይህ ንም ፡ ያደርግልን ፡ ዘንድ ፡ ሕይወታችንን ፡ ለእርሱ ፡ እንስጥ ።

ቸ) «በተስፋው ፡ መንፈስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታተማችሁ ፤ እር ሱም ፡ የርስታችን ፡ መያዣ ፡ ነው ።» (ቊ. ፲፫ ፡ ፲፬ ።) የተስፋው ፡ መን ፈስ ፡ በተስፋ ፡ የተሰጠው ፡ መንፈስና ፡ ተስፋም ፡ የሚሰጥ ፡ መንፈስ ፡ ነው ። [31] መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ርስትን ፡ ለመውረሳችን ፡ ፩ኛ ፡ ማኅ ተም ፡ («ታተማችሁ») ፡ ፪ኛ ፡ መያዣ ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ እንድ ፡ ውል ፡ የሚረጋገጥ ፡ (የሚጸና ፡) በማኅተም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ርስት ፡ ለመውረሳችን ፡ ማኅተም ፡ ነው ። እርሱ ፡ ተሰጥቶናል ፡ በስጦታዎቹም ፡ በተለይም ፡ በፍሬዎቹ ፡ ይታወቅብናል ። [32] መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መቀበላችንን ፡ ካወቅን ፡ ርስትን ፡ ለመውረሳችን ፡ የጸና ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

፪ኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ደግሞ ፡ መያዣ ፡ ነው ። መያዣ ፡ (ቀብድ) የቀረው ፡ በኋላ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ማረጋገጫና ፡ ምልክት ፡ ነው ። [33] እንዲ ሁም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሙሉውን ፡ ርስት ፡ በኋላ ፡ እንደምንቀበል ፡ ያ ፡ ቀን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ መያዣ ፡ ነው ። [34]

ቊ. ፲፭ — ፳፫ ።

ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ ያላቸውን ፡ ታላቅ ፡ እድል ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያው ፡ ጸሎት ።

፲፭ ፤ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚሆን ፡ በጌታ ፡ በኢ የሱስ ፡ ስለ ፡ ማመንና ፡ ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ስለሚሆን ፡ መውደድ ፡
፲፮ ፤ ሰምቼ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እያመሰገንሁ ፡ ስጸልይ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡

29. ቁላ. ፩ ፡ ፲፱ ። ፩ኤጥ. ፩ ፡ ፫—፩ ። 30. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፱—፳፪ ። 31. ኢዮ. ፪ ፡ ፳፰ ። ዮሐ. ፲፬ ፡ ፳፯ ። የሐዋ. ፩ ፡ ፬ ፡ ፭ ፤ ፪ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ። 32. ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፰—፲ ። ገላ. ፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። 33. ፪ቆሮ. ፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። 34. ዘፍጥ. ፴፰ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፪ቆሮ. ፩ ፡ ፳፪ ፤ ፭ ፡ ፭ ።

፲፯ ፤ ማሳሰብን ፡ አልተውም ፤ የክብር ፡ አባት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ እርሱን ፡ በማወቅ ፡ የጥበብንና ፡ የመገለጥን ፡
፲፰ ፤ ፲፱ ፤ መንፈስ ፡ እንዲሰጣችሁ ፡ እለምናለሁ ። ይህም ፡ የልባችሁ ፡ ዓይኖች ፡ ሲበሩ ፡ የመጥራቱ ፡ ተስፋ ፡ ምን ፡ እንዲሆን ፡ በቅዱ ሳንም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የርስት ፡ ክብር ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ምን ፡ እንዲሆን ፡ ሰምናምንም ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ የኃይሉ ፡ ታላቅ
፲፱፣፳፣፳፩ ፤ ነት ፡ ምን ፡ እንዲሆን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ኃይል ፡ ክርስቶስንም ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣውና ፡ ከአለቅነትና ፡ ከሥልጣ ንም ፡ ከኃይልም ፡ ከጌትነትም ፡ ሁሉ ፡ በላይና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሊመጣ ፡ ባለው ፡ ዓለም ፡ ደግሞ ፡ ከሚጠራው ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ በቀኙ ፡ ሲያስቀምጠው ፡ በክርስቶስ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደ ፡ ብርታቱ ፡ ጕልበት ፡ ሥራ ፡
፳፪ ፤ መጠን ፡ ነው ፤ ሁሉንም ፡ በእግሩ ፡ በታች ፡ አስገዛለት ፡ ከሁሉ ፡ በላይም ፡ ራስ ፡ እንዲሆን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
፳፫ ፤ ሰጠው ። እርስዋም ፡ አካሉና ፡ ሁሉን ፡ በሁሉ ፡ የሚሞላ ፡ የእ ርሱ ፡ ሙላቱ ፡ ናት ።

ሐዋርያው ፡ በኢየሱስ ፡ ስለ ፡ ማመናቸውና ፡ ክርስቲያንን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መውደዳቸው ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ ሊጸልይላቸው ፡ በመንፈሱ ፡ ተግ ድዶአል ። አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መገኘታቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግ ናል ፡ ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንርሱን ፡ በጸሎት ፡ ያቀ ርባል ፡ ይማልድላቸውማል ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የሚፈልገው ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ የጥበብና ፡ የመገለጥ ፡ መንፈስ ፡ እን ዲሰጣቸው ፡ ይለምናል ። የልባቸው ፡ ዓይኖች ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲበሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያላቸውን ፡ ሀብት ፡ እርሱም ፡ የመጥራቱ ፡ ተስፋና ፡ የርስቱ ፡ ክብር ፡ ባለጠግነት ፡ የኃይሉም ፡ ታላቅነት ፡ ምንና ፡ ምን ፡ እን ደ ፡ ሆኑ ፡ ሊያዩና ፡ ሊገነዘቡ ፡ ሊያውቁም ፡ ይችላሉ ። ኃይሉም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። የብርታቱ ፡ ጕልበት ፡ ኃይልማ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ አስነሥቶአል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ በማይባል ፡ መጠን ፡ ከሁሉም ፡ በላይ ፡ አስ ቀምጦታል ፡ ሁሉንም ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አስገዝቶለታል ፡ ከሁሉም ፡ በላይ ፡ ራስ ፡ እንዲሆን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጥቶታል ። ይኸውም ፡ ኃይል ፡ ለእነርሱ ፡ ነው ፡ በእነርሱም ፡ ይሠራል ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማመንና ፡ ቅዱሳንን ፡ ሁሉ ፡ ማፍቀር ፡ (ቊ. ፲፭ ፡) እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የእውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ። [35] በእኛስ ፡ ይታያሉን ?

ለ)«እያመሰገንሁ ፡ ስጸልይ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ማሳሰብን ፡ አልተውም ።» (ቊ. ፲፮ ፡) በጎቹ ፡ የትም ፡ ዘንድ ፡ ቢገኙ ፡ እውነተኛ ፡ እረኛ ፡ ይጸል

35. ዮሐ. ፲፫ ፡ ፴፭ ።

ይላቸዋል ። [36] በእነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ ለጸሎት ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ መኖሩን ፡ እናያለን ፡ እነርሱም ፡ ፩ኛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመስገን ፡ ፪ኛም ፡ ለሌሎች ፡ መማለድ ፡ ናቸው ። [37] እኛ ፡ ስንጸልይ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ልብ ፡ እናድርግ ። ለመሆኑ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ለሚኖሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እኛ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንጸልያለን? ስለ ፡ እነርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሳሰብ ፡ እናዘወትር ።

ሐ) «እርሱን ፡ በማወቅ ፡ የጥበብንና ፡ የመገለጥን ፡ መንፈስ ፡ እንዲሰጣችሁ ፡ እለምናለሁ ።» (ቍ. ፲፯ ።) ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይሆን ፡ ራሱን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካላወቅን ፡ በእርሱ ፡ ያለውን ፡ ለእኛ ፡ የሚሆነውን ፡ ልናውቅ ፡ አንችልም ። ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «ከእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በቀር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ማንም ፡ አያውቅም» ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ነው ። [38] የጥበብና ፡ የመገለጥ ፡ መንፈስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የልቦናችንን ፡ ዓይኖች ፡ ካላበራ ፡ ዓይኖቻችን ፡ ዕውር ፡ ናቸውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልናውቅና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገሮች ፡ ልናይ ፡ አንችልም ። [39] የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ አያደርስምና ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ነገሮቹን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ገለጣ ፡ ልዩ ፡ የዓይን ፡ መክፈት ፡ ያስፈልገናል ። [40] ብዙዎች ፡ የማያስተውሉት ፡ የልቦናቸው ፡ ዓይኖች ፡ ስላልተከፈቱ ፡ ነው ። [41] ይህን ፡ ልዩ ፡ ገለጣ ፡ ይስጠን ፡ ዘንድ ፡ የከብር ፡ ሁሉ ፡ ባለቤት ፡ የሆነ ፡ አምላካችንን ፡ እንለምነው ።

መ) «የመጥራቱ ፡ ተስፋ ፡ የርስት ፡ ከብር ፡ የኃይል ፡ ታላቅነት ።» (ቍ. ፲፰ ፡ ፲፱ ።) እነኝህ ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ለእኛ ፡ ናቸው ።

፩ ፡ የመጥራቱ ፡ ተስፋ ። እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ጠርቶናል ። «ወደ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ጠራን?» ቢሉ ፡ አጭሩ ፡ መልስ ፡ «ወደ ፡ ከብር ፡ ጠራን ፡» የሚል ፡ ነው ። [42] ከብርስ ፡ ምንድር ፡ ነው? ከብርማ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚኖርበት ፡ ነው ፡ እኛም ፡ የዚህ ፡ ክብር ፡ ተካፋዮች ፡ ለመሆን ፡ ተጠርተናል ። እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ኃጢአታችንን ፡ በማስወገድ ፡ አጽድቆናል ፡ ቀድሶናልም ፡ እንድንከብርም ፡ ዐቅዶአል ። [43] እኛ ፡ ወደ ፡ ከብር ፡ የእግር ፡ መንገዳችንን ፡ ይዘናል ። ወደ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ተጠራን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብቻ ፡ ሊገልጥልን ፡ ይችላል ፡ ይገልጥልናልም ። ዓይናችንን ፡ በከብር ፡ ተስፋ ፡ ላይ ፡ ተክለን ፡ እንጓዝ ።

36. ፩ሳሙ. ፲፪ ፡ ፳፫ ። 37. ፊልጵ. ፩ ፡ ፮ ። ፩ተሰ. ፭ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፩ጢሞ. ፪ ፡ ፩—፬ ። 38. ፩ቆሮ. ፪ ፡ ፲—፲፪ ። 39. ኢሳ. ፲፩ ፡ ፪ ። ፩ቆሮ. ፪ ፡ ፲—፲፬ ። ዮሐ. ፫ ፡ ፫ ። ፪ቆሮ. ፬ ፡ ፬ ። 40. ፩ቆሮ. ፩ ፡ ፳፩ ። ገላ. ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ኤፌ. ፫ ፡ ፫ ። 41. ማቴ. ፮ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። 42. ፩ተሰ. ፪ ፡ ፲፪ ። ፪ተሰ. ፪ ፡ ፲፬ ። ፩ጴጥ. ፭ ፡ ፲ ። 43. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴ ።

፪ ፡ በቅዱሳንም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የርስት ፡ ክብር ፡ ባለ ፡ ጠግነት ። ይህን ፡ በሁለት ፡ በኩል ፡ እናስብ ። እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ አለው ፡ እኛም ፡ በእርሱ ፡ ርስት ፡ አለን ።

እስራኤል ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ነበረች ። [44] እኛም ፡ ከርስቲያኖች ፡ ዛሬ ፡ የከበርን ፡ ርስቱ ፡ ነን ። [45] እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፡ እንዲሁም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እኛን ፡ ይወዳል ፡ ዋጋው ፡ እንደ ፡ በዛ ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ ዕቃውም ፡ ይመስከተናል ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምንሆነውን ፡ ይግለጽልን!

በሁለተኛ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያወረሰንን ፡ ርስት ፡ እናስብ ፤ በክርስቶስ ፡ አውርሶናልና ። [46] ክብሩ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ያለው ፡ ርስት ፡ ነውና ፡ የሚጠቅም ፡ ርስት ፡ ነው! ስለዚህ ፡ ርስት ፡ በቍ. ፲፩ ፡ ላይ ፡ አንብበናል ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያለልንን ፡ የርስት ፡ ክብር ፡ ባለ ፡ ጠግነትን ፡ ይግለጽልን!

፫ ፡ ለምናምን ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ የኃይሉ ፡ ታላቅነት ። ሞላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ለክርስቲያን ፡ ተቀምጦአል ፡ ለክርስቲያንም ፡ ያገለግላል ። ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ መካከል ፡ ለይቶ ፡ አስነሥቶ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ድረስ ፡ ያደረሰው ፡ ኃይል ፡ ተቀምጠልናል ። ደካማዎችና ፡ ምስኪኖች ፡ መሆናችን ፡ ይሰማናል? «እጸና ፡ ዘንድ ፡ ክቶ ፡ አልችልም ፡ ሳልወድቅ ፡ አልቀርም ፡ » ወይስ ፡ «አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አልችልም ፡ አልበቃም ።» እንላለን? እሺ ፡ አይደለም! በም. ፫ ፡ ፭ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ እንመልከት ። ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ኃይል ፡ እንዳሰልን ፡ በእኛም ፡ እንደሚሠራ ፡ ሐዋርያው ፡ ያረጋግጣል ። «ክርስቲያን ፡» መባል ፡ የሚያኮራ ፡ ነገር ፡ ቢሆንም ፡ የክርስቲያንን ፡ ተስፋ ፡ የክርስቲያን ፡ የርስቱ ፡ ክብር ፡ ባለጠግነትን ፡ ለክርስቲያን ፡ የተቀመጠውን ፡ ኃይል ፡ ማወቅ ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ ነው ። የጥበብና ፡ የመገለጥ ፡ መንፈስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ የልቦናችንን ፡ ዓይኖች ፡ ያብራልን! አሜን ።

ሠ) «ከሚጠራው ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ።» (ቍ. ፳፩ ።) ስለዚህ ፡ ስም ፡ በፊልጵ. ፪ ፡ ፱—፲፩ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እናነባለን ። ከሌላ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡ ስም ፡ ነው ። [47] በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ትልቅ ፡ ስም ፡ ሞልቶአል ፡ እኛም ፡ እንደሚገባን ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ ያንንም ፡ እናከብራለን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ የኢየሱስ ፡ ስም ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ነው ። መብለጥ ፡ ይቅርና ፡ የሚተካከለው ፡ ስም ፡ የለም ።

44. ዘዳግ. ፴፪ ፡ ፱ ። ፩ሳሙ. ፲ ፡ ፩ ። መዝ. ፻፮ ፡ ፭፩ ። ፩ጴጥ. ፪ ፡ ፱ ። 45. ዘጸአ. ፲፱ ፡ ፭ ፡ ፮ ። 46. ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። 47. ዘጸአ. ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ረ) «ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ራስ ፡ እንዲሆን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጠው ። እርስዋም ፡ አካሉ ፡ ናት ።» (ቊ. ፳፪ ፤ ፳፫ ።) በዓለማት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ራስ ፡ የሆነውን ፡ ክርስቶስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሰጠው ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ ናት ። [48]

እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደዚሁም ፡ በም. ፬ ፡ ፬፤—፲፤ና ፡ በቊላ. ፩ ፡ ፲፰ ፡ ፳፬ ፤ ፪ ፡ ፲፱ ፡ ላይ ፡ የጳውሎስን ፡ ሌላ ፡ ታላቅ ፡ ትምህርት ፡ እናገኛለን ። በ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፲፪—፴ ፡ ላይ ፡ ሐዋርያው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አካል ፡ ስለ ፡ መሆንዋ ፡ ምእመናንም ፡ አባሎች ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፡ ይናገራል ፤ እኛም ፡ በዚህ ፡ ትርጓሜአችን ፡ በመግቢያው ፡ ከፍል ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ጠቅሰነዋል ። (ገጽ ፡ ፬ ።) አሁን ፡ ግን ፡ ትምህርቱ ፡ ሌላ ፡ ነው ። አሁን ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ፡ አካልና ፡ ስለ ፡ አባሎች ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ራስና ፡ ስለ ፡ አካሉ ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ ራስ ፡ ነው ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አካል ፡ ናት ። ክርስቶስ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ግንኙነት ፡ የሰው ፡ ራስ ፡ ከአካሉ ፡ ጋር ፡ የሰውም ፡ አካል ፡ ከራሱ ፡ ጋር ፡ እንዳለው ፡ ግንኙነት ፡ ያለ ፡ ነው ። የሰው ፡ አካል ፡ የሰው ፡ ራስ ፡ መሙያ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስ ፡ መሙያ ፡ («ሙላቱ») ናት ። ያለ ፡ ራስ ፡ አካሉ ፡ ጐደሎ ፡ ነው ፡ ያለ ፡ አካልም ፡ ራስ ፡ ጐደሎ ፡ ነው ። ራስ ፡ አልባ ፡ የሆነ ፡ አካል ፡ ገዥና ፡ መሪ ፡ እንደሌለውና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከንቱ ፡ እንደ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ ያላት ፡ ከንቱ ፡ ፍጥረት ፡ ናት ። አካል ፡ አልባ ፡ የሆነ ፡ ራስ ፡ ደግሞ ፡ ያሰበውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውል ፡ እንደማይችል ፡ እንዲሁም ፡ ክርስቶስ ፡ ያለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዓለም ፡ የሚሆነውን ፡ ታላቅ ፡ አሳቡንና ፡ ዕቅዱን ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም ። ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰጠው ፡ መብ ትና ፡ እደራ ፡ ምንኛ ፡ ታላቅ ፡ ነው!

አንባቢ ፡ ሆይ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ አሳብ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ አስፈላጊው ፡ ናት ። እንተ ፡ ለክርስቶስ ፡ አስፈላጊው ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ ነው ። አስብበት !

48. ቊላ. ፩ ፡ ፲፰ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ሐዋርያው ፡ ጠቅላይና ፡ መጠቅለያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ አካሉም ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይናገራል ።

እስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ክፋትና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማዳን ፡ ይና ገራል ። (ቊ. ፩—፲ ።) ሰው ፡ በበደሉና ፡ በኃጢአቱ ፡ ሞቶ ፡ ነበር ፡ የቊ ጣም ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በምሕረቱና ፡ በጸጋው ፡ እንዲያው ፡ በክርስቶስ ፡ አዳነው ።

ሰው ፡ የሚድን ፡ በክርስቶስ ፡ ሥራ ፡ በማመን ፡ ስለሆነ ፡ በአይሁ ድና ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ መለያያ ፡ ተወግዶአል ፡ ሁለቱም ፡ ማኅበሮች ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነዋል ። ይህችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ ሲሄድ ፡ የሚያ ድግን ፡ ሕንጻ ፡ መስላ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኖርባት ፡ መቅደስ ፡ እስከምትሆን ፡ ድረስ ፡ በምእመናንዋ ፡ ትታነጻለች ። (ቊ. ፲፩—፳፪ ።)

ቊ. ፩ — ፲ ።

ወደ ፡ መዳን ፡ ምልዓት ፡ ያደረሰን ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ።

፩ ፤ ፪፤ እናንተም ፡ በበደላችሁና ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ሙታን ፡ ነበራችሁ ፤ በእነርሱም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳለው ፡ ኑሮ ፡ በማይታዘዙትም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ እንደሚሠራው ፡ መንፈስ ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ አስቃ

፫ ፤ ፈቃድ ፡ ቀድሞ ፡ ተመላለሰባችሁባቸው ። በእነዚህም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ደግሞ ፡ የሥጋችንንና ፡ የልቡናችንን ፡ ፈቃድ ፡ እያደረግን ፡ በሥጋችን ፡ ምኞት ፡ ቀድሞ ፡ እንኖር ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ ደግሞ ፡ ከፍ

፬ ፤ ጥረታችን ፡ የቊጣ ፡ ልጆች ፡ ነበርን ። ነገር ፡ ግን ፡ እግ

፭ ፤ ዚአብሔር ፡ በምሕረቱ ፡ ባለ ፡ ጠጋ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከወ ደደን ፡ ከትልቅ ፡ ፍቅሩ ፡ የተነሣ ፡ በበደላችን ፡ ሙታን ፡ እንኳ ፡ በሆንን ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ሕይወት ፡ ሰ

፮ ፤ ፯ ፤ ጠን ፡ በጸጋ ፡ ድናችኋልና ፡ በሚመጡ ፡ ዘመናትም ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ለእኛ ፡ ባለው ፡ ቸርነት ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጠውን ፡ የጸጋውን ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስነሣን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ በሰማ

፰ ፤ ያዊ ፡ ስፍራ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስቀመጠን ። ጸጋው ፡ በእም ነት ፡ አድኖአችኋልና ፤ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡

ነው ፡ እንጂ ፡ ከእናንተ ፡ አይደለም ፤ ማንም ፡ እንዳይመካ ፡
፱ ፤ ፲ ፩ ከሥራ ፡ አይደለም ። እኛ ፡ ፍጥረቱ ፡ ነንና ፤ እንመላለስ
በት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ያዘጋጀውን ፡
መልካሙን ፡ ሥራ ፡ ለማድረግ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡
ተፈጠርን ።

ለክርስቶስ ፡ ያደረገውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእናንተም ፡ እድርጎአል። [1] ክርስቶስ ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እናንተም ፡ ሙታን ፡ ነበራችሁ ። «እን ደምን ፡ ሙታን ፡ ነበርን?» ብትሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየዘነጋችሁ ፡ እንደ ፡ ዘመናዊ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ መንፈስ ፡ ስትመላለሱና ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ በማይታዘዙቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚሠለጥን ፡ እንደ ፡ ሰይጣንም ፡ ፈቃድ ፡ ስትኖሩ ፡ በበደላችሁና ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ሙታን ፡ ነበራችሁ ። ሁላች ንም ፡ እይሁድም ፡ የአሕዛብ ፡ ወገንም ፡ በእነዚህ ፡ በማይታዘዙቱ ፡ መካ ከል ፡ ተገኝተን ፡ የሥጋችንንና ፡ የልቡናችንን ፡ ፈቃድ ፡ ቀድሞ ፡ እየፈ ጸምን ፡ ሥጋውያን ፡ ሆነን ፡ እንኖር ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ ደግሞ ፡ ቍጣ ፡ የሚገባንና ፡ የሚደርስብንም ፡ ሰዎች ፡ ነበርን ። [2] እንደዚህ ፡ ነበ ርን ፡ ያለ ፡ ሕይወት ፡ ያለ ፡ ተስፋም ፡ ነበርን ። ነገር ፡ ግን ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አለ! እግዚአብሔር ፡ በነገሩ ፡ ገባ! የገባውም ፡ እርሱ ፡ በምሕረቱ ፡ ባለ ፡ ጠጋ ፡ ፍቅሩም ፡ ትልቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ገባና ፡ በክርስቶስ ፡ መሆናች ንን ፡ እያየ ፡ እየቈጠረም ፡ ሙታን ፡ ብንሆንም ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ሕይ ወት ፡ ሰጠን ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገውም ፡ በጸጋው ፡ ነው ። በሚመጡ ትም ፡ ዘመናት ፡ ማለት ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ዘመናት ፡ ሁሉ ፡ የጸጋው ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ለእኛ ፡ ባደረገው ፡ ቸርነት ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ አስነሣን ፡ በሰማያዊም ፡ ስፍራ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስቀመጠን ።

ሐዋርያው ፡ «አስቀመጠን» ይልና ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ «ጸጋው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ አድኖአችኋልና ፡» ይላቸዋል ። ይህም ፡ ማዳን ፡ ወይም ፡ ደኅንነት ፡ ፈጽሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ተመክቶ ፡ «ሠርቻለሁና ፡ ይገባኛል ፡ » ሊል ፡ ከቶ ፡ አይችልም ። የማይችልበት ፡ ምክንያት ፡ እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ ዳግመኛ ፡ የተ ፈጠርነው ፡ እግዚአብሔር ፡ «አስቀድሞ» ከተባለ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያዘ ጋጀልንን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ስንሠራው ፡ ልንመካበት ፡ አንችልም ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «እናንተም ።» (ቍ. ፩ ።) እኔ ፡ በጥቅሱ ፡ ላይ ፡ «እ ናንተም» የተባለውን ፡ ቃል ፡ መጨመሬን ፡ ታያላችሁ ። ምክንያቱም ፡ መልእክቱ ፡ በተጻፈበት ፡ በግሪኩ ፡ ቋንቋ ፡ ቃሉ ፡ አለ ። ጳውሎስ ፡ ም. ፩ ፡ ፲፱ ፡ ጀን ፡ ይዞ ፡ «እናንተንም ፡ ሕይወት ፡ ሰጣችሁ፡» ይል ፡ ነበር ፡

1. ኤፌ. ፩ ፡ ፩—፲፪ ። 2. ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፩—፰ ።

ጀመረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሕይወት ፡ መስጠት ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ እንባቢዎቹ ፡ ሙታን ፡ መሆናቸውን ፡ አስቀድመው ፡ እንዲገነዘቡ ፡ ፈልጎ ፡ ዞር ፡ ይልና ፡ ስለ ፡ መሞታቸው ፡ መናገር ፡ ይጀምራል ። «ሕይ ወት ፡ ሰጣችሁ» የሚለውም ፡ ቃል ፡ በቍ. ፩ ፡ ላይ ፡ ይገባል ፡ ሆኖም ፡ ሐዋርያው ፡ በመካከሉ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ እይሁድም ፡ ተናግሮ ፡ ነበርና ፡ በ«ሰጣችሁ ፡» ፋንታ ፡ «ሰጠን ፡» ይላል ።

ለ) «በበደላችሁና ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ሙታን ፡ ነበራችሁ ።» (ቍ. ፩ ።) «እንደምን ፡ ሙታን ፡ ነበሩ?» ቢሉ ፡ ኃጢአት ፡ እኮ ፡ ይገድላል! [3] በሥጋችን ፡ መሞታችን ፡ እይደለም ፡ በሥጋ ፡ ገና ፡ እንኖራለን ፤ እንበ ላለን ፡ እንጠጣለንም ፡ ሥራችንን ፡ እንሠራለን ፡ ቤተ ፡ ሰዎቻችንንም ፡ እንጠብቃለን ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ስናደርግ ፡ ሳለን ፡ የሞትን ፡ ነን ። እግዚአብሔር ፡ እዳምን ፡ «ከዕፀ ፡ በለስ ፡ በበላህ ፡ ቀን ፡ ሞትን ፡ ትሞ ታለህ ፡» አለው ። [4] እዳምም ፡ በላ ፤ ሆኖም ፡ ገና ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በሥጋው ፡ ኖረ ። እንግዲያውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መሠ ረት ፡ የሞተው ፡ ምኑ ፡ ነው? መንፈሳዊ ፡ ክፍሉ ፡ ነዋ! ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ አሁን ፡ ክፍል ፡ የለውም ፡ ዕድል ፡ ፋንታም ፡ የለውም ፤ ምውት ፡ ነው ። [5] እኛም ፡ ሁላችን ፡ እንደዚሁ ፡ በበደላችን ፡ (ማለት ፡ ከሚገባን ፡ መንገድ ፡ በመውጣታችን ፡) በኃጢአታችንም ፡ (ማለት ፡ በዓላማ ፡ ላይ ፡ ደግነን ፡ በመሳታችን ፡) ሙታን ፡ ነበርን ።

ሐ) «የሥጋችንንና ፡ የልቡናችንን ፡ ፈቃድ ፡ እያደረግን ፡» (ቍ. ፫ ።) ስለ ፡ ጸታዊ ፡ ኃጢአት ፡ ብቻ ፡ አናስብ ። በእርግጥ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ኃጢ አት ፡ ይሆናል ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከሥጋችንና ፡ ከልቡናችን ፡ ከዚህ ፡ የሚ በልጥ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይወጣል ። ከሥጋ ፡ የሚመነጨው ፡ በገላ. ፭ ፡ ፲፱—፳፩ ፡ ላይ ፡ ተዘርዝሮአል ፤ ከልቡናችንም ፡ (ከአሳባችንም ፡) መጥፎ ፡ ሥዕል ፡ በየዓይነቱ ፡ ይወጣል ፡ [6] ከልባችንም ፡ ደግሞ ፡ በማር. ፯ ፡ ፳፩ ፡ ላይ ፡ የተ ጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ይመነጫል ። በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ቀድሞ ፡ ክርስቶስን ፡ ከማወቃችን ፡ በፊት ፡ ሁላችን ፡ እንኖር ፡ ነበር ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ሕይወት ፡ አልነበረንም ፤ የሞትን ፡ ነበርን ።

መ) «ከፍጥረታችን ።» (ቍ. ፫ ።) ከፍጥረታችን ፡ ወይም ፡ ከተፈ ጥሮአችን ፡ የሆንን ፡ እናስተውል ። ከተፈጥሮአችን ፡ የቍጣ ፡ ወራሾች ፡ ነን ! እንዴ ፡ ራሱን ፡ መሳይ ፡ የሆነውን ፡ ይወልዳልና ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ከተፈጥሮአችን ፡ የቍጣ ፡ ልጆች ፡ ነን ። ሰው «የምበቃ ፡ ነኝ ፡ እንድም ፡ ስንኳ ፡ አያስፈልገኝም» ብሎ ፡ ለምን ፡ ያስባል? እግዚአብሔር ፡ በነገሩ ፡ በምሕረት ፡ ካልገባልን ፡ እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ በላከው ፡ መድኀን ፡ ካላመንን ፡ ተስፋ ፡ የለንም ። [7]

3. ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፳፫ ፡ ም. ፮ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። 4. ዘፍጥ. ፪ ፡ ፲፯ ።
5. ዮሐ. ፲፫ ፡ ፰ ። ኤፌ. ፬ ፡ ፲፰ ። 6. ሕዝቅ. ፰ ፡ ፮—፲፩ ።

ሠ) «ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ሕይወት ፡ ሰጠን ።» (ቊ. ፭ ።) «ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ሕይወት ፡ የሰጠን ፡ እንደምን ፡ ነው?» ቢሉ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ መዋሃዳችንን ፡ ያስቡ ። ክርስቶስ ፡ የመጣው ፡ ለእኛ ፡ ነው ፡ የሞተውም ፡ ለእኛ ፡ ነው ፡ የተነሣውም ፡ ለእኛ ፡ ነው ። [8] ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገው ፡ በእኛ ፡ ስም ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ «በክርስቶስ» ሆነናል ፡ ለእርሱ ፡ የሆነውም ፡ (የተደረገውም ፡) ሁሉ ፡ ለእኛ ፡ ሆኖአል ፡ (ተደርጎአል ፡) ። እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣው ፡ እኛን ፡ አብሮ ፡ አስነሣን ፡ (ሕይወት ፡ ሰጠን) ፡ አብሮም ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ አስቀመጠን ። (ቊ. ፮ ፡ ፯ ።) እግዚአብሔር ፡ ሲመለከተን ፡ በክርስቶስ ፡ ሆነን ፡ ሁልጊዜ ፡ ያየናል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ክክርስቶስ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆናችንንም ፡ ይቈጥራል ፡ እኛም ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ መቀኘጠር ፡ ያሻናል ። [9]

ረ) «ጸጋው ፡ በእምነት ፡ እድኖአችኋል ።» (ቊ. ፰ ።) ይህም ፡ ማለት ፡ የማዳን ፡ ነገር ፡ በሞላ ፡ እንዲያው ፡ የተሰጠ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ እኛም ፡ ስጦታውን ፡ የምንቀበለው ፡ በእምነት ፡ እጅ ፡ ነው ። [10] ግሡ ፡ በአላፊ ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ የዳንን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የምናገኘውን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ እለመሆኑን ፡ እንረዳለን ። ክርስቶስ ፡ ለማዳን ፡ መጣ ፡ እዳነንም ፡ ስለዚህ ፡ («ከሞትን ፡ በኋላ ፡ ምናልባት ፡ ከኃጢአታችን ፡ እንድናለን ፡» የሚል ፡ አሳብ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ አይገኝምና ፡ «በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስ ፡ በሞተበት ፡ ዕለት ፡ ዳንን ፡» እንበል ፡ እንጂ ፡ «ወደ ፡ ፊት ፡ እንድናለን ፡» እንበል ። «ድኛለሁ!» ለማለት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያዳግተናል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እውነቱ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ አይደለምን? ክርስቶስ ፡ እላዳነምን?

ሰ) «ክሥራ ፡ አይደለም ።..... እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ያዘጋጀውን ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ ለማድረግ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተፈጠርን ።» (ቊ. ፱ ፡ ፲ ።)በሥራ ፡ አልዳንንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተፈጠርን! «ይህስ ፡ እንደምን ፡ ነው?» ቢሉ ፡ እላይ ፡ እንዳየነው ፡ ሁሉ ፡ ደኅንነት ፡ (መዳን ፡) በክርስቶስ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመልን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ የምንቀበለውም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ (ምግባር ፡) በመሥራት ፡ ሳይሆን ፡ ክርስቶስ ፡ ባደረገው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ በማመን ፡ ነው ። [11] በሥራችን ፡ እንዳችን ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ የማንችለበቱ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ (ምግባር ፡) ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ ትሩፋትም ፡ ሳይሆን ፡ ስሁላችን ፡ የተገባ ፡ የታዘዘ ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። [12] በፍጹም ፡ አዲስ ፡ ሰዎች ፡ ሆነን ፡ በክርስቶስ ፡ ተፈጥረናል ፡ አዲስ ፡ የተፈጠርነውም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራ ፡ ነው ፤ ታስቦ

7. ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ። ዮሐ. ፫ ፡ ፴፮ ። 8. ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፭፫—፭፭ ።
9. ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ። 10. ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፬—፳፭ ። ገላ. ፪ ፡ ፲፮ ።
11. ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ። ፪ጢሞ. ፩ ፡ ፱ ። ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ። 12. ሉቃ. ፲፮ ፡ ፯—፲ ።

አል ፡ ተዘጋጅቶአልም ። [13] መልካም ፡ ዛፍ ፡ መልካምን ፡ ፍሬ ፡ እንዲያው ፡ ታፈራለች ፡ ተብሎ ፡ እንደሚታሰበው ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንደምንሠራ ፡ ታስቦአል ። [14] ስለዚህ ፡ በሥራ ፡ ልንመካ ፡ ወይም ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ልንገዛ ፡ አንችልም ። ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ በፍቅሩ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ ካደረገልን ፡ እኛ ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በማድረግ ፡ ደስ ፡ ልናሰኘው ፡ የዘወትር ፡ ዓላማችን ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። [15]

ቊ. ፲፩ — ፳፪ ።

እውጭ ፡ የነበሩት ፡ የእሕዛብ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ጭምር ፡ እንደ ፡ ዳኑና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አባላት ፡ እንደሆኑ ።

፲፩ ፤ ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥጋ ፡ አሕዛብ ፡ የነበራችሁ ፡ በሥጋ ፡ በእጅ ፡ የተገረዙ ፡ በተባሉት ፡ ያልተገረዙ ፡ የተባላችሁ ፡ ይህን ፡ አስቡ ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ክእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ርቃችሁ ፡ ለተስፋውም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንግዶች ፡ ሆናችሁ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ተስፋን ፡ አጥታችሁ ፡ ክእግዚአብሔርም ፡ ተለይታችሁ ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ነበራችሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ ቀድሞ ፡ ርቃችሁ ፡ የነበራችሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፲፬ ፤ ፲፭ ፤ ሆናችሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ቀርባችኋል ። እርሱ ፡ ሰላማችን ፡ ነውና ፤ ሁለቱን ፡ ያዋሐደ ፡ በአዋጅ ፡ የተነገሩትንም ፡ የትእዛዛትን ፡ ሕግ ፡ ሽሮ ፡ በመካከል ፡ ያለውን ፡ የጥል ፡ ግድግዳ ፡ በሥጋው ፡ ያፈረሰ ፤ ይህም ፡ ከሁለታቸው ፡ አንድን ፡ አዲስን ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ይፈጥር ፡ ፲፮ ፤ ዘንድ ፡ ሰላምንም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ጥልንም ፡ በመስቀሉ ፡ ገድሎ ፡ በእርሱ ፡ ሁለታቸውን ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ክእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ያስታርቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። መጥቶም ፡ ርቃችሁ ፡ ለነበራችሁ ፡ ለእናንተ ፡ ሰላምን ፡ ቀር ፲፯ ፤ ፲፰ ፤ በው ፡ ለነበሩትም ፡ ሰላምን ፡ ሰበከ ፤ በእርሱ ፡ ሥራ ፡ ሁላችን ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ መግባት ፡ አለንና ። እንግዲያስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ክቅዱሳን ፡ ጋር ፡ ባለ ፡ አገሮችና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ፡ እንግዶችና ፡ መጻተኞች ፡ አይደላችሁም ። ፳ ፤ በሐዋርያትና ፡ በነቢያት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ታንጻችኋል ፡ የማዕዘኑም ፡ ራስ ፡ ድንጋይ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፤ ፳፩ ፤

13. ቈላ. ፩ ፡ ፲ ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። 14. ማቴ. ፳፭ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ። ገላ. ፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።
15. ፩ተሰ. ፬ ፡ ፩ ።

ፍ፩ ፤ በእርሱም ፣ እያንዳንዱ ፣ ሕንጻ ፣ ሁሉ ፣ እየተጋጠመ ፣ በጌታ ፣ ቅዱስ ፣ ቤተ ፣ መቅደስ ፣ እንዲሆን ፣ ያድጋል ፤
ፍ፪ ፤ በእርሱም ፣ እናንተ ፣ ደግሞ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ መኖሪያ ፣ ለመሆን ፣ በመንፈስ ፣ አብራችሁ ፣ ትታነጻላችሁ ።

«ስለዚህ» ፤ ማለት ፣ ከቍ. ፩ ፣ አንሥቶ ፣ እስከ ፣ ቍ. ፲ ፣ ድረስ ፣ የተጻፈውን ፣ ነገር ፣ ከሆነ ፣ ስለዚህ ፣ ምልክት ፣ በሥጋችሁ ፣ የላችሁምና ፣ በግልጥና ፣ በሥጋ ፣ መገረዝ ፣ በተገረዙቱ ፣ ዘንድ ፣ «ያልተገረዙ ፣» ተብላችሁ ፣ የምትናቁ ፣ አሕዛብ ፣ ሆይ ፣ ቀድሞ ፣ የነበራችሁትንና ፣ ዛሬ ፣ የሆናችሁትን ፣ አስቡ ። [16] ቀድሞ ፣ ክርስቶስ ፣ ከመምጣቱ ፣ በፊት ፣ በእስራኤል ፣ ነገር ፣ መብት ፣ የሌላችሁ ፣ ባዕዳን ፣ ነበራችሁ ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ የመሢህ ፣ ተስፋ ፣ በተሰጠበቱ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ ውስጥ ፣ እድል ፣ ፈንታ ፣ የሌላችሁ ፣ ነበራችሁ ፣ «ወደ ፣ ፊት ፣ ይሻለናል ፣» የሚል ፣ ተስፋ ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ አጣችሁ ፣ እውነተኛ ፣ አምላክ ፣ የሆነውንም ፣ እግዚአብሔርን ፣ አላወቃችሁትም ። ይህም ፣ ሁሉ ፣ የሆነባችሁ ፣ ያለ ፣ ክርስቶስ ፣ ስለ ፣ ነበራችሁ ፣ ነው ። [17]

አሁን ፣ ግን ፣ ዛሬ ፣ «በክርስቶስ ፣» ከመሆናችሁ ፣ የተነሣ ፣ ሁሉም ፣ ተለወጠ ። ከእግዚአብሔር ፣ ርቃችሁ ፣ የነበራችሁ ፣ በክርስቶስ ፣ ደም ፣ ቀርባችኋል ። ይህም ፣ የሆነ ፣ ክርስቶስ ፣ ሰላማችን ፣ በመሆኑ ፣ ነው ። እርሱ ፣ የሰላም ፣ አለቃ ፣ ሆኖ ፣ በሰውና ፣ በእግዚአብሔር ፣ በሰውና ፣ በሰውም ፣ ማለት ፣ በአይሁድና ፣ በአሕዛብ ፣ መካከል ፣ ሰላምን ፣ አድርጎአል ። [18]

ክርስቶስ ፣ ሥጋውን ፣ መሥዋዕት ፣ አድርጎ ፣ በመስቀል ፣ ላይ ፣ በማቅረብ ፣ እርሱ ፣ በአይሁድና ፣ በአሕዛብ ፣ መካከል ፣ መለያያ ፣ የሆነውን ፣ የሙሴን ፣ ሕግ ፣ ሽሮ ፣ በመካከላቸው ፣ የነበረውን ፣ ጥል ፣ አጠፋ ። ይህንም ፣ ያደረገው ፣ ሰላምን ፣ ለማድረግና ፣ ሁለቱን ፣ ወገን ፣ በአንድ ፣ አካል ፣ በአንድ ፣ ማኅበር ፣ ማለት ፣ በቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ጋር ፣ ለማስታረቅና ፣ ፍጥረቱ ፣ ፈጽሞ ፣ ልዩ ፣ የሆነውን ፣ አይሁድም ፣ አይባል ፣ አሕዛብ ፣ አንድ ፣ አዲስን ፣ ሰው ፣ በራሱ ፣ «በክርስቶስ» ፣ ለመፍጠር ፣ ነው ። [19] ይህንም ፣ አድርጎ ፣ ሲያበቃ ፣ መግባት ፣ በክርስቶስ ፣ ለሁሉም ፣ ተገኝቶአልና ፣ ራሱ ፣ መጣ ፣ በመንፈስ ፣ ቅዱስና ፣ በሐዋርያትም ፣ መጣና ፣ ለሁሉም ፣ ሰላምን ፣ አወጀ ። [20]

እንግዲያውስ ፣ ርቀው ፣ የነበሩቱ ፣ አሕዛብ ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ጀኖ ፣ ማዕረግ ፣ ዜጎች ፣ እንኳ ፣ ሳይሆኑ ፣ አሁን ፣ በአንድ ፣ አገር ፣ መብት ፣ ሁሉ ፣ አብረው ፣ የሚካፈሉ ፣ ባልንጀራ ፣ ሕዝብ ፣ ሆነዋል ፤ የአንድም ፣

16. ሮሜ ፣ ፪ ፣ ፳፭ ፣ ፳፱ ። 17. ዘፍጥ. ፲፯ ፣ ፲፰ ፣ ፲፯ ፣ ፩—፲፱ ። የሐዋ. ፲፯ ፣ ፳፪—፴፩ ። ገላ. ፮ ፣ ፳ ። 18. ቈላ. ፩ ፣ ፳፩ ፣ ፳፪ ። ሉቃ. ፪ ፣ ፲፬ ። ኢሳ. ፱ ፣ ፮ ። ፮ ። ዘካ. ፱ ፣ ፲ ። 19. ም. ፩ ፣ ፳፫ ፣ ፳፮ ። ቈላ. ፩ ፣ ፳፪ ። ፪ቆሮ. ፭ ፣ ፲፯ ። 20. ዮሐ. ፳ ፣ ፲፱ ፣ ፳፭ ፣ ፳፯ ። የሐዋ. ፲ ፣ ፴፯ ። ፪ተሰ. ፫ ፣ ፲፮ ። ኢሳ. ፶፯ ፣ ፲፱ ።

አገር ፣ ሰዎች ፣ ብቻ ፣ ሳይሆኑ ፣ የአንድ ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ ሰዎች ፣ ናቸው ፣ እርሱም ፣ የእግዚአብሔር ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ ሰዎች ፣ ናቸው ። ቤተ ፣ ሰዎችም ፣ ብቻ ፣ ሳይሆኑ ፣ እንዲያውም ፣ ራሱን ፣ ቤቱን ፣ ናቸው! [21] ሕንጻ ፣ ሁሉ ፣ በመታነጽ ፣ ላይ ፣ ሲሆን ፣ ሳለ ፣ ድንጋይ ፣ በድንጋይ ፣ ላይ ፣ እየተጨመረ ፣ ሲሄድ ፣ የቤቱ ፣ ቁመት ፣ እንደሚያድግ ፣ ሁሉ ፣ እንዲሁም ፣ በሐዋርያትና ፣ በአዲስ ፣ ኪዳን ፣ ነቢያት ፣ መሠረት ፣ ትምህርት ፣ በተጀመረችውና ፣ ቅርጽዋንም ፣ ሁሉ ፣ በክርስቶስ ፣ በተቀረጸችው ፣ (በተወሰነችው) አንዲትዋ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ውስጥ ፣ ምእመናን ፣ ሁሉ ፣ አይሁድም ፣ አሕዛብም ፣ አብረው ፣ ሆነው ፣ አንድ ፣ ድንጎች ፣ ይጨመራሉ ። አንዱ ፣ በአንዱ ፣ ላይ ፣ ሲጨመር ፣ ቤቱ ፣ እያደገ ፣ ይሄድና ፣ በፍጻሜ ፣ ላይ ፣ እግዚአብሔር ፣ በመንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ የሚኖርበት ፣ መቅደስ ፣ ይሆናል ። [22]

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «በክርስቶስ ፣ ደም ፣ ቀርባችኋል ።» (ቍ. ፲፫ ።) ከእግዚአብሔር ፣ የሚያርቀን ፣ ኃጢአት ፣ ነው ። [23] ኃጢአትን ፣ የሚያስወግድ ፣ የክርስቶስ ፣ ደም ፣ ነው ። [24] ስለዚህ ፣ የሚያቀርበን ፣ የክርስቶስ ፣ ደም ፣ መሆኑን ፣ እንገነዘባለን ።

ለ) «እርሱ ፣ ሰላማችን ፣ ነው ።» (ቍ. ፲፬ ፣ ፲፭ ።) ሁለት ፣ ሰዎች ፣ ሲጣሉ ፣ አስታራቂ ፣ በመካከላቸው ፣ ቢገባ ፣ ያ ፣ መካከለኛ ፣ አስታራቂ ፣ ሰላማቸው ፣ ነው ። የእኛ ፣ ሰላም ፣ በእኛና ፣ በእግዚአብሔር ፣ መካከል ፣ የገባ ፣ በእኛና ፣ በጠላቶቻችን ፣ ሁሉ ፣ መካከል ፣ የሚገባ ፣ ዕርቅም ፣ የሚያደርግ ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ። አንባቢ ፣ ሆይ ፣ የእርስዎ ፣ ሰላም ፣ ክርስቶስ ፣ ነውን ፣ ወይስ ፣ በሌላ ፣ ይታመናሉ? በሌላ ፣ የታመኑ ፣ እንደሆነ ፣ እኮ ፣ አይሆንልዎትም!

ሐ) «በአዋጅ ፣ የተነገሩትን ፣ የትእዛዛትን ፣ ሕግ ፣ ሽሮ ።» (ቍ. ፲፭ ፣ ፲፮ ።) «እንደምን ፣ ሻረው?» ቢሉ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ማቅረቢያ ፣ ከመሆኑ ፣ ሻረው ፣ አስወገደውም ። ክርስቶስ ፣ ከመምጣቱ ፣ በፊት ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ማቅረቢያው ፣ ኦሪት ፣ ወይም ፣ ሕግ ፣ ነበረ ። «በአዋጅ ፣ የተነገረው ፣ ሕግ ፣» ይኸው ፣ ነው ። [25] ክርስቶስ ፣ ግን ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ማቅረቢያው ፣ ሌላ ፣ እርሱም ፣ ራሱ ፣ ክርስቶስ ፣ ሆነ ። [26] ሁለተኛውን ፣ ሊያጸና ፣ የፊተኛውን ፣ ሻረ ።

መ) «በመካከል ፣ ያለውን ፣ የጥል ፣ ግድግዳ ፣ በሥጋው ፣ አፈረሰ ።» (ቍ. ፲፬ ፣ ፲፭ ።) ጳውሎስ ፣ በቤተ ፣ መቅደስ ፣ ውስጥ ፣ የነበረውን ፣ የመሰያያ ፣ ግድግዳ ፣ የሚያስብ ፣ ይመስላል ። በጥንቱ ፣ ቤተ ፣ መቅደስ ፣ ውስጥ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ አዳራሾች ፣ ነበሩ ፣ እያንዳንዱም ፣ ከፊተኛው ፣ ይልቅ ፣ ጥቂት ፣ ከፍ ፣ ይል ፣ ነበር ። ሰው ፣ ሲገባ ፣ መጀመሪያው ፣ አዳ

21. ዕብራ. ፫ ፣ ፮ ። 22. ም ፣ ፫ ፣ ፭ ፣ ፮ ። ም. ፮ ፣ ፲፭ ። ፩ኤጥ. ፪ ፣ ፩—፮ ። መዝ. ፩፻፲፯ ፣ ፳፪ ። የሐዋ. ፬ ፣ ፲፩ ። 23. ኢሳ. ፶፱ ፣ ፩ ፣ ፪ ። 24. ዮሐ. ፩ ፣ ፳፱ ። ኤፌ. ፩ ፣ ፯ ። ዕብራ. ፱ ፣ ፲፫ ፣ ፲፩ ፣ ፳፯ ። 25. ዘጸአ. ም. ፳ ። ዘዳግ. ፮ ፣ ፩—፫ ። 26. ዮሐ. ፲፱ ፣ ፯ ። ገላ. ፫ ፣ ፳፫—፳፭ ። ዕብራ. ፲ ፣ ፩—፲ ።

ራሽ ፡ «የአሕዛብ ፡ አዳራሽ» ነበረ ፤ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ «የቤቶች ፡ አዳራሽ» ነበረ ፤ ቀጥሎም ፡ «የእስራኤላውያን ፡ አዳራሽ» ፡ ከእርሱም ፡ ወዲያ ፡ «የካህናት ፡ አዳራሽ» ፤ በመጨረሻም ፡ ላይ ፡ እግዚ አብሔር ፡ የሚገኝበት ፡ «መቅደስ» ነበረ ።

አሕዛብ ፡ ወደ ፡ «አሕዛብ ፡ አዳራሽ» ሊገቡ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ በግሪክና ፡ በሮማይስጥ ፡ ተጽፎ ፡ «ከእስራኤል ፡ ያልሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቅጥርና ፡ ግድግዳ ፡ ቢያልፍ ፡ ሞት ፡ ይሞ ታል ፡» የሚል ፡ ማስታወሻ ፡ የተለጠፈበት ፡ አንድ ፡ ግድግዳ ፡ ነበረ ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ከአሕዛብ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲገባ ፡ አልተፈቀደ ትም ። (አይሁድ ፡ ጳውሎስን ፡ አብዝተው ፡ የጠሉት ፡ የኤፌሶኑን ፡ ጥሮ ፊሞስን ፡ ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ እንዳስገባው ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ነው ። (የሐዋ. ፳፩ ፡ ፳፱ ።)

ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በአይሁድና ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ጥል ፡ በማጥፋት ፡ ግድግዳውን ፡ አፈረሰ ። «እንደምን ፡ አፈረሰው?» ቢሉ ፡ በሥጋው ፡ አፈረሰው ። ማለት ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ በመሞት ፡ ዓለምን ፡ ስላዳነ ፡ በእርሱ ፡ በበሩ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ይድ ናል ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ የሚከለክል ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ የለም ። [28]

ሠ) «ጥልን ፡ በመስቀሉ ፡ ገድሎ ።» (ቊ. ፲፮ ።) «በአይሁድና ፡ በአ ሕዛብ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ጥል ፡ እንደምን ፡ ገደለ?» ቢሉ ፡ ሰውን ፡ የሚያገናኝ ፡ የክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ነው ። መዳንን ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ መስቀል ፡ የሚመጡ ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡ ይገናኛሉ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይ ሁድ ፡ አሕዛብ ፡ ጥቁር ፡ ነጭ ፡ ጌታ ፡ ሠራተኛ ፡ የለም ፤ ጥል ፡ ተወገደ ፡ እነርሱም ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ጥልን ፡ በመስቀሉ ፡ የገደለው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

ረ) «በእርሱ ፡ ሥራ ፡ ሁላችን ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ መግ ባት ፡ አለን ።» (ቊ. ፲፰ ።) በዚህ ፡ ቊጥር ፡ ላይ ፡ ፫ቱ ፡ ሥላሴን ፡ እናገኛ ለን ። በወልድ ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ ሁላችን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አማ ካይነት ፡ ወደ ፡ አብ ፡ እንገባለን ፡ ይላል ። ማንኛችንም ፡ ብንሆን ፡ ሁላ ችን ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ መግባት ፡ አለን ። የምንቀርበው ፡ «ስለ ፡ ክር ስቶስ» ነው ፤ ክርስቶስንም ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ ስንቀርብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከልካይ ፡ ሳይሆን ፡ አቅራቢ ፡ ሆኖ ፡ እጃችንን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ያገባናል ። [29] እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንድንቀርብ ፡ የመ ሰነልን ፡ መንገድ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

ይህም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መጽናናትን ፡ ይሰጠናል ! ተመልከቱ ፡ አባ ካችሁ ፤ በወደድንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የትም ፡ ቦታ ፡ ብንገኝ ፡ በማንኛውም ፡

27. ገላ. ፫ ፡ ፳፰ ። ቈላ. ፫ ፡ ፲፩ ። 28. ዮሐ. ፲ ፡ ፮—፱ ። 29. ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፲፫ ።

ሰዓት ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ውድ ፡ አባታችን ፡ ዘንድ ፡ በድፍረት ፡ ልንቀርብና ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ረድኤትን ፡ ልናገኝ ፡ እንችላለን! (፩ጢ. ፪ ፡ ፲፮ ።)

ሰ) «ታንጻችኋል ፡ ... ትታነጻላችሁ ።» (ቊ. ፳—፳፪ ።) ሐዋርያው ፡ አሁን ፡ አሳቡን ፡ ለውጦ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ መናገርን ፡ ትቶ ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ መናገር ፡ ይጀምራል ። በክርስቶስ ፡ ያመኑቱ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ተገጣጠሙ ፡ ያስባቸዋል ። ቤቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ መሠረት ፡ የጣሉት ፡ ሐዋርያትና ፡ አብረዋቸው ፡ የሠሩት ፡ ነቢያት ፡ ናቸው ፤ [30] ድን ጋዮቹ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገጣጠሙት ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ፡ የቤቱ ንም ፡ ቅርጽ ፡ ሁሉ ፡ የሚገዛው ፡ የማዕዘኑ ፡ ራስ ፡ ድንጋይ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ቤቱ ፡ ዛሬ ፡ በመታነጽ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ መታነጽ ፡ ግን ፡ ሲፈጸም ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስ ፡ ይሆናል ። [31] ሁሉም ፡ «በእርሱ» ፡ በክርስቶስ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በዚህች ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ የሚጋጠሙ ፡ «በክርስቶስ ፡» የሆኑቱ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። (ቊ. ፳፩ ፡ ፳፪ ።) በክርስቶስ ፡ የሆንንም ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አብረን ፡ እንታነጻለን ። [32] ስለዚህ ፡ ድሮ ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡ በታነጸው ፡ ግዙፋዊ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፋንታ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተጋጠምን ፡ እኛ ፡ እዲስና ፡ እውነተኛ ፡ መቅደስ ፡ ለመሆን ፡ እንበቃለን።

እንባቢ ፡ ሆይ ፡ እርስዎ ፡ በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ድንጋይ ፡ ነዎትን? በዚህ ፡ መንፈሳዊ ፡ «ቤት» ቦታዎን ፡ ይዘዋልን? በዙሪያዎ ፡ መቸም ፡ በየ ዓይነቱ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ድንጎች ፡ አሉ ። ድንጎቹ ፡ በየዓይነቱ ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ናቸውና ፡ ይውደዱአ ቸው! እርስዎም ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ መሆንዎን ፡ እያሰቡ ፡ ያለዎትን ፡ ታላቅ ፡ መብትና ፡ እንደዚሁም ፡ ያለበዎትን ፡ ታላቅ ፡ ኃላፊነት ፡ ያስታውሱ ። በሚሠሩትም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ቤቱን ፡ ያንጹ ፡ እንጂ ፡ እንዳያፈርሱት ፡ ይጠ ንቀቁ ! [33]

30. የሐዋ. ፲፭ ፡ ፳፯ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ፡ ፴፪ ። ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፳፰ ። ኤፌ. ፫ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። 31. ፩ቆሮ. ፫ ፡ ፲ ። መዝ. ፩፻፲፯ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ፩ጴጥ. ፪ ፡ ፮—፰ ። ፩ጢሞ. ፫ ፡ ፲፭ ። 32. ፩ቆሮ. ፫ ፡ ፲፮ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ። ፪ቆሮ. ፮ ፡ ፲፮ ። ራእይ ፡ ፳፩ ፡ ፩—፲፱ ። 33. ፩ቆሮ. ፫ ፡ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ሥስት ።

ሐዋርያው ፡ ለአሕዛብ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ርቀው ፡ የነበ
ሩት ፡ እንዴት ፡ እደቀረቡና ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ባለ ፡ አገሮች ፡
የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ሰዎችና ፡ የአንዱ ፡ ሕንጻ ፡ ድንጋች ፡ መሆና
ቸውን ፡ በልቡ ፡ ሲያሰላስል ፡ ሊጸልይላቸው ፡ ይመኛል ። መጸለይም ፡
ይጀምራል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቁ. ፩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ሌላ ፡ አሳብ ፡
ያቋርጠውና ፡ እስከ ፡ ቁ. ፲፬ ፡ ድረስ ፡ ጸሎቱን ፡ ያቈያል ። አሳቡ ፡ «እኔ ፡
ስለ ፡ እነርሱ ፡ ሰምቻለሁ ። (፩ ፡ ፲፩) ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ሰምተዋልን?
እረ ፡ ሳይሰሙ ፡ የቀሩ ፡ አይመስለኝም ፡» የሚል ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ስለ ፡
ሐዋርያነቱ ፡ ጥቂት ፡ ይንገራቸው ። እንግዲያውስ ፡ ከቁ. ፪—፲፫ ፡ ስለ ፡
ሐዋርያነቱ ፡ ሲናገር ፡ ከቁ. ፲፬—ፍ፩ ፡ ጸሎቱን ፡ ይጸልያል ።

ቁ. ፩ — ፲፫ ።

**ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ ለጳውሎስ ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ።**

፩፤ ስለዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ ሆናችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የክርስ
ቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስር ፡ የሆንሁ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ለእግዚአ

፪፤ ብሔር ፡ እንበረከካለሁ ። ለእናንተ ፡ ስለ ፡ ተሰጠኝ ፡ ስለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ መጋቢነት ፡ በእርግጥ ፡ ሰምታችኋል ፤

፫፤ አስቀድሜ ፡ በአጭሩ ፡ እንደ ፡ ጻፍሁ ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡

፬፤ በገለጣ ፡ አስታወቀኝ ፤ ይህንም ፡ ስታነቡ ፡ የክርስቶስን ፡ ምሥ
ጢር ፡ እንዴት ፡ እንደማስተውል ፡ ልትመለከቱ ፡ ትችላላችሁ ፤

፭፤፮፤ ይህም ፡ አሕዛብ ፡ አብረው ፡ እንዲወርሱ ፡ በእንድ ፡ አካ
ልም ፡ አብረው ፡ እንዲሆኑ ፡ በወንጌልም ፡ ስብከት ፡ በክር
ስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በሆነ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አብረው ፡ እንዲ
ካፈሉ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሐዋርያትና ፡ ለነቢያት ፡ በመንፈስ ፡
አሁን ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ በሌሎቹ ፡ ትውልዶች ፡ ዘንድ ፡

፯፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ አልታወቀም ። እንደ ፡ ኃይሉ ፡ ሥራ ፡
እንደ ፡ ተሰጠኝም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስጦታ ፡

፰፤፱፤ መጠን ፡ የወንጌል ፡ አገልጋይ ፡ ሆንሁለት ። ፍለጋ ፡ የሌለ
ውን ፡ የክርስቶስን ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ለአሕዛብ ፡ እሰብክ ፡
ዘንድ ፡ ሁሉንም ፡ በፈጠረው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከዘላለም ፡
የተሰወረው ፡ የምሥጢር ፡ ሥርዓት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ለሁሉ ፡ እገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ጸጋ ፡ ከቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡

፲፤ ይልቅ ፡ ለማንስ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጠ ፤ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ አሁን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በኩል ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አለቆችና ፡

፲፩፤ ሥልጣናት ፡ ትታወቅ ፡ ዘንድ ፤ ይህም ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ በጌታችን ፡ የፈጸመው ፡ የዘላለም ፡ አሳብ ፡ ነበረ ፡

፲፪፤ በእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ እምነታችን ፡ በኩል ፡ ድፍረትና ፡

፲፫፤ የመታመን ፡ መግባት ፡ በእርሱ ፡ አለን ። ስለዚህ ፡ ስለ ፡
እናንተ ፡ ስላለ ፡ መከራዬ ፡ እንዳትታክቱ ፡ እለምናችኋለሁ ፡
ክብራችሁ ፡ ነውና ።

ሐዋርያው ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመው ፡ ታላቅ ፡ ለውጥ ፡
ነግሮአቸዋልና ፡ ሊጸልይላቸው ፡ ይወዳል ። «ስለዚህ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ስለ ፡
አሕዛብ ፡ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስር ፡ የሆንሁኝ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ....»
ይልና ፡ አሳብ ፡ አቋርጦት ፡ ናሮ ፡ ይቆማል ። «ለእግዚአብሔር ፡ እንበረ
ከካለሁ» የሚሉ ፡ ቃላት ፡ በግሪክ ፡ ላይ ፡ የሉም ፤ በአማርኛ ፡ ትርጉማችን ፡
ላይ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ከቁ. ፲፬ ፡ ላይ ፡ ተወስዶዋል ። «ለመሆኑ ፡ የአሕዛብ ፡
ሐዋርያ ፡ መሆኔንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ አድል ፡ ዘንድ ፡ መጋቢ
ነት ፡ እንደ ፡ ተሰጠኝ ፡ ሰምታችሁ ፡ የለምን?» ይላቸዋል ። «በም. ፩ ፡
፱ ፡ ፲ ፡ ላይ ፡ በአጭሩ ፡ አስታውቄአችኋለሁ ። ይህም ፡ የማድሰው ፡ ምሥ
ጢር ፡ ከራሴ ፡ ሳይሆን ፡ በልዩ ፡ ገለጣ ፡ ተገለጠልኝ ።[1] በልዩ ፡ ገለጣ ፡ መሆ
ኑን ፡ የሚያስረዳችሁም ፡ ድሮ ፡ አይሁዳዊና ፡ ፈሪሳዊም ፡ በነበርሁኝ ፡
ጊዜ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አሳብ ፡ በፍጹም ፡ ባልተቀበልሁኝም ፡ ነበ
ርና ፡ ነው ። ይህም ፡ ምሥጢር ፡ በወንጌል ፡ ተገለጠ ። ምሥጢሩ ፡ ማለት ፡
አሕዛብ ፡ ሰማያዊ ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ ርስት ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡
እንዲወርሱ ፡[2] ተለይተው ፡ ሳይሆንም ፡ ተዋሕደው ፡ በእንድ ፡ አካል ፡
አብረው ፡ እንዲሆኑ ፡[3] በክርስቶስ ፡ በሆነው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አብረው ፡
ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ እንዲካፈሉ ፡[4] በሌሎች ፡ ትውልዶች ፡ ዘንድ ፡ ተጠቅሶ ፡
በከፊልና ፡ በጨረፍታም ፡ ቢታወቅ ፡ እንኳ ፡ አሁን ፡ ለሐዋርያትና ፡ ለነ
ቢያት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በተገለጠ ፡ መጠን ፡ በፍጽም ፡ አልታወቀም ፡
ነበር ።[5] የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ ሠራ ፤ እርሱ ፡ በጸጋው ፡
ጠራኝ ፤ እኔም ፡ የወንጌል ፡ አገልጋይ ፡ ሆንሁለት ።[6] ሥራዬም ፡ ሥራዬስ ፡ ክር
ስቶስንና ፡ በእርሱ ፡ ያለውንም ፡ የማይመረመርን ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ለአሕ
ዛብ ፡ መስበክና ፡ በፈጣሪ ፡ አምላክ ፡ ከዘላለም ፡ ጀምሮ ፡ የተሰወርን ፡
የምሥጢር ፡ አሳብ ፡ (ዕቅድ ፡ ም· ፩ ፡ ፭—፲) ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዓለም ፡

1. ገላ. ፩፡፲፯ ። 2. ገላ ፡ ፫ ፡ ፳፱ ፤ ፬ ፡ ፮ ። ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።
3. ኤፌ.፪፡፲፯ ። 4. ፪ጢሞ.፩፡፩ ። 5. የሐዋ. ፲፩፡ ፲፩—፲፰ ። ሮሜ ፡ ፲፩፡ ፳—፲፪ ።
6. ሮሜ ፡ ፲፩፡ ፲፩፡ ፲፯ ። ኤፌ. ፲፱ ፤ ፫፡ ፰ ። ቈላ ፡ ፩ ፡ ፳፫—፳፱ ። ፩ጢሞ.፩ ፡ ፲፪—፲፯ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ መግለጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሥራ ፡ ቀድሞ ፡ እሳዳጅ ፡ በመ
ሆኔ ፡ ከቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ለማንስ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጥቶአል! የእግዚ
አብሔር ፡ አሳብ ፡ ከዘላለም ፡ ጀምሮ ፡ የተሰወረበቱ ፡ በየዓይነቱ ፡ የሆኑ ፡
የጥበቡ ፡ ቀለማት ፡ በሰማይ ፡ ለሚገኙት ፡ መላእክትና ፡ ሥልጣናት ፡
እንዲታወቁ ፡ ነው ፡ ይህም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ እንዲታወቁ ፡
ነው ። ይህንም ፡ እሳቡን ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ፈጽሞአል ፤ አሁንም ፡
በእርሱ ፡ በማመንና ፡ በእርሱ ፡ በኩል ፡ በመምጣት ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
ወደ ፡ ጠቢብና ፡ ሁሉን ፡ ወደሚችል ፡ አምላክ ፡ በድፍረትና ፡ በመታመን ፡
ልንገባ ፡ እንችላለን ። ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ በደረ
ሰብኝ ፡ መክራ ፡ ምክንያት ፡ ትታክታላችሁ? እረ ፡ ክብራችሁ ፡ ነው!»

አሕዛብ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ ይካፈላሉ ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡
አሳብ ፡ ተፈጽሞአል ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መግበት ፡ አላቸው ፤
ሐዋርያውም ፡ የታሰረው ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ብሎ ፡ ነው ። እረ ፡ ለምን ፡ ይታ
ከታሉ?

ማስገንዘቢያ ። ሀ)«የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስር ፡ የሆንሁ ።» (ቊ. ፩ ።)
ስመሆኑ ፡ የሮማውያን ፡ እስር ፡ አልነበረምን? ነበረ! ቢሆንም ፡ በሐዋር
ያው ፡ አስተያየት ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ። የታሰረው ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡
ማለት ፡ የክርስቶስ ፡ ስለሆነና ፡ ስክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ምስክርነት ፡
ነበረ ። በተጨማሪም ፡ የሮማውያን ፡ እስር ፡ የሆነው ፡ በእግዚአብሔርና ፡
በጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ መታሰሩን ፡ ሲመለከት ፡ ጳው
ሎስ ፡ ራሱን ፡ የኢየሱስ ፡ እስር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያህል ፡ ይቈጥራል ፡ እንጂ ፡
የሮማውያን ፡ እስር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያህል ፡ አይቈጥርም ። እኛስ? የእርሱን ፡
የመሳለሰ ፡ ችግር ፡ ሲያጋጥመን ፡ «የኢየሱስ ፡ እስር ፡ ነኝ ፤ የእግዚአብ
ሔር ፡ እስር ፡ ነኝ ።» ብለን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እጅ ፡ እናይበታለንን?

ሰ) «ስለ ፡ ተሰጠኝ ፡ መጋቢነት ።» (ቊ. ፪ ።) ጳውሎስ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ጸጋ ፡ መጋቢ ፡ ነበረ ። ሥራው ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ ሥራውም ፡ ተሰ
ጥቶታል ። የሚያድለው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ የክርስቶስን ፡ ምሥ
ጢር ፡ ነው ።[7] መጋቢና ፡ በቊ. ፯ ፡ ላይ ፡ እንደሚሰው ፡ ሁሉ ፡ አገልጋ
ይም ፡ የሆነው ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ምርጫ ፡ ሳይሆን ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ጥሪና ፡ ሹመት ፡ ነበረ ።[8] (በግሪኩ ፡ በቊ. ፯ ፡ ላይ ፡ «አገልጋይ ፡
ተደረግሁኝ» ይላል ።) በእኛ ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥጢር ፡ መጋቢዎችና ፡
የወንጌል ፡ አገልጋዮች ፡ በሆንንም ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ይሁን ።
አስቀድመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥሪውንና ፡ መሾሙን ፡ እንስማ ።
ለጥቅም ፡ ከሰማይ ፡ የታየንን ፡ ራእይ ፡ እንቢ ፡ ላንል ፡ ራሳችንንና ፡ የዚ
ህን ፡ ዓለም ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፡ ከደን ፡ ታጥቀን ፡ የምሥጢሩ ፡ መጋቢዎ

7. ፩ቆሮ. ፬ ፡ ፩ ። 8. ገላ. ፩ ፡ ፩—፪ ፡ ፲፭ ። ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፲፭—፲፮ ።

ችና ፡ የወንጌል ፡ አገልጋዮች ፡ ስመሆን ፡ እንነሣ ።[9] ብዙውንም ፡ ለማደል ፡
ከተሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ ብዙ ፡ እንደሚፈልግ ፡ ልብ ፡ እናድርግ ።[10]

ሐ) «ምሥጢር ።» (ቊ. ፫ ፡ ፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ።) «ምስጢሩስ ፡ ምንድር ፡ ነው?»
ቢሉ ፡ ምሥጢሩማ ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። በም. ፭ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡
ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ በም. ፫ና ፡
በቊ. ፲፩ ፡ ላይ ፡ «በክርስቶስ ፡ የፈጸመው ፡ የዘላለም ፡ አሳብ» ይባላል ።
ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፡ የታሰበው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ሐዋርያት ፡
ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተሰወረው ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕቅድ ፡
ነው ። ምሥጢሩ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ እርሱና ፡ በእርሱም ፡ የሚደረገውና ፡
የሚገኘው ፡ ሁሉ ፡ ነው ። በሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈውም ፡
በወንጌል ፡ የተገለጠው ፡ ሁሉ ፡ ነው ። በምሥጢሩ ፡ ውስጥ ፡ ለአሕዛብ ፡
የሚደርስ ፡ ታላቅ ፡ በረከት ፡ ተጠቅልሎአል ፡ በአሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ለሁላ
ችን ፡ የሚሆን ፡ ክብር ፡ ተጠቅልሎአል ፡ በአሳቡም ፡ ውስጥ ፡ የአንዲት ፡
ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መቋቋም ፡ ተጠቅልሎአል ። ምሥጢሩ ፡
ይኸው ፡ ነው ።[11]

መ) «በወንጌልም ።» (ቊ. ፮—፯ ።) ቃሉ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ በመቆሙ ፡
ችግር ፡ ይፈጠራል ። በአማርኛ ፡ ትርጉማችን ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሦስተኛው ፡
ነገር ፡ ስለ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ የሚናገር ፡ ይመስላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡
ብዙዎች ፡ መምህራን ፡ «አይደለም ፤ ስለ ፡ ሦስቱ ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ርስትና ፡
ስለ ፡ አካሉ ፡ ስለ ፡ ተስፋ ፡ ቃልም ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡
ብቻ ፡ አይደለም ፡ የሚናገረው» ይላሉና ፡ እንዲሁም ፡ ይተረጕሙታል ።
እርግጥ ፡ ነው ፡ ፫ቱን ፡ ነገሮች ፡ ያስታወቀንና ፡ ፫ቱን ፡ ነገሮች ፡ የከፈተ
ልን ፡ ፫ቱንም ፡ ነገሮች ፡ ያስቻለልን ፡ ወንጌል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቃሉ ፡
ስለ ፡ ፫ቱ ፡ ነገሮች ፡ ይናገራል ፡ እንላለን ።

ሠ) «ለቅዱሳን ፡ ሐዋርያት .... ተገለጠ ።» (ቊ. ፭—፯ ።) «መቼ ፡
ተገለጠላቸው?» ቢሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተገለጠው ፡ በሐዋ . ም .
፲ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተተረከው ፡ ነው ። ለቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ የተገለጠው ፡
በገላ. ፩ ፡ ፲፯ ፤ ፪ ፡ ፲፩—፲፮ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ነው ።

ረ) «እንደ ፡ ኃይሉ ፡ ሥራ .. የወንጌል ፡ አገልጋይ ፡ ሆንሁለት ።»
(ቊ. ፯ ።) እግዚአብሔር ፡ ጳውሎስን ፡ በጸጋው ፡ ጠራ ፡ በኃይሉም ፡ አስ
ቻለው ። የወንጌል ፡ አገልጋይ ፡ የሆነው ፡ የሠራውም ፡ እንደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ኃይል ፡ መጠን ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ በገዛ ፡ ኃይሉ ፡ አልነበረም ።[12]
እንዲያውም ፡ ጳውሎስ ፡ በሰውነቱ ፡ ደካማ ፡ ነበረ ፡ ንግግሩም ፡ የተናቀ ፡
ነበር ።[13] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለሥራ ፡ የቀጠረው ፡ እግዚአብሔር ፡ በገዛ ፡ ኃይሉ ፡

9. የሐዋ. ፳፮ ፡ ፲፱ ። ግሥ. ፲፯ ፡ ፳፰—፳፯ ። 10. ሉቃ. ፲፪ ፡ ፵፰ ። ፩ቆሮ. ፬ ፡ ፪—፮ ።
11. ቈላ. ፩፡፳፮ ። 12. ቈላ. ፩ ፡ ፳፱ ። 13. ፩ቆሮ. ፪፡፩—፭ ። ፪ቆሮ. ፲ ፡ ፲፡፲ ፡ ፲—፲ ።

ሠራበት ፤ ስለዚያም ፡ ኃይል ፡ ታላቅነት ፡ በም. ፩ ፡ ፲፰—፳፪ ፡ ላይ ፡ አን ብበናል ። እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ሥራ ፡ ሲጠራን ፡ በገዛ ፡ ኃይ ላችን ፡ እንደምንሠራ ፡ አያስብም ። የሚፈልገው ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ በኃ ይሉ ፡ ሊሠራ ፡ ነው ።[14] ደካማነታችንንና ፡ አለመብቃታችንን ፡ ሳንመለ ከት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኃይል ፡ እንመልከት ። ደካማነታችንን ፡ ብንመ ለከትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ታምነን ፡ የወንጌል ፡ ሥራችንን ፡ እንሥራ ።[15]

ሰ) «ፍለጋ ፡ የሌለውን ፡ የክርስቶስ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ለአሕዛብ ፡ እስብክ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ጸጋ ፡ ተሰጠኝ ።» (ቊ. ፰ ፡ ፱ ።) ግሩም! ለእኔ ፡ ተሰ ጥቶአል! የክርስቶስን ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ለማያውቁ ፡ እስብክ ፡ ዘንድ ፡ ምንኛ ፡ ታላቅ ፡ መብት ፡ ነው! ይሁን ፡ እንጂ ፡ የክርስቶስን ፡ ባለ ፡ ጠግ ነት ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ አውቀዋለሁን?

በክርስቶስ ፡ ያለውና ፡ ክክርስቶስ ፡ የምናገኘው ፡ ነገር ፡ እኩ ፡ ጥቂት ፡ አይደለም ። ብዙ ፡ ስው ፡ በእውነቱ ፡ የዓለም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አልተገነዘበም ፤ የማያከብረውም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።[16] በክርስቶስ ፡ ውስጥ ፡ ሀብትና ፡ መዝገብ ፡ ባለ ፡ ጠግነትም ፡ አለ ። ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ቸርነቱና ፡ ስለ ፡ መቻሉ ፡ ስለ ፡ ትዕግሥቱም ፡ ባለ ፡ ጠግ ነት ፡ በሮሜ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ እናነባለን ። በኤፌሶን ፡ መልእክታችን ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ጸጋው ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ስለ ፡ ምሕረቱ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ስለ ፡ ርስት ፡ ክብር ፡ ባለ ፡ ጠግነትና ፡ ስለ ፡ ክብሩም ፡ ባለጠግነት ፡ እና ነባለን ።[17]

ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ዎታል ። ሊንቁት ፡ የሚገባዎት ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ እኩ ። አይመረምሩ ትምን? አይጠቀሙበትምን? ለእርሰዎ ፡ ብሎ ፡ የሠራውንም ፡ ሥራ ፡ እስኪ ፡ ያስቡ ። ለእርሰዎ ፡ ጽድቅንና ፡ በረከትን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በድፍረት ፡ መግባትንም ፡ ሰጥቶአል ። ክርስቶስ ፡ ባለ ፡ ጠጋ ፡ አይ ደለምን? ታዲያስ ፡ ፍለጋ ፡ የሌለውን ፡ የክርስቶስን ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ እር ስዎ ፡ ራስዎ ፡ እያስተዋሉ ፡ ለማያውቁት ፡ አያስታውቁምን?

ሸ) «ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ።» (ቊ. ፲ ።) «በማብራሪያው ፡ ላይ ፡ «የጥበቡ ፡ ቀለማት ፡» የተባለው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው?» ይሉኝ ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ ጳውሎስ ፡ የጻፈው ፡ ቃል ፡ እርሱን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በአማርኛ ፡ ትርጉማችን ፡ «ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ» ተባለ ። መልካም ፡ ነው ፡ ሆኖም ፡ ሐዋርያው ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፍ ፡ «በየቀለማቱ ፡ የሆነ ፡ ጥበብ» ብሎአል ። በቀስተ ፡ ዳመና ፡ እንዳለው ፡ ነገር ፡ ነው ። በቀስተ ፡ ዳመና ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡

14. ኤፌ. ፫ ፡ ፰ ። 15. ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፫—፳፩ ። ፪ቆሮ. ፪ ፡ ፲፯ ፤ ፫ ፡ ፩—፮ ።
16. ፩ጴጥ. ፪ ፡ ፯ ። 17. ኤፌ. ፩ ፡ ፯ ፤ ፪ ፡ ፯ ፤ ፪ ፡ ፬ ፤ ፩ ፡ ፲፰ ፤ ፫ ፡ ፲፮ ።

ቀለማት ፡ እንዳሉ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ አሉ ። የቀስተ ፡ ዳመና ፡ ቀለማት ፡ ሁሉ ፡ ሲገጣ ጠሙ ፡ ሙሉ ፡ ቀስተ ፡ ዳመና ፡ እንደሚሆንና ፡ እኛ ፡ እያንዳንዱን ፡ ቀስም ፡ ስናስተውል ፡ ሙሉውን ፡ ቀስተ ፡ ዳመና ፡ እንደምናይ ፡ እንዲ ሁም ፡ እያንዳንዱን ፡ የእግዚብሔርን ፡ የጥበብን ፡ ቀለም ፡ ስናስተውል ፡ ሙሉውን ፡ ጥበብ ፡ ለማወቅ ፡ እንበቃለን ። «የጥበቡ ፡ ቀለማት» የተባ ለው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ለመሆኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕይወታችን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሲመ ራን ፡ ጥበቡ ፡ ምንኛ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ነው! ወደ ፡ ኋላ ፡ ዞረን ፡ ስንመ ለክት ፡ በጥበቡ ፡ ያደረገልንን ፡ እናስተውል ። እውቀቱና ፡ ማስተዋሉም ፡ እንደምን ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ቸርነቱም ፡ እንደምን ፡ ታላቅ ፡ ነው!

«የእግዚአብሔር ፡ ባለ ፡ ጠግነትና ፡ ጥበብ ፡ እውቀቱም ፡ እንዴት ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ ፍርዱ ፡ እንዴት ፡ የማይመረመር ፡ ነው ፡ ለመን ገዱም ፡ ፍለጋ ፡ የለውም ።» ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫ ።

ቀ) «በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ በሰማያዊ ፡ ሥፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አለቆችና ፡ ሥልጣናት ፡ ትታወቅ ፡ ዘንድ ።» (ቊ. ፲ ።) ቤተ ፡ ክርስቲያን! ታላቅ ፡ ድርጅት ፡ ናት ፡ እኩ! አደራ ፡ የተሰጣትም ፡ ሥራ ፡ እንደዚሁ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። «ሥራዋ ፡ ምንድር ፡ ነው?» ቢሉ ፡ ማስታወቅ ፡ ማስተማርም ፡ ነው ። ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አደራ ፡ የተሰጣት ፡ ተግባር ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ማስተማር ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ የዓለምን ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ በሰማያዊ ፡ ሥፍራ ፡ ያሉትን ፡ አለቆችና ፡ ሥልጣናትም ፡ ጭምር ፡ ነው ።[18] የሐዋርያት ፡ ተግባር ፡ ማስተማር ፡ ነበረ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ተግባር ፡ ይኸው ፡ ነው ። የማታስተምር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሞተች ፡ ናት ፡ በእርስዋም ፡ መጀመሪያ ፡ የሐዋርያ ነት ፡ ምልክት ፡ የለባትም ። «ምኑን ፡ ታስተምራለች?» ይላሉን? የእግዚ አብሔርን ፡ ጥበብ ፡ የክርስቶስን ፡ ምሥጢር ፡ ነዋ ![19]

«ምነው ፡ በሰማያዊ ፡ ሥፍራ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የመላእክት ፡ አለ ቆችና ፡ ሥልጣናት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አያውቁም ፡ ወይ?» ቢሉ ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ጥበብ ፡ ውስጥ ፡ የማያውቋቸው ፡ ቀለማት ፡ አሉ ፤ ቤተ ፡ ክር ስቲያኒቱም ፡ እነዚህን ፡ የማያውቋቸውን ፡ ቀለማት ፡ ታስታውቃቸዋ ለች ። ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሲመጣ ፡ አይተውታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የመ ጣበትን ፡ ምክንያት ፡ አላወቁም ። «እግዚአብሔር ፡ ያስበው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው?» አሉ ።[20] ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፡ የሆነውንም ፡ ዕቅድ ፡ አላወቁም ። ይህንንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሊመለክቱ ፡ ይመኛሉ ።[21] የሚ

18. ኤፌ. ፮ ፡ ፲፪ ። 19. ቈላ. ፪ ፡ ፩—፫ ። 20. መዝ. ፰ ፡ ፬—፰ ።
21. ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፲፪ ።

ያውቁትም ፡ የገሀነም ፡ ደጆች ፡ በማይችሉአት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ ነው ።[22] ዛሬስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተግባርዋን ፡ ስትፈጽም ፡ ትገኛለችን ?

ቊ. ፲፬ — ፳፩ ።

ምእመናን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጠንክረው ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማወቅ ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያው ፡ ጸኖ ፡ ጸሎት ።

፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለ ፡ አባትነት ፡ ሁሉ ፡ ከሚሰየምበት ፡ ክአብ ፡ ፊት ፡ እንበረ

፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ክካለሁ ፡ በመንፈሱ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታችሁ ፡ በኃይል ፡ እንድትጠነክሩ ፡ ክርስቶስም ፡ በልባችሁ ፡ በእምነት ፡ እንዲኖር ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ መጠን ፡ ይስጣችሁ ፡ የእናንተም ፡ ሥርና ፡ መሠረት ፡ በፍቅር ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፡

፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ከቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ስፋቱና ፡ ርዝመቱ ፡ ክፍታውም ፡ ጥልቅነቱም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ ለማስተዋል ፡ ከመታወቅም ፡ የሚያልፈውን ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማወቅ ፡ ትበረቱ ፡ ዘንድ ፡ እስክ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሳችሁ ፡ ትሞሉ ፡ ዘንድ ።

፳፤ እንግዲህ ፡ በእኛ ፡ እንደሚሠራው ፡ ኃይል ፡ መጠን ፡ ክምንለምነው ፡ ወይም ፡ ከምናስበው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡

፳፩ ፤ አጅግ ፡ አብልጦ ፡ ሊያደርግ ፡ ለሚችለው ፡ ለእርሱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስክ ፡ ትውልዶች ፡ ሁሉ ፡ ከዘላለም ፡ እስክ ፡ ዘላለም ፡ ክብር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

ግሩም ፡ የሆነ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፤ ክፍል ፡ ክፍሉንም ፡ ለመለየት ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። የሚጸልየው ፡ ለሁለት ፡ ነገር ፡ ነውን ፡ ለሦስት? በአማርኛ ፡ ትርጉማችን ፡ ለሁለት ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡ ይመስላል ፤ መጀመሪያ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታቸው ፡ ይጠነክሩ ፡ ዘንድ ፤ ሁለተኛም ፡ እስክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሰው ፡ ይሞሉ ፡ ዘንድ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሚጸልየው ፡ ለሦስት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። ፩ኛ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታቸው ፡ ይጠነክሩ ፡ ዘንድ ፤ ፪ኛ ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማወቅ ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፤ ፫ኛ ፡ እስክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሰው ፡ ይሞሉ ፡ ዘንድ ።

እውነተኛው ፡ የቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ በእውነት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ እውነቱን ፡ የሚያውቅ ፡ ያ ፡ የሚጸልይ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡

22. ማቴ. ፲፮ ፡ ፲፰ ።

ይሆናል ። ተንበርክከ ፡ ተጣጥሮ ፡ መጸለዩን ፡ ልብ ፡ እናድርግ ። ለመሆኑ ፡ እኛ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ናፍቀን ፡ ተጣጥረን ፡ በጋለ ፡ መንፈስ ፡ ስንጸልይ ፡ ጸሎታችንንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስናፈስ ፡[23] ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለምን ? ብዙውን ፡ እንፈልጋለን ፡ በአንድ ፡ ጊዜም ፡ ቶሎ ፡ ብለን ፡ ለሁሉ ፡ እንጸልያለን ። በኋላም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጸሎታችንን ፡ መርምሮ ፡ ሊፈታታውና ፡ ሊተነትነው ፡ ቢወድ ፡ ይቸገርበት ፡ ይሆናል! ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በሐዋርያው ፡ ጸሎትም ፡ «በእርግጥ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡» ለማለት ፡ ባንችልም ፡ ቅሉ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይጨነቅበት ። ራሱ ፡ ግሪኩ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፡ ለመጨረሻውም ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ማሰርያ ፡ ግሥ ፡ እንኳ ፡ የለም ።

ሐዋርያው ፡ በቊ. ፩ ፡ ላይ ፡ የጀመረውን ፡ ጸሎት ፡ አሁን ፡ ይቀጥላል ። «ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉንም ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለልና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ ለማሰታወቅ ፡ ስለ ፡ አሰበ ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተንበርክኬ ፡ እጸልያለሁ ፡» ይላል ። እንደ ፡ አይሁድ ፡ ልማድ ፡ ቆሞ ፡ ሳይሆን ፡ ተንበርክክ ፡ መጸለዩ ፡ በኃይል ፡ አጥብቆ ፡ መጸለዩን ፡ ያስረዳል ። ጸሎቱን ፡ የሚያቀርበው ፡ አባትነት ፡ ሁሉ ፡ ወደሚለየምበት ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እኛ ፡ «አባትነት» ስንል ፡ ሰለምን ፡ ነገር ፡ እናስባለን? ስለ ፡ ቸር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፤ ሮጠን ፡ በድፍረት ፡ ቀርበን ፡ ረዴትን ፡ ማግኘት ፡ አይደለምን? አይ! አባትነት ፡ የትም ፡ ዘንድ ፡ ቢገኝ ፡ በሰማይም ፡ ሆነ ፡ በምድር ፡ ሁሉም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አባትነት ፡ አነስተኛ ፡ ጥላ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ አባትነት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ክሁሉ ፡ የሚበልጥና ፡ የሚሻል ፡ እውነተኛ ፡ አባትነት ፡ ነው ። ሐዋርያውም ፡ ጸሎቱን ፡ የሚያቀርበው ፡ ለዚህ ፡ ቸርና ፡ ቻይ ፡ ለሆነ ፡ አባት ፡ ነውና ፡ የለመነውን ፡ ያገኝ ፡ የለምን? ያገኛል![24] ስለምን ፡ ነገርስ ፡ ይጸልያል? ድርብ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ ይጸልያል ። የኤፌሶንና ፡ በዙሪያዋ ፡ የተገኙት ፡ ምእመናን ፡ ዓለምንና ፡ ፈተናውን ፡ ችለው ፡ ታላቅ ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታቸው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኃይል ፡ እንዲጠነክሩና ፡ ክርስቶስ ፡ በልባቸው ፡ እንዲኖር ፡ ነው ።[25] ሁለቱም ፡ ነገሮች ፡ በእውነት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ናቸው ። «ይህን ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጣችሁ!» ይላል ። መጠኑስ? እሪ ፡ መለስተኛ ፡ መጠን ፡ አይደለም! እንደ ፡ ክብሩ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ መጠን ፡ ነው ፡ ሰፋፊ ፡ መጠን! በዚህ ፡ መጠን ፡ ይስጣቸው!

እንደገና ፡ ድርብ ፡ ለሆኑ ፡ ለሁለት ፡ ነገሮች ፡ ደግሞ ፡ ይጸልያል ። ቀድሞ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታቸው ፡ እንዲጠነክሩ ፡ ጸሎት ፡ አቅርቦአል ፡ አሁን ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማወቅ ፡ እንዲበረቱ ፡ ይጸልያል ። ሥራቸውና ፡ መሠረታቸው ፡ እንደ ፡ ተክል ፡ ተተክሎ ፡ እንደ ፡ ሕንጻም ፡ ታንጸ ፡[81] በእ

23. ፩ሳሙ. ፩ ፡ ፲፮—፲፯ ። 24. ፊልጵ. ፬ ፡ ፲፱ ። 25. ፩ቆሮ. ፲፮ ፡ ፲፫ ። 26. ፩ቆሮ. ፫ ፡ ፱ ።

ግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ጸንቶ ፡ ኖሮ ፡ ከሞላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ መጠኑ ፡ እስከዚህ ፡ ነው ፡ የማይባለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቅድ ፡ ወይም ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማስተዋልና ፡ የማይቻልም ፡ ቅሉ ፡ ቢሆን ፡ ያን ፡ ፍቅር ፡ በሕይወታቸው ፡ ለማወቅ ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡ ይጸልያል ።[27] በተጨማሪም ፡ ወይም ፡ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ እውቀት ፡ የወጣ ፡ ይሆናል ፡ እስከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ድረስ ፡ ይሞሉ ፡ ዘንድ ፡ ይለምናል ።

ጸሎቱንም ፡ ጨርሶ ፡ ሲያበቃ ፡ በእኛ ፡ ውስጥ ፡ በእኛም ፡ በኩል ፡ እንደሚሠራው ፡ ኃይል ፡ መጠን ፡ ከተለመነው ፡ ወይም ፡ ከታሰበው ፡ ሁሉ ፡ ስንኳ ፡ በላይ ፡ እጅግ ፡ አብልጦ ፡ ሊያደርግ ፡ ለሚቻለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በክርስቶስ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሆነውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅ ፡ አሳብ ፡ እያየ ፡ ምስጋናን ፡ ያቀርባል ።[28] «አሜን» ብሎም ፡ ጸሎቱንና ፡ የመልእክቲቱን ፡ የዶክትሪንን ፡ (የትም ሀርትን ፡) ክፍል ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ያደርሳል ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «እንበረከካለሁ ።» (ቊ. ፲፬ ፡ ፲፭ ።) እንደ ፡ አይሁድ ፡ ልማድ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ ጸሎቱ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ይንበርከክ ፡ ነበር ።[29] በሐዋርያትም ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተንበርክከው ፡ የጸለዩ ፡ ይመስላል ።[30] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊው ፡ ጸሎቱ ፡ ከልብ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብንቆም ፡ ብንቀመጥ ፡ ብንንበረከክ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አይቈጠርም ።[31] ቢሆንም ፡ ጸሎትን ፡ የምንጸልይ ፡ ለቸር ፡ አባት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ እያሰብን ፡ ከዚህ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የሚስማማውንና ፡ የሚገባውንም ፡ አቀራረብ ፡ እንምረጥ ።[32]

ለ) «በውስጥ ፡ ሰውነታችሁ ።» (ቊ. ፲፮ ፡ ፲፯ ።) «የውስጥ ፡ ሰውነት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው?» ቢሉ ፡ በእያንዳንዳችን ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ መንፈሳዊው ፡ ክፍል ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የውስጥ ፡ ሰውነታችንን ፡ የሚያጠነክረው ፡ ክርስቶስ ፡ በልባችን ፡ ሲኖር ፡ ነውና ፡ የውስጥ ፡ ሰውነታችንና ፡ ልባችን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘባለን ። የውጭው ፡ ሰውነታችን ፡ እንዳለ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ የውስጥ ፡ ሰውነታችን ፡ አለ ።[33] ኃይልን ፡ የምንፈልገው ፡ በዚያ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ሰው ፡ እንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሚዳዊ ፡ ኃይልን ፡ ዓለማዊ ፡ ኃይልን ፡ ይፈልጋል ። ይህን ፡ ሲያደርግ ፡ ወይም ፡ ስታደርግ ፡ እምብዛም ፡ መንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡

27. ፊልጵ.፩፡፱። ዮሐ.ቮ፡፲፭። ሮሜ፡፭፡፭። ገላ.፪፡፳። 28. ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፭። ይሁዳ፡ቊ. ፳፬። 29. ፩ነገ. ፰፡ ፳፪፡ ፳፫፡ ፱፱። ማቴ.፮፡፭። ሉቃ. ፲፰፡ ፲፭፡ ፳፪። የሐዋ. ፯፡ ፷፡ ፱፡ ፺። 30. የሐዋ. ፳፡ ፴፮፤ ፳፩፡፭። 31. ዮሐ. ፮፡ ፳፬። 32. መዝ. ፵፯፡ ፪፡ ፮፡ ፯። ሚል. ፩፡ ፲፪። 33. ፪ቆሮ. ፬ ፡ ፲፮ ። ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፳፪—፳፬ ።

እየቀነሰ ፡ ይሄዳል ። መንፈሳዊ ፡ ኃይልን ፡ የምናገኘው ፡ ከርስቶስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በልባችን ፡ ሲኖር ፡ ነው ።

ሐ) «ከርስቶስ ፡ በልባችሁ ፡ በእምነት ፡ እንዲኖር ።» (ቊ. ፲፯ ፡ ፲፯ ።) ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ በሰማይ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በልባችን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ልኮአል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ነውና ፡ «ክርስቶስ ፡ በልባችን ፡ ይኖራል ፡» ይባላል ።[34] «ይኖራል» ሲባልም ፡ እንደ ፡ ነዋሪ ፡ ባለቤት ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለጥቂት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ እንደሚቀመጥ ፡ እንደ ፡ እላፊ ፡ እንግዳ ፡ መሆኑ ፡ አይደለም ። ልባችንን ፡ የግልና ፡ የገዛ ፡ ራሱ ፡ ቤት ፡ ለማድረግ ፡ ይመጣል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ሰብሮ ፡ እንደ ፡ ድል ፡ ነሺ ፡ ገዝቶ ፡ ያለ ፡ ፈቃዳችን ፡ አይመጣም ፡ «በእምነት» ይኖራል ፡ ተባለ ፡ እንጂ ። ማለት ፡ እኛ ፡ በእምነት ፡ በሩን ፡ ስንከፍትለትና ፡ «ግባ» ብለን ፡ ስንጋብዘው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ ካልተጠራ ፡ አይገባም ። ሲጋበዝ ፡ ግን ፡ ከነኃይሉ ፡ ይገባል ።

መ) «ሥርና ፡ መሠረት ።» (ቊ. ፲፰ ፡ ፲፱ ።) እንድ ፡ ተክል ፡ ሥሩን ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ እጥልቆ ፡ እንደሚሰድ ፡ እንድ ፡ ሕንጻም ፡ ሲሚንቶ ፡ በሚመስል ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እንደሚቆም ፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ከርስቲያን ፡ ሥሩን ፡ ወደ ፡ ፍቅር ፡ መስደድና ፡ መሠረቱን ፡ ፍቅርን ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልገዋል ። «ይህም ፡ ፍቅር ፡ ምንድር ፡ ነው?» ቢሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍቅሩ ፡ የዋለለትን ፡ ውለታ ፡ በመገንዘብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሆን ፡ የእንድ ፡ ሰው ፡ ፍቅር ፡ ነው ።[35] ያ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ፍቅር ፡ ከተተከለ ፡ ከቆመም ፡ አይነቀልም ፡ አይናወጥምም ። በፍቅርም ፡ ጸንቶ ፡ ሲኖር ፡ ወደ ፡ ማስተዋልና ፡ ወደ ፡ ማወቅም ፡ ይደርሳል ።[36]

ሠ) «እስከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሳችሁ ፡ ትሞሉ ፡ ዘንድ ።» (ቊ. ፲፰ ፡ ፲፱ ።) እግዚአብሔር ፡ በሙላቱ ፡ በመሞላት ፡ እንጂ ፡ ፍቅርን ፡ እውቀትን ፡ ኃይልን ፡ ለብቻው ፡ ለብቻው ፡ በመስጠት ፡ ጉድለታችንን ፡ ሊያምዋላ ፡ እላሰበም ። በከፊል ፡ ሳይሆን ፡ ሙላትን ፡ ይሰጠናል ።[37] ጳውሎስ ፡ እስከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሰን ፡ እንሞላ ፡ ዘንድ ፡ ይጸልያል ፤ ይህም ፡ ለእያንዳንዳችን ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብና ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። በእጭሩ ፡ ከርስቶስን ፡ እንድንመስል ፡ ነው ።[38] መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታችንና ፡ ከርስቶስ ፡ በልባችን ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ይኸው ፡ ነው ። ከርስቶስን ፡ እንመስል ፡ ዘንድ ፡ ጠባያችንን ፡ ይቀርጻሉ ፤ ከዕለታትም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቅርጹ ፡ ይሞላል ።[39]

34. ዮሐ. ፲፬ ፡ ፲፯—፲፰ ። የሐዋ .፲፯ ፡ ፮ ፡ ፮ ። 35. ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ፭ ። 36. ቈላ. ፪፡፮ ። 37. ዮሐ. ፩ ፡ ፲፯ ። 38. ሮሜ፡ ፰፡ ፳፱ ። ኤፌ. ፬፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። 39. ፩ዮሐ. ፫ ፡ ፪ ።

ረ) «በእኛ ፡ እንደሚሠራው ፡ ኃይል ፡ መጠን ።» (ቊ. ፳ ።) ጳውሎስ ፡ በጸሎቱ ፡ አሁኑኑ ፡ ሲሰማንና ፡ ሲያስብ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ «እግዚአብሔር ፡ ከምንለምነው ፡ ወይም ፡ ከምናስበው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ አብልጦ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።» ይላል ። ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አደራረግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ አይደለም ። አምላክ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ሊያደርግ ፡ እንደሚችል ፡ እናምናለን ።[40] የሚያስደንቀውና ፡ በጣሙን ፡ የሚያስገርመው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በእኛ ፡ ማለት ፡ በእኛ ፡ ውስጥና ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ ሰማድረግ ፡ መቻሉ ፡ ነው! ይህ ፡ በእውነት ፡ ያስገርማል! ቢሆንም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። በ፩ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ ይልቁንም ፡ በሞላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቁን ፡ ሥራ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

በተሰይ ፡ ስለ ፡ ምእመናንና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምትናገር ፡ በዚህች ፡ መልእክት ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህ ፡ ኃይል ፡ ኢያሴ ፡ ጊዜያት ፡ እና ነባሰንና ፡ ነገሩን ፡ ደኅና ፡ አድርገን ፡ መገንዘብ ፡ ይገባናል ።[41] ወንድም ፡ ሆይ ፡ ደካማ ፡ ነዎትን? የማይረባ ፡ ዓቅመ ፡ ቢስ ፡ ታናሽ ፡ ሰው ፡ ኃይልም ፡ ሥልጣንም ፡ የሌለዎት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይሰማዎታልን? ቤተ ፡ ክርስቲያንስ? በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ይሰማታልን? እስኪ ፡ ዝም ፡ ይበሉ፤ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ከምንለምነው ፡ ወይም ፡ ከምናስበው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ አብልጦ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል! ያ ፡ ኃይል ፡ እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣው ፡ ያሳየው ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ በእርስዎ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሊሠራ ፡ ተሰናድቶአል ። «ኃይልን ፡ በሚሰጠኝ ፡ በክርስቶስ ፡ ሁሉን ፡ እችላለሁ» ይበሉ ፡ እኮ![42] እርስዎ ፡ ለዚህ ፡ ዝግጁ ፡ ነዎትን? ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ ዝግጁ ፡ ናትን? እሪ ፡ መብታችን ፡ ታላቅ ፡ ነው! ኃላነፊታችንም ፡ እንደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

ሰ) «በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በክርስቶስ ።» (ቊ. ፳፩ ።) ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ በዓለምም ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ በሰማይ ፡ የሚታወቀው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አማካይነት ፡ ነው ፡ አሳቡም ፡ የሚፈጸመው ፡ በክርስቶስ ፡ ነው ።[43] እንግዲያውስ ፡ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱም ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይፈልቃል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በእማርኛ ፡ ትርጕማችን ፡ አሁን ፡ «—ና» የምትባለው ፡ መስተፃምር ፡ የለችምና ፡ «በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስቶስ» ማለት ፡ ክብር ፡ አቅራቢዋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታቀርበውም ፡ በክርስቶስ ፡ በኩል ፡ መሆኑ ፡ ይሆናል ።

---

40. ሮሜ፡ ፮፡፫፡፳፩። ፩ተሰ. ፩፡፲፩። 41. ም. ፩፡ ፲፱፡ ፳፡ ም. ፫፡ ፮፡ ፳፡ም. ፮፡ ፲።
42. ፊልጵ. ፬ ፡ ፲፫ ። 43. ም. ፫ ፡ ፲ ።

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ እርሱም ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥጢር ፡ በሰማያዊ ፡ ሰፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አለቆችና ፡ ሥልጣናት ፡ እንዲታወቅ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በኩል ፡ ክብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦአልና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ምእመንዋ ፡ የተጠሩለት ፡ ሥራ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። (ም. ፫ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።) ይህ ፡ በመልእክቲቱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ በዶክትሪን ፡ (በትምህርት ፡) ክፍል ፡ ላይ ፡ ተጽፎአል ፡ ክፍሱም ፡ «አሜን» በተባለው ፡ ቃል ፡ ተዘግቶአል ። (ም. ፫ ፡ ፳፩ ።) አሁን ፡ በመልእክቲቱ ፡ ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ በገቢር ፡ የሚገለጥ ፡ በሥራ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ አካል ፡ የሆነች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎችዋ ፡ (አካላት) የሆኑ ፡ ምእመናንም ፡ ይህን ፡ ዶክትሪን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲት ፡ እንደሚያውሉ ፡ ተጽፎአል ፡ ይህም ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ «አሜን» በሚባል ፡ ቃል ፡ ይዘጋል ። (ም. ፮ ፡ ፳፬ ።)

በምዕራፍ ፡ አራት ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ምእመናን ፡ አባሎችዋ ፡ (አካላት) ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ይገልጣል ። (ቊ. ፩—፲፮) ፡ ቀጥሎም ፡ ከቊ. ፲፯— ፴፪ ፡ ድረስ ፡ ሐዋርያው ፡ ክሰሚገባ ፡ ስለ ፡ ምእመናን ፡ አዲስና ፡ ልዩ ፡ አመላለስ ፡ ይናገራል ።

ቊ. ፩ — ፲፯ ።

ስለ ፡ ምእመናን ፡ አንድነትና ፡ ልዩነት ።

፩ ፡ እንግዲህ ፡ በጌታ ፡ እስር ፡ የሆንሁ ፡ እኔ ፡ በተጠራችሁበት ፡ መጠራታችሁ ፡ እንደሚገባ ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ አለምናች
፪ ፡ ኋለሁ ፤ በትሕትና ፡ ሁሉና ፡ በየዋህነት ፡ በትዕግሥትም ፤
፫ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በፍቅር ፡ ታገሡ ፤ በሰላም ፡ ማሰሪያ ፡ የመንፈስን ፡ አንድነት፡ ለመጠበቅ ፡ ትጉ ። በመጠራታችሁ፡
፬ ፡ በአንድ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ተጠራችሁ ፡ አንድ ፡ አካልና ፡
፭ ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ አለ፤ አንድ ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት፡ አንዲት ፡ ጥምቀት ፤ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ በሁሉም ፡ የሚ
፮ ፡ ሠራ ፡ በሁሉም ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ የሁሉም ፡ አባት ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ስጦታ ፡
፯፡፰ ፡ መጠን ፡ ለእያንዳንዳችን ፡ ጸጋ ፡ ተሰጠን ። ስለዚህ፡ — ወደ ፡ ላይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ምርኮን ፡ ማረከ ፡ ለሰዎችም ፡ ስጦታን ፡ ሰጠ ፡
፱ ፡ ይላል ። (ወደ ፡ ምድር ፡ ታችኛ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ፡ ማለት ፡
፲ ፡ ካልሆነ ፡ ይህ ፡ ወጣ ፡ ማለትስ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው? ይህ ፡ የወረደው ፡ ሁሉን ፡ ይሞላ ፡ ዘንድ ፡ ከሰማያት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የወጣው ፡

፲፩ ፤ ደግሞ ፡ ያው ፡ ነው ።) እርሱም ፡ አንዳንዶች ፡ ሐዋርያት ፡ ሌሎቹም ፡ ነቢያት ፡ ሌሎቹም ፡ ወንጌልን ፡ ሰባኪዎች ፡ ሌሎቹም ፡ እረኞችና ፡ አስተማሪዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ሰጠ ፤
፲፪፣ ፲፫ ፡ ሁላችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ በማመንና ፡ በማወቅ ፡ ወደሚገኝ ፡ አንድነት ፡ ሙሉ ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ የክርስቶስም ፡ ሙላት ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ ሙላቱ ፡ ልክ ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ ቅዱሳን ፡ አገልግሎትን ፡ ለመሥራት ፡ የክርስቶስን ፡ አካል ፡ ለማነጽ ፡ ፍጹማን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ።
፲፬ ፤ እንደ ፡ ስሕተት ፡ ሽንገላ ፡ ባለ ፡ ተንኰል ፡ በሰዎችም ፡ ማታለል ፡ ምክንያት ፡ በትምህርት ፡ ነፋስ ፡ ሁሉ ፡ እየተፍገመገምን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህም ፡ እየተንሳፈፍን ፡ ሕፃናት ፡ መሆንን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አያገባንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እውነትን ፡ በፍቅር ፡ እየያዝን ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ራስ ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደግ ፤ ክእርሱም ፡ አካል ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ዘልክ ፡ እንደሚሠራ ፡ መጠን ፡ በተሰጠለት ፡ በጅማት ፡ ሁሉ ፡ እየተጋጠመና ፡ እየተያያዘ ፡ ራሱን ፡ በፍቅር ፡ ለማነጽ ፡ አካሉን ፡ ያሳድጋል ።

እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ በመልእክቲቱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ከሆነ ፡ ማለት ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በፊቱ ፡ ቅዱሳንና ፡ ነውር ፡ የሌለን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ከተመረጥን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ልንሆን ፡ አስቀድመን ፡ ከተወሰንን ፡ እኛ ፡ ለክብሩ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ከታሰበ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ክክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ከተቀመጥን ፡ ከቅዱሳን ፡ ጋር ፡ ባለ ፡ አገሮችና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ በተሰፋ ፡ ቃልም ፡ አብረን ፡ የምንካፈል ፡ ከሆንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከዘላለም ፡ የተሰወረው ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥጢር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሁሉ ፡ እንድንገልጥና ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉቱ ፡ ለማስታወቅ ፡ ከተጠራን ፡[1] ወንበዴ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ እስር ፡ የሆነ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደሚገባ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ከመጠራታችን ፡ ጋር ፡ በሚስማማ ፡ አመላለስ ፡ እንመላለስ ፡ ዘንድ ፡ ይለምንናል ።[2] «ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ አመላለስ ፡ እንዴት ፡ ነው?» ቢባልም ፡ ፭ኛ ፤ መጠራታችንን ፡ አይተን ፡ እንኰራ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ክብር ፡ ከየት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ተገንዝበን ፡ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሆነን[3] ፡ በትሕትና ፡ መመላለስ ፡ ነው ። ፪ኛ ፤ እኛ ፡ ዋነኞቹ ፡ ለመሆን ፡ ሳንመኝ ፡ ሌሎችን ፡ እንዳንጐዳ ፡ እየተጠነቀቅን ፡ ሥራችንን ፡ ሁሉ ፡ በቀስታና ፡ በፍቅር ፡ መንፈስ ፡ በመሥራት ፡ እንደ ፡ ርግቦች ፡ ሆነን ፡[4] በየዋህነት ፡ መመላለስ ፡ ነው ። ፫ኛ ፤ ገበሬው ፡ እንደሚ

1. ም. ፩ ፡ ፱ ። ም. ፩ ፡ ፩ ። ም. ፩ ፡ ፲፪ ፤ ፫ ፡ ፳፩ ። ም. ፪ ፡ ፯ ። ም. ፪ ፡ ፲፱ ፤ ፫ ፡ ፯ ። ም. ፫ ፡ ፩—፲ ። 2. ቈላ. ፩ ፡ ፲ ። ፩ ፡ ተሰ. ፪ ፡ ፲፪ ። 3. ዘኍል. ፲፪ ፡ ፫ ። 4. ማቴ. ፲ ፡ ፲፮ ።

ታገሥ ፡ ራሱ ፡ ጌታም ፡ እንደሚታገሥ ፡[5] እኛም ፡ ብዙ ፡ ጊዜና ፡ እስክ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ወንድማችንን ፡ እየታገሥን ፡ በትዕግሥት ፡ መመላለስ ፡ ነው ። ፮ኛ ፤ በመካከላችን ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በመመልከት ፡ መለያየትንና ፡ ጠብን ፡ በማንሣት ፡ ፋንታ ፡ ሁላችን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ መሆናችንን ፡ ተገንዝበን ፡[6] በሰላም ፡ ማሰሪያ ፡ ታስረን ፡ የመንፈስን ፡ አንድነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ተግተን ፡ መመላለስ ፡ ነው ። አንድነታችንም ፡ የእውነት ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ሐዋርያውም ፡ በእነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅኔ ፡ ወይም ፡ መዝሙር ፡ የሚጠቅስ ፡ ይመስላል ። ወደ ፡ ክርስትና ፡ በተጠራንበት ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ተስፋ ፡ ተይዘን ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ተስፋ ፡ እርሱም ፡ የክብር ፡ ተስፋ ፡ ተጠርተናል ።[7] በክርስቶስ ፡ የሆኑቱም ፡ ሁሉ ፡ የአንዱ ፡ አካል ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ አካላት ፡ ናቸው ።[8] በመካከላችን ፡ ወይም ፡ በልባችን ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለ ። የሁላችን ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ነው ፤[9] ሁላችንም ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃናት ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰኑትን ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደግማለንና ፡ እናምንበታለን ፡ ስለዚህም ፡ ሃይማኖታችን ፡ አንድ ፡ ነው ። ስንጠመቅም ፡ ሁላችን ፡ በአብ ፡ በወልድና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ እንጠመቃለንና ፡ ጥምቀታችን ፡ አንድ ፡ ነው ።[10] በላይ ፡ ያለው ፡ በሁሉም ፡ የሚሠራና ፡ በሁሉም ፡ የሚኖር ፡ ሦስትነቱ ፡ በአንድነት ፡ የሆነ ፡ አምላካችንም ፡ አንድ ፡ ነው ።[11]

ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ቢሆኑም ፡ በመካከላቸው ፡ ልዩነት ፡ አለ ። ለእያንዳንዳቸው ፡ ለእያንዳንዳችንም ፡ ያውም ፡ ክርስቶስ ፡ በወደደው ፡ መጠን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ተሰጥቶአል ።[12] ሰጪው ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። «ይህስ ፡ በምን ፡ ይታወቃል?» ቢሉ ፡ ዳዊት ፡ በመዝ. ፷፯ ፤ ፷፰ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ስጦታን ፡ የሚሰጥ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ ነው ። «ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ» ሲል ፡ አስቀድሞ ፡ ወረደ ፡ ማለቱ ፡ አይደለምን? ነው! ታዲያ ፡ ማን ፡ ነው? ክርስቶስ ፡ ነዋ! አስቀድሞ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ምድር ፡ ወረደ ፡ ቀጥሎም ፡ የሁሉም ፡ መፈጸሚያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያትም ፡ ወጣ ።[13] ወጥቶም ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ አሸናፊ ፡ ጂኔራል ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲያበቃ ፡ ድል ፡ የሆኑትን ፡ ሕዝብ ፡ ሰብስቦ ፡ አስክትሎ ፡ ያዞራቸው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ግርማ ፡ በሞላበት ፡ ሰልፍ ፡ ሲሄድ ፡ ስጦታን ፡ ይሰጥና ፡ ይቀበል ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ እንዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ አለቆችንና ፡ ሥልጣናትን ፡ ገፎ ፡ ድል ፡ በመንሣት ፡ በክርስቶስ ፡ እያዞራቸው ፡ በግልጥ ፡ አሳያቸው ፡ በክርስቶስም ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ስጦታን ፡ ሰጠ ።[14] ምኑን ፡ ሰጣቸው?

5. ያዕ. ፭ ፡ ፰ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፱ ። 6. ገላ. ፫ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ። 7. ም. ፭ ፡ ፲፰ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፪ ። 8. ም. ፪ ፡ ፲፩—፲፮ ። 9. ፩ቆሮ. ፰ ፡ ፮ ፡ ፯ ። 10. ማቴ. ፳፰ ፡ ፲፱ ። 11. ሮሜ ፡ ፴ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ። 12. ም. ፫ ፡ ፪ ፡ ፯—፱ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፮—፰ ። ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፲፩ ። 13. ዘፍጥ. ፵፱ ፡ ፳፭ ። ኢሳ. ፶፭ ፡ ፱ ። ዘዳግ. ፲ ፡ ፲፬ ። 14. ፪ቆሮ. ፪ ፡ ፲፩ ። ቈላ. ፪ ፡ ፲፭ ።

ለእያንዳንዶቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያነትን ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ሰጣቸው ፡ ለሌሎቹ ፡ የክርስቲያን ፡ ነቢያት ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የነቢይነትን ፡ ስጦታ ፡ ሰጣቸው ፡ ለሌሎቹም ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡ የወንጌል ፡ ሰባኪነትን ፡ ጸጋ ፡ ሰጣቸው ፡ ለሌሎች ፡ ደግሞ ፡ የክርስቶስን ፡ መንጋ ፡ ይጠብቁና ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የእረኛነትንና ፡ የአስተማሪነትን ፡ ስጦታ ፡ ሰጣቸው ። ዓላማውስ ፡ ምንድር ፡ ነው? እነኝህ ፡ ስጦታዎች ፡ የተሰጡ ፡ ምን ፡ እንዲሆኑ ፡ ነው? የተሰጡት ፡ የአካሉ ፡ አባሎች ፡ (አካላት ፡) የሆኑ ፡ ቅዱሳን ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ለአገልጋይነት ፡ ሥራ ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ የሆነችውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማነጽ ፡ ፈጽሞ ፡ ቻዮች ፡ (ብቁዎች ፡) እንዲሆኑ ፡ ነው ።[15] ይህም ፡ ሥራቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሆነውን ፡ አንዱን ፡ ክርስቶስን ፡ በማመንና ፡ እርሱን ፡ በግል ፡ ሕይወት ፡ በማወቅ ፡ ወደ ፡ አንድነት ፡ ያደርሳልና ፡ ሁላችን ፡ ወደ ፡ አንድነት ፡ እስክንደርስና ፡ ሁላችን ፡ በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ ሙሉ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ እንዲያ ውም ፡ ክርስቶስን ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ መምሰል ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ ነው ።[16] ይህም ፡ አስፈላጊያችን ፡ ነው ። በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወርዶ ፡ ኖሮ ፡ በማዕበል ፡ የተናወጠችንና ፡ በነፋስም ፡ የተወሰደችን ፡ ታንኳ ፡ መሰ ልን ።[17] በሰዎች ፡ ተንኰልና ፡ በስሕተት ፡ ሽንገላ ፡ በሚፈለስፉት ፡ በሐ ሰት ፡ ትምህርት ፡ ነፋስ ፡ ሁሉ ፡ ተናውጠን ፡ ተወስደን ፡ ሕፃናት ፡ ልንሆን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አይገባንም ። ነገር ፡ ግን ፡ በተንኰል ፡ ሳይሆን ፡ እውነትን ፡ እየያዝን ፡ ቁመት ፡ ጨምረን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንበልና ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ራሳችን ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደግ ። ከእርሱ ፡ ከራስ ፡ (ከክርስቶስ ፡) በተ ሰጠለት ፡ ጅማት ፡ (አባል ፡ አካላት ፡ ክርስቲያን ፡) ሁሉ ፡ ተጋጥሞ ፡ ተያ ይዞም ፡ እያንዳንዱም ፡ ክፍል ፡ በየመጠኑ ፡ ሲሠራ ፡ አካሉ ፡ ሁሉ ፡ (ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡) መንፈሳዊ ፡ ቁመት ፡ እየጨመረ ፡ ይሄድና ፡ ራሱን ፡ በፍቅር ፡ ያንጻል ።

<u>ማስገንዘቢያ</u> ። ሀ) «እንግዲህ» (ቁ. ፭ ።) በሃይማኖታችንና ፡ በአካሂዳ ችን ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ። ለምሳሌ ፡ የንጉሥ ፡ አሽ ከር ፡ በማይገባ ፡ ኑሮ ፡ ቢኖር ፡ ደግ ፡ አይደለም ። እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ለመቀመጥ ፡ የተጠራን ፡ ሰዎች ፡ ስንሆን ፡ ክርስቶስ ፡ ከዕለታዊ ፡ ሕይወታችን ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ እንዳ ለው ፡ ማሰብ ፡ ይገባናል ። ክርስቲያኖች ፡ ከሆንን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የሚ ያስተምረውንም ፡ ካመንን ፡ እንደ ፡ እምነታችን ፡ መኖርና ፡ መመላለስ ፡ ይገባናል ።

ለ) «መጠራታችሁ» (ቁ. ፩ ።) በሕይወታችን ፡ ዘመን ፡ በአንዱ ፡ ወቅት ፡ ሁላችን ፡ በቅዱስ ፡ አጠራር ፡ ተጠራን ፡ ወይም ፡ እንጠራለን ። እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ እንዲደርስ ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡

15. ፩ቆሮ. ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ። 16. ቈላ. ፩ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ። 17. ሉቃ. ፰ ፡ ፳፮—፳፱ ።

እንዳይጠፋ ፡ ስለሚወድ ፡ ሁሉን ፡ ጠርቶአል ።[18] ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ «ሳሙ ኤል ፡ ሳሙኤል ፡» ሲል ፡ እንዳንዶቻችን ፡ እንዳንሰማ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ይዘ ናል ፤ እንዳንዶቻችን ፡ በኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ደንቍረናል ፤ እንዳንዶ ቻችን ፡ ቸል ፡ ብለናል ፤ ሌሎቻችንም ፡ ብንሰማም ፡ ቅሉ ፡ ፈርተናል ።[19] እረ ፡ መጠራታችንን ፡ ሰምተን ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ እንስጥ!

ሐ) «በትሕትና ፡ ሁሉ ... በየዋህነት ... በትዕግሥት ... በሰላም» (ቁ. ፪ ፡ ፫ ።) የአንድ ፡ ክርስቲያን ፡ ፬ ፡ ምልክቶች ፡ «ሰው ፡ የእኔን ፡ አካ ሄድ ፡ ሲያስተውል ፡ እነዚህን ፡ ምልክቶች ፡ ያያልን?» ብሎን ፡ እያንዳን ዳችን ፡ እናስብ ።

መ) «አንድ ፡ አካል ።» (ቁ. ፬ ።) ይህን ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በም. ፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ላይ ፡ አግኝተናል ፡ በዚህም ፡ በአሁኑ ፡ ምዕራፍ ፡ በቁ. ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ላይ ፡ እናገኘዋለን ። ሐዋርያው ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይናገርም ። እነኝህ ፡ የየአገሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ አይደሉም ። አይሁኑ ፡ እንጂ ፡ የአካሉ ፡ አባሎች ፡ (አካላት) በእያንዳንዳቸው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። ሐዋርያው ፡ የሚናገረው ፡ የገሃነም ፡ ደጆች ፡ ስለማይችሉአት ፡ ስለ ፡ አንዲት ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ አቅሌሲያ ፡ ነው ።[20]

የአካሉ ፡ አባሎች ፡ (አካላት ፡) የምንሆነው ፡ የአንዱ ፡ አገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ በመሆናችን ፡ አይደለም ። የአካሉ ፡ አባሎች ፡ የም ንሆነው ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ በማመን ፡ አዲስ ፡ ስንወለድ ፡ ነው ። የአካሉ ፡ አባሎች ፡ በአገር ፡ ሁኔታና ፡ ባሕል ፡ ምክንያት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የእምነት ፡ አሳቦች ፡ ይሰያዩ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ አዳኝነት ፡ ሁሉም ፡ ይስማማሉና ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ይህንም ፡ አንድነት ፡ ልናውቅና ፡ ልና ጸና ፡ መታገል ፡ ይገባናል ።

ሠ) «አንድ ፡ ጌታ ።» (ቁ. ፭ ።) «ጌታ ፡» ብለን ፡ እንጠራዋለን ። ለመ ሆኑ ፡ ጌታችን ፡ ነውን? ክርስቶስ ፡ «እናንተ ፡ መምህርና ፡ ጌታ ፡ ትሉኛ ላችሁ ፤ እንዲሁም ፡ ነኝና ፡ መልካም ፡ ትላላችሁ ። እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ጌታ ፡ መምህር ፡ ስሆን ፡ እግራችሁን ፡ ካጠብሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እርስ ፡ በር ሳችሁ ፡ እግራችሁን ፡ ትተጣጠቡ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል» ብሎአል ።[21] ጨም ሮም ፡ «ስለምን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ትሉኛላችሁ ፡ የምለውንም ፡ አታደርጉም ፡» ብሎአል ። «ጌታ ፡» ብለን ፡ እንጠራዋለን ።[22] እንታዘዝ ለታለንን?

ረ) «ከሁሉ ፡ በላይ...በሁሉም ።» (ቁ. ፮ ።)ኤኖና ፡ ፪ኛ ፡ ማዕረግ ፡ ክርስቲያን ፡ የለም ። በክርስቶስ ፡ ያሉቱ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ናቸው ።[23] እርስ ፡

18. ፪ጢሞ. ፩ ፡ ፱ ። ፪ጴጥ. ፫ ፡ ፱ ። 19. ፩ሳሙ. ፫ ፡ ፩—፲ ። 20. ግቱ. ፲፮ ፡ ፲፰ ። 21. ዮሐ. ፲፫ ፡ ፲፫ ። 22. ሉቃ. ፮ ፡ ፵፮ ። 23. ገላ. ፫ ፡ ፳፰ ።

በርሳችን ፡ እንጎአደድ ፡ እንኰራርም ። እንዱን ፡ ከሌላ ፡ የሚሰይ ፡ የተ
ቀበለው ፡ ስጦታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የተሰጡት ፡ የጸጋ ፡ ስጦታዎች ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ መጠን ፡ በአሠራራችን ፡ ብቻ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
እንሆናለን ።[24]

ሰ) «ለእያንዳንዳችን ፡ ጸጋ ፡ ተሰጠን ።» (ቊ. ፯ ።) ለካህናት ፡ ብቻ ፡
አይደለም ፡ እኮ! ለእያንዳንዳችን ፡ ተሰጥቶአል ። ይህን ፡ ነው ፡ በብርቱ ፡
ማስታወስ ፡ የሚገባን ። ስጦታ ፡ የተሰጠው ፡ ለካህናት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡
ለምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ይህ ፡ ነው ፡ «የምእመናን ፡ ካህንነት» የተ
ባለው ፡ ነገር ። እያንዳንዱ ፡ አማኝ ፡ ክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡
ሊያገኛ ፡ መብት ፡ አለው ፡ መሥራትም ፡ ይገባዋል ። የካህናት ፡ ሥራ ፡
ብቻ ፡ አይደለም ። ሁላችን ፡ ካህናት፡ ነን ፤[25] ሁላችን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ውስጥ ፡ የምንሠራው ፡ ሥራ ፡ አለን ። ሆኖም ፡ እላይ ፡ እንዳልን ፡ ሁሉ ፡
ይህን ፡ ስንል ፡ በአገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሁላችን ፡ እንድናገ
ለግል ፡ ማለታችን ፡ ከቶ ፡ አይደለም ። የምንናገርበት ፡ ስለ ፡ አቅሌሲያ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያንም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ምድራዊ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይደለም ። በም
ድራዊ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዲያገለግሉ ፡ የተሰዩና ፡ የተሾሙ ፡
አገልጋዮች ፡ አሉ ።

ሸ) «ወንጌልን ፡ ለባኪዎች ።» (ቊ. ፲፩ ።) እነኝህ ፡ ገና ፡ በቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ። በክርስቲያን ፡ አገር ፡ ስለምንኖርና ፡ የክር
ስቲያንን ፡ መልክ ፡ ስለ ፡ ያዝን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ስለምንሄድ ፡
ስለዚህ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነንና ፡ ወንጌልን ፡ ለባኪዎች ፡ አያስፈልጉም ፡
ማለት ፡ ስህተት ፡ ነው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወንጌልን ፡ ያውቃል ፡ ማለት ፡ እው
ነት ፡ አይደለም ፤ ወንጌልን ፡ የማያውቁ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚ
መጡ ፡ ሞልተዋል ። «የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕያውነት ፡ የሚገመተው ፡
ወንጌልን ፡ በምትሰብክበት ፡ መጠን ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ በመ
ጽሐፉ ፡ ጽፎአል ።

ቀ) «ወደሚገኝ ፡ አንድነት ፡» (ቊ. ፲፪ ፡ ፲፫ ።) ሁላችን ፡ የአንዱ ፡
ድርጅት ፡ አባሎች ፡ እንድንሆን ፡ ማሰቱ ፡ አይደለም ። ሁላችን ፡ የኦር
ቶዶክስ ፡ ወይም ፡ የፕሮቴስታንት ፡ ወይም ፡ እንኳ ፡ የሮም ፡ ካቶሊክ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ እንድንሆን ፡ አይደለም ። ጕሪኖዎቹ ፡ ብዙ ፡
ይሆናሉ ፡ ናቸውም ፡ መንጋው ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ።[26] ሁላችን ፡ በእሳባ
ችን ፡ እንለያይ ፡ ይሆናል ፡ አንዳንዶችም ፡ ሰዎች ፡ ለእኛ ፡ እንግዳ ፡ ሆነው ፡
የሚታዩን ፡ እምነቶች ፡ ያሉአቸው ፡ ይመስለናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በክርስ
ቶስና ፡ እርሱ ፡ በፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ሁላችን ፡ ከታመንን ፡ አንድ ፡ ነን ።

24. ፩ቆሮ. ፬ ፡ ፯ ።
25. ዘጸአ. ፲፱ ፡ ፮ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ራእ. ፩ ፡ ፮ ፡ ፭ ፡ ፲ ።
26. ዮሐ. ፲ ፡ ፲፮ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አማኞችን ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ይጥራል ፡ ይህም ፡
ሁላቸውን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ በማቀራረብ ፡ ነው ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ ሁላችን ፡ ክርስቶስን ፡ ስናገለግል ፡ አንድ ፡ እንሆ
ናለን ።

በ) «በትምህርት ፡ ነፋስ ፡ ሁሉ ።» (ቊ. ፲፬ ።) ስንት ፡ ናቸው ፡ ዛሬ ፡
አዲስ ፡ የሚመጡብን ፡ ትምህርቶች! ከባሕር ፡ ማዶ ፡ የሚመጡ ፡ አሉ ፡
ብሔራዊም ፡ የሚሆኑ ፡ አሉ! ልንለያቸው ፡ እንችላለንን? ልንለያቸው ፡
እንድንችል ፡ የራሳችንን ፡ ሃይማኖት ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልገናል ። ከዛሬ ፡
ስሕተቶች ፡ አንዱ ፡ የራሳችንን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳናውቅ ፡ የሌላውን ፡ መቃ
ወም ፡ ነው ። በሐሰት ፡ ትምህርት ፡ ሳንታለል ፡ ከሃይማኖታችንም ፡ ሳን
ናወጥ ፡ መቆም ፡ የምንችለው ፡ ከሕፃንነት ፡ ወጥተን ፡ ሙሉ ፡ ሰዎች ፡
ስንሆን ፡ ነው ፡ ይህም ፡ የሚሆነው ፡ ሃይማኖታችን ፡ ያረፈበትን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ስናውቅ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ጥቅሱን ፡ ለመድገም ፡ መቻል ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ መጽሐፉ ፡ የሚለውን ፡ ማወቅና ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።[27]
መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ የማያውቅ ፡ ወይም ፡ በሚበቃ ፡ ያላጠናው ፡ ሰው ፡
በየትምህርት ፡ ነፋስ ፡ ሁሉ ፡ በቀላሉ ፡ ይታለላል ።

ተ) «እውነትን ፡ በፍቅር ፡ እየያዝን ።» (ቊ. ፲፭ ።) እውነትን ፡ ማወ
ቅና ፡ መያዝ ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው! ይሁን ፡ እንጂ ፡ እውነትን ፡
በማይገባ ፡ መንፈስ ፡ መያዝ ፡ ጅልነት ፡ ነው ። በጣም ፡ እርግጠኞች ፡ ብን
ሆንም ፡ እውነትን ፡ በጠንካራ ፡ ልብና ፡ በፈራጅ ፡ መንፈስ ፡ ልናስተምር ፡
ብንሞክር ፡ የሚያዳምጠን ፡ የለም ። ተቀናቃኞቻች ፡ መሆን ፡ መልካም ፡
ነው ፡ ከጥል ፡ ጋር ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ መልካም ፡ አይደለም ። እውነትን ፡ በፍ
ቅር ፡ መያዝ ፡ ያስፈልገናል ። በቊላ. ፬ ፡ ፮ና ፡ በ፩ቆሮ. ፲፫ ፡ ፪ ፡ በምሳሌም ፡
፲ ፡ ፲፪ና ፡ በ፪ጢሞ. ፪ ፡ ፳፭ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ እናስተውልና ፡ ከሐሰት ፡
ጋር ፡ ስንታገል ፡ ዘወትር ፡ በፍቅር ፡ ይሁን ።

ም. ፬ ፡ ፲፯—ም. ፭ ፡ ፳ ።

የምእመናን ፡ አዲስ ፡ አመላለስና ፡ አነጋገር ። ቊ. ፲፯—፴፪ ።

፲፯ ፤ እንግዲህ ፡ አሕዛብ ፡ ዶግሞ ፡ በአእምሮአቸው ፡ ከንቱነት ፡
እንደሚመላለሱ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳትመላለሱ ፡
፲፰ ፤ አላለሁ ፡ በጌታም ፡ ሆኜ ፡ እመሰክራለሁ ። እነርሱ ፡ ባለ
ማወቃቸው ፡ ጠንቅ ፡ በልባቸውም ፡ ደንዳንነት ፡ ጠንቅ ፡
ልቡናቸው ፡ ጨለመ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ሕይወት ፡ ራቁ ፤
፲፱ ፤ ደንዝዘውም ፡ በመመንት ፡ ርኵሰትን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡
ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ሴሰኝነት ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡ ። እና

27. ፪ተሰ. ፪ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ፭ ። ፪ጢሞ. ፫ ፡ ፲፫—፲፮ ።

ኛ ፤ ንት ፡ ግን ፡ ከርስቶስን ፡ እንደዚህ ፡ አልተማራችሁም ፤
ኛ፩ ፤ በእርግጥ ፡ ሰምታችሁታልና ፡ እውነትም ፡ በኢየሱስ ፡ እን
ኛ፪ ፤ ዳሰ ፡ በእርሱ ፡ ተምራችኋል ፤ ፊተኛ ፡ ኑሮአችሁን ፡ እያሰ
ባችሁ ፡ እንደሚያታልል ፡ ምኞት ፡ የሚያጠፋውን ፡ አሮ
ጌውን ፡ ሰው ፡ አስወግዱ ፡ በአእምሮአችሁም ፡ መንፈስ ፡
ኛ፫ ፤ ታደሱ ፡ ለእውነትም ፡ በሚሆኑ ፡ ጽድቅና ፡ ቅድስና ፡ እንደ ፡
ኛ፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረውን ፡ አዲሱን ፡ ሰው ፡
ኛ፭ ፤ ልበሱ ። ስለዚህ ፡ ውሸትን ፡ አስወግዳችሁ ፡ እርስ ፡ በርሳ
ችን ፡ ብልቶች ፡ ሆነናልና ፡ እያንዳንዳችሁ ፡ ከባልንጀሮቻ
ኛ፮ ፤ ችሁ ፡ ጋር ፡ እውነትን ፡ ተነጋገሩ ። ተቈጡ ፡ ኃጢአትንም ፡
ኛ፯ ፤ አታድርጉ ፤ በቍጣችሁ ፡ ላይ ፡ ጸሐይ ፡ አይግባ ፡ ለዲያብ
ኛ፰ ፤ ሎስም ፡ ፋንታ ፡ አትስጡት ። የሰረቀ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
አይስረቅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ፈንታ ፡ ለጐደለው ፡ የሚያ
ካፍለው ፡ እንዲኖርለት ፡ ከገዛ ፡ እጆቹ ፡ መልካምን ፡ እየ
ኛ፱ ፤ ሠራ ፡ ይድከም ። ለሚሰሙት ፡ ጸጋን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ እን
ደሚያስፈልግ ፡ ለማነጽ ፡ የሚጠቅም ፡ ማናቸውም ፡ በጎ ፡
ቃል ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ ከአፋችሁ ፡ ከቶ ፡ አይውጣ ።
ፃ ፤ ለቤዛም ፡ ቀን ፡ የታተማችሁበትን ፡ ቅዱሱን ፡ የእግዚአ
ፃ፩ ፤ ብሔርን ፡ መንፈስ ፡ አታሳዝኑ ። መራርነትና ፡ ንዴት ፡
ቍጣም ፡ ጩኸትም ፡ መሳደብም ፡ ሁሉ ፡ ከክፋት ፡ ሁሉ ፡
ፃ፪ ፤ ጋር ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይወገድ ። እርስ ፡ በርሳችሁም ፡ ቸሮ
ችና ፡ ርኅሩኆች ፡ ሁኑ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በክርስ
ቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ ።

እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ መጠራት ፡ ከተጠራችሁና ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ከርስቶስ ፡ ማደግ ፡ ካለባችሁ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ አመላለስ ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ አይገባችሁም ፡ እነርሱ ፡ በአእምሮአቸው ፡ ከንቱነት ፡ ይመላለሳሉ ። እግዚአብሔርን ፡ አያውቁ
ምና ፡ እንዳያውቁትም ፡ ልባቸውን ፡ አደንድነዋልና ፡ ልቡናቸው ፡
ጨለመ ።[28] እውነተኛ ፡ ሕይወት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ ነውና ፤[29] እን
ርሱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላወቁምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡
ከወቀደው ፡ ሕይወት ፡ ራቁ ፤ ጫማ ፡ የማያደርግ ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡ መር
ገጥ ፡ እስከሚችል ፡ ድረስ ፡ እግሩ ፡ ጠንካራ ፡ እንደሚሆን ፡ ሁሉ ፡ እን
ዲሁም ፡ አሕዛብ ፡ በኃጢአት ፡ በመመላለሳቸውና ፡ ኃጢአትን ፡ በማዘ
ውተራቸው ፡ የማይሰማቸው ፡ ጠንካራዎች ፡ ሆኑና ፤[30] በፍትወት ፡ እየተ
ነዱ ፡ ርኵሰትን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ራሳቸውን ፡ አሳ
ልፈው ፡ ሰጡ ።[31]

---

28. ሮሜ ፡ ፩ ፤ ፲፩—፲፫ ፡ ፳፭ ። 29. ዮሐ. ፲፯ ፡ ፫ ። 30. ፩ጢሞ. ፬ ፡ ፪ ።
31. ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፴፪ ።

እናንተ ፡ ግን ፡ ከእነርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ልዩ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ። እና
ንተ ፡ ተምራችኋል ፡ እውቃችሁማል ። «ምኑን ፡ ተምረናል?» ብትሉም ፡
ክርስቶስን ፡ ተምራችኋል! ሰምታችሁት ፡ የለምን?[32] እነርሱ ፡ አላወቁም ፡
እናንተ ፡ ግን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቹ ፡ ሆናችኋል ፡ እውነት ፡ በኢየሱስ ፡
እንዳለ ፡ ትእዛዙንም ፡ ተምራችኋል ።[33] እንግዲያውስ ፡ ከተማራችሁ ፡
በፊት ፡ ትኖሩበት ፡ የነበረውን ፡ ኑሮአችሁን ፡ እያሰባችሁ ፤[34] ያን ፡ ጊዜ ፡
የነበራችሁበትን ፡ እንደሚያታልል ፡ ምኞት ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡
የሚደርሰውን ፡ አሮጌውን ፡ ሰው ፡ አስወግዱም ።[35] ድሮ ፡ አእምሮአችሁ ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የአእምሮአችሁ ፡ መንፈስ ፡ እንኳ ፡ ከንቱ ፡ ነበረ ፡ ርኩ
ሰትንም ፡ ሁሉ ፡ ታደርጉ ፡ ነበር ።[36] አሁን ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሠ
ራር ፡ በአእምሮአችሁ ፡ መንፈስ ፡ ታደሱና ፤[37] በኢየሱስ ፡ ከተማራችሁት ፡
ከእውነት ፡ በሚመነጨ ፡ በጽድቅና ፡ በቅድስና ፡ አዲስ ፡ ፍጥረቶች ፡
ሆናችሁ ፤[38] እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልክና ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረውን ፡
አዲሱን ፡ ሰው ፡ ልበሱ ።

አሮጌውን ፡ ማውለቅ ፡ አዲሱንም ፡ መልበስ ፡ አለብንና ፡ ሐዋርያው ፡ አሁን ፡ ከቍ
ፅ፭ ፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ም. ፭ ፡ ፭ ፡ ድረስ ፡ ማውለቅና ፡ መልበስ ፡ የሚገባንን ፡ ነገር ፡ ዘር
ዝር ፡ ያስረዳል ። ማውለቅም ፡ የሚገባን ፡ መጀመሪያው ፡ ነገር ፡ ውሸት ፡ መናገርን ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ ከርስቲያኖች ፡ በእንድ ፡ አካል ፡ ውስጥ ፡ የም
ትገኙ ፡ አካላት ፡ (ብልቶች ፡) ናችሁና ፡ እንዳትጐዱ ፡ እንዳትጐዳዱም ፤[39]
ውሸትን ፡ ማስወገድና ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በእውነት ፡ መኖርንና ፡ እው
ነት ፡ መናገርን ፡ መልበስ ፡ አለባችሁ ። ትቈጡም ፡ እንደሆነ ፡ ኃጢአትን ፡
እንዳታደርጉ ፡ ተጠንቀቁ ። የቈየ ፡ ቍጣ ፡ ለዲያብሎስ ፡ መግቢያ ፡ መን
ገድን ፡ ይሰጣልና ፡ ሳይመሽ ፡ ታረቁ ። ስርቆትንም ፡ አስወግዱ ፤ የዛሬ ፡
መንፈሳችን ፡ የመጠቀም ፡ መንፈስ ፡ ሳይሆን ፡ የመጥቀም ፡ መንፈስ ፡
ነውና ፡ ከርስቲያን ፡ ስርቆት ፡ የሚመስለውን ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ አሁን ፡
አይሥራ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለጐደለበት ፡ ሊሰጥ ፡ እንዲችል ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳ
ደረገው ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያን ፡ በገዛ ፡ እጆቹ ፡ መልካምን ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡
ይድከም ።[40] መጥፎ ፡ ንግግርም ፡ ማለት ፡ ግም ፡ ቃል ፡ ከክርስቲያን ፡ አፍ ፡
አይውጣ ። ማስወገድ ፡ አለበት ። ሰውን ፡ በሚያጠፋ ፡ አስቀያሚ ፡ ቃል ፡
ሳይሆን ፡ ለሰሚው ፡ ጸጋን ፡ በሚሰጥና ፡ ለየጊዜው ፡ እንደሚያስፈልግ ፡
ሁሉ ፡ ሊያንጽ ፡ በሚጠቅም ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ።[41] በንግግራችሁ ፡ በውስ
ጣችሁ ፡ የሚኖረውንና ፡ እስከ ፡ ፍጹም ፡ መዳን ፡ ቀን ፡ የሚጠብቀንን ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አታስቀይሙ ፡ አታሳዝኑም ። የበጉ ፡ ፈቃድ ፡ ተቃ

---

32. ኤፌ. ፫ ፡ ፪ ። 33. ዮሐ. ፲፬ ፡ ፯ ። ማቴ. ፳፰ ፡ ፲፱ ። 34. ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፲፰ ።
35. ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ። 36. ቈላ. ፫ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ቍ. ፲፯—፲፱ ። 37. ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ።
38. ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፲፯ ። 39. ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፳፭ ። 40. ፩ተሰ. ፪ ፡ ፱ ። ፪ተሰ. ፫ ፡ ፰ ።
፩ቆሮ. ፬ ፡ ፲፪ ። 41. ሉቃ. ፩ ፡ ፷፪ ። ምሳሌ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ።

ራኒ ፡ የሆነውን ፡ መራርነት ፡ በድንገት ፡ የሚነሣውን ፡ ንዴት ፡[42] በልባችን ፡ የሚፈላውን ፡ ቊጣ ፡ ሰዎች ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ የምንሰማውን ፡ ጩኸት ፡ መሳደብን ፡ ሁሉ ፡ ከፉትንም ፡ በየዓይነቱ ፡ ፈጽሞ ፡ አስወግዱ ። እነዚህን ፡ አስወግዳችሁ ፡ ቸርነትንና ፡ እንጀተ ፡ ርኅሩኅነትን ፡ ልበሱ ። እግዚአብሔርም ፡ በክርስቶስ ፡ በኩል ፡[43] ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ ብሎ ፡ እናንተን ፡ ይቅር ፡ እንዳለ ፡ ሁሉ ፡ እናንተም ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «በአእምሮአቸው ፡ ከንቱነት ።» (ቊ. ፲፯ ።) እግዚአብሔርን ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ሕይወቱ ፡ በከንቱነት ፡ ይሞላል ። አሕዛብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳያውቁ ፡ የማይረቡ ፡ ጣዖታትን ፡ ሲያመልኩ ፡ ራሳቸው ፡ በአእምሮአቸው ፡ ከንቱ ፡ ሆኑ ።[44] መጽሐፈ ፡ መክብብን ፡ የደረሰው ፡ ሰባኪ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይኸው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ የሌለበት ፡ ሕይወት ፡ «ከንቱ ፡ ከንቱ ፡ የከንቱ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ያለ ፡ ነው ፡» ይላል ።[45] እግዚአብሔርንም ፡ አለማወቅ ፡ ወደ ፡ ተበላሸ ፡ ጠባይ ፡ ወደ ፡ ሞራል ፡ ጥፋት ፡ ያደርሳል ። (ቊ. ፲፱ ።) «እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ አልፈልግም ፡» ያሰውን ፡ ሰው ፡ ተመልከቱ ። አእምሮው ፡ ይጨልማል ፡ በጨለማም ፡ ይመላለሳል ፡ ኑሮውም ፡ የኃጢአት ፡ ይሆናል ።

ለ) «በጌታ ፡ ሆኜ ፡ እመሰክራለሁ ።» (ቊ. ፲፯ ።) «በጌታ ፡ ሆኜ ፡» ማለት ፡ «በጌታ ፡ አፍ ፡ በጌታም ፡ ስም ፡» እናገራለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ የሚለው ፡ ቃሉን ፡ ሊያጸና ፡ ነው ።

ሐ) «እንደሚያታልል ፡ ምኞት ፡ የሚጠፋውን ፡ አሮጌውን ፡ ሰው ፡ አስወግድ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረውን ፡ አዲሱን ፡ ሰው ፡ ልበሱ ።» (ቊ. ፳፪ ፡ ፳፬ ።) አሮጌው ፡ ሰው ፡ እኛ ፡ ክርስቶስን ፡ ከማወቃችን ፡ በፊት ፡ የነበርንው ፡ ነው ፤ አዲሱም ፡ ሰው ፡ ክርስቶስን ፡ ከማወቃችን ፡ ወዲህ ፡ የሆነው ፡ ነው ። ያን ፡ ነበርን ፡ ይህን ፡ ሆንን ። ያን ፡ ማስወገድ ፡ ይህንም ፡ መልበስ ፡ አስብን ። ምኞት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አታላይ ፡ ነው ። ጥጋብን ፡ ደስታንም ፡ የሚሰጠን ፡ ሲነግረን ፡ ወደ ፡ ጥፋትና ፡ ወደ ፡ ጎዘን ፡ ያደርሳል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ድሮ ፡ ምኞት ፡ እያታለለን ፡ እንደ ፡ መሄዱ ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እናመራ ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ክርስቶስን ፡ ከተማርን ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረውን ፡ አዲሱን ፡ ሰው ፡ (እኛ ፡ አዲስ ፡ ተፈጥረናል ፡)[46] ለብሰን ፡ በጽድቅና ፡ በቅድስና ፡ እንደ ፡ መሄዳችን ፡ መጠን ፡ ወደዚያ ፡ ምሳሌ ፡ እናመራለን ።

መ) «ውሸትን ፡ አስወግዳችሁ ።» (ቊ. ፳፭ ።) ማንኛውም ፡ ውሸት ፡ ሁሉ ፡ የሚመጣው ፡ ከሐሰት ፡ አባት ፡ ከዲያብሎስ ፡ ነውና ፡ መጥፎ ፡

42. ሉቃ. ፮ ፡ ፳፰ ። የሐዋ. ፲፱ ፡ ፳፰ ። 43. ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፲፱ ። 44. ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፰ ። መዝ. ፩፻፲፫ ፡ ፲፮—፲፯ ። 45. መክ. ፩ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ። 46. ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፲፯ ። ኤፌ. ፪ ፡ ፲ ።

ነው ።[47] መልካም ፡ ውሸት ፡ የለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ውሸትን ፡ መናገር ፡ ምንኛ ፡ ቀላል ፡ ነው! ባሎች ፡ ከሚስቶቻቸውና ፡ ሚስቶች ፡ ከባሎቻቸው ፡ ጋር ፡ ሲናገሩ ፡ ፪ ፡ ባልንጀሮች ፡ በመንገድ ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ ስባኪያን ፡ ስብከታቸውን ፡ ሲሰብኩ ፡ ውሸትን ፡ መናገር ፡ ምንኛ ፡ ቀላል ፡ ነው! አይደለምን? «መቸም ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ማታለል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡» እንላለን ። ተገቢ ፡ መልስ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ «ምን ፡ ያህል ፡ አገለገልህ ፡ ሲባል ፡ «፮!» እንላለን ። ውሸት ፡ ነው ። «ይህንስ ፡ ለምን ፡ እደረጋችሁ ፡?» ሲባልም ፡ «አላደረግንም!» እንላለን ፡ ውሸት ፡ ነው ። «እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መከርሁት» ብለናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ብሰን ፡ አል መከርነውም ። ባልንጀሮች ፡ እካላት ፡ (ብልቶች) ከሆኑት ፡ ከርስቲያኖች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ (በእንድነት ፡) ልንኖር ፡ ብንወድ ፡ ውሸት ፡ አስወግደን ፡ በተማራ ፡ እምነት ፡ መኖር ፡ ያሻናል ።[48] ውሸት ፡ አንድነትን ፡ ያጠፋልና ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነተኞች ፡ ያልሆንን ፡ እንደሆነ ፡ ሞላ ፡ ማኅበሩ ፡ ይሸበራል ። ሐዋርያው ፡ «ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እውነትን ፡ እንናገር» ይላል ። አንድነትን ፡ የሚያጠፋ ፡ ዋነኛው ፡ ነገር ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እውነትን ፡ አለመናገራችን ፡ ነውና ፡ ውሸትን ፡ እናስወግድ ።

ሠ) «ተቈጡ ፡ ኃጢአትንም ፡ አታድርጉ ።» (ቊ. ፳፮ ።) «ተቈጡ ፡» ማለቱን ፡ እንጂ ፡ «እተቈጡ» አለማለቱን ፡ እናስተውል ። ቊጣ ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ሊያደርስ ፡ ይችላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ ኃጢአት ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ ይቈጣል ፡[49] ክርስቶስም ፡ ተቈጥቶአል ፡[50] ሐዋርያትም ፡ ተቈጥተዋል ።[51] በራሳችን ፡ ምክንያት ፡ ማለት ፡ ራሳችን ፡ ስለ ፡ ተነካን ፡ ሰውም ፡ እኛን ፡ ስለ ፡ በደለ ፡ አንቈጣ ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚቈጣበት ፡ ሁሉ ፡ ልንቈጣ ፡ አንችልምን ። ሐዋርያው ፡ በመዝ. ፬ ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የዳዊትን ፡ ቃል ፡ የሚጠቅስ ፡ ይመስላል ። እየጠቀሰም ፡ «ተቈጡ» ይላል ፡ «ነገር ፡ ግን ፡ በቊጣችሁ ፡ አትደሩ» ፤ ምክንያቱም ፡ ፭ኛ ፡ የተያዘ ፡ ቊጣ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ መሥራት ፡ ሳያደርስ ፡ አይቀርምና ፤ ፪ኛ ፡ ዛሬ ፡ ያልታረቅን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዛሬ ፡ ይልቅ ፡ ነገ ፡ መታረቅ ፡ ይበልጡን ፡ ያስቸግራል ። ጌታም ፡ በማቴ. ፭ ፡ ፳፪ ፡ ላይ ፡ «በወንድሙ ፡ ላይ ፡ የሚቈጣ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ይገባዋል ፡» ሲል ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እናስብ ።

ረ) «የሰረቀ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይስረቅ ።» (ቊ. ፳፰ ።) ከርስቲያን ፡ ይሰርቃልን? አይሰርቅም ! እውነት ፡ ነው ፡ ከርስቲያኖች ፡ ነንና ፡ አንሰርቅም ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በሚታመንብን ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ጥርጥር ፡ ቢነሣ ፡ ቶሎም ፡ ይነሣል ፡ ያስነቅፋልና ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልገናል ።[52] በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የተቀ

47. ዮሐ. ፰ ፡ ፵፬ ። 48. ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። ዘካ. ፰ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ሉቃ. ፲፩ ፡ ፴፮ ። 49. ዘዳግ. ፩ ፡ ፴፮ ። ፩ነገ. ፲፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ኢሳ. ፭ ፡ ፳፭ ። 50. ማር. ፫ ፡ ፭ ። ዮሐ. ፪ ፡ ፲፫—፲፯ ። 51. ፪ቆሮ. ፲፩ ፡ ፳፱ ። 52. ፪ቆሮ. ፰ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

መጠው ፡ የእደራ ፡ ገንዘብ ፡ የእኛ ፡ አለመሆኑን ፡ ዘወትር ፡ እናስታውስ ።
እረ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ «የሰረቀ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይስረቅ ፡» ተብ
ሎአልና ፡ በሌላም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሆነ ፡ በመንግሥት ፡ እንጠንቀቅ!

ሰ) «ለማነጽ ፡ የሚጠቅም ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ ከአፋችሁ ፡ ከቶ ፡
አይውጣ ።» (ቊ. ፳፱ ።) በእንዲህ ፡ ያለ ፡ መጠራት ፡ ከተጠራንና ፡ በነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ማደግ ፡ ካለብን ፡ መጥፎ ፡ ማድረግን ፡ ብቻ ፡
ሳይሆን ፡ መጥፎ ፡ መናገርን ፡ ጭምር ፡ ማስወገድ ፡ ይኖርብናል ። «ክፉ»
ቃል ፡ ማለት ፡ ግም ፡ ቃል ፡ ነው ፡ በእርሱም ፡ ተጠቅልለው ፡ ርኵስና ፡
ብላሽ ፡ ንግግር ፡ መራገምም ፡ ሁሉ ፡ ይገኛሉ ። ሐዋርያውም ፡ «ከቶ ፡ አይ
ውጣ» ይላል ። ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ቢገኝበት ፡ አይከፋም ፡ እንደ ፡ ማለት ፡
ሳይሆን ፡ ከቶ ፡ አይገኝም ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ግም ፡ ንግግርን ፡ መልመድ ፡
መጥፎ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ከክርስትና ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ነው ፡ ለክርስቲ
ያንም ፡ የማይገባ ፡ ነው ። እንሽሽውና ፡ ርኵሰት ፡ በጨው ፡ እንደሚከ
ለከል ፡ ሥጋም ፡ በጨው ፡ እንደሚጣፍጥ ፡ እንዲሁም ፡ ንግግራችን ፡ ከግ
ምነት ፡ ሁሉ ፡ በጸጋ ፡ ተጠብቆ ፡ በጸጋ ፡ የጣፈጠ ፡ ይሁን ።[53] ያ ፡ ግም ፡ ንግ
ግር ፡ ያዋርዳል ፡ ያፈርሳልም ፡ የጸጋ ፡ ንግግር ፡ ግን ፡ የሚሰሙትን ፡ ያን
ጻል ። የእኛ ፡ ንግግርስ? ያዋርዳል ፡ ወይስ ፡ ያንጻል? ጌታ ፡ «ከቃልህ ፡ የተ
ነሣ ፡ ትኰነናለህ ፡» ብሎአል ።[54]

ሸ) «ለቤዛ ፡ ቀን ፡ የታተማችሁበት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።» (ቊ. ፴ ።)
«የቤዛ ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ ነው?» ቢሉ ፡ ልጅነትን ፡ ተቀብለን ፡ ሰውነታችን ፡
የሚታደስበትና ፡ ርስታችንን ፡ የምንቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የዳግም ፡
ምጽዓት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።[55] «ማኅተምስ ፡ ምንድር ፡ ነው?» ቢሉ ፡ ማኅተምማ ፡
በእመንበት ፡ ጊዜ ፡ የታተምንበት ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማኅተም ፡ ነው ፡
የክርስቶስ ፡ ለመሆናችን ፡ ምልክት ፡ ነበረ ።[56] በዚያ ፡ ማኅተም ፡ ታትመን ፡
ሳለን ፡ ማንኛውም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሊያገኘን ፡ አይችልም ፡ እስከዚያም ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ በደኅንነት ፡ እንጠበቃለን ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከሥላሴ ፡
አንድ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ያዝናል ። እርሱንም ፡ በአድራጎታ
ችንም ፡ ሆነ ፡ በንግግራችን ፡ ማሳዘን ፡ አይገባንም ።

ቀ) «እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ፡ ይቅር ፡ ተባ
ባሉ ።» (ቊ. ፴፪ ።) ለካ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ ብሎናል!
ግሡ ፡ የሚጠራው ፡ በኀላፊ ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ ይቅርታው ፡ የተደረገ ፡ የሆ
ነም ፡ ነገር ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ኃጢአታችንን ፡ ሁሉ ፡ ታላቁንም ፡
ታናሹንም ፡ ይቅር ፡ ብሎአል ።[57] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይቅር ፡ ያለው ፡ በምን ፡
ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንገንዘብ ። እኛ ፡ መልካም ፡ ሰዎች ፡ በመሆና
ችን ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ በመሥራታችን ፡ እይደለም ። መልካም ፡

53. ቈላ. ፬ ፡ ፮ ። 54. ማቴ. ፲፪ ፡ ፴፯ ። 55. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፫ ።
56. ኤፌ. ፩ ፡ ፲፫ ። 57. መዝ. ፻፳፱ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

ሥራ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።[58] እግዚአብ
ሔር ፡ ይቅር ፡ ያለን ፡ በክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ምክንያትና ፡ ስለ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ብሎ ፡ በክርስቶስም ፡ በዙል ፡ ነው ።[59] እንግዲያውስ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያን ፡ ኃጢአታችንን ፡ ሁሉ ፡ ካሳለፈ ፡ እኛን ፡ የበደለ ፡ የወንድማችን ፡
ወይም ፡ እንኳ ፡ የጠላታችን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው? ሐዋርያው ፡ «እግዚ
አብሔር ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ»
ይላል ። ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ስንፈጽም ፡ እንገኛለንን?

58. ሉቃ. ፲፯ ፡ ፯—፲ ። 59. ፩ዮሐ. ፪ ፡ ፲፪ ።

ምዕራፍ ፡ አምስት ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ከቁ. ፩ ፡ እንሥቶ ፡ እስከ ፡ ቁ. ፳ ፡ ድረስ ፡ የምናገኘው ፡ ባለፈው ፡ ክፍል ፡ ማለት ፡ በም. ፬ ፡ ፲፯—፴፪ ፡ ድረስ ፡ እን ዳገኘነው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ። የክርስቶስ ፡ ከሆንን ፡ የተለየን ፡ ሰዎች ፡ (ቅዱሳን ፡) ሆነን ፡ መኖር ፡ ያስፈልገናል ፡ እንጂ ፡ ከኃጢአት ፡ (ከጨለማ ፡) ዓለም ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ ተባብረን ፡ መኖር ፡ እንችልም ። የጨለማውን ፡ ሥራ ፡ አውጥተን ፡ የብርሃንን ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ መልበስ ፡ አስፈላጊያችን ፡ ነው ። (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ።) ክፍሉ ፡ የሚያስተምረን ፡ ምእመናን ፡ እንደ ፡ ተወ ደዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ በፍቅር ፡ መኖር ፡ ርኵስትን ፡ ሁሉ ፡ ጠል ተው ፡ በንጽሕና ፡ መኖር ፡ ከጨለማ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ሳይተባበሩ ፡ በብር ሃን ፡ መኖር ፡ ጥበብ ፡ እንደሌላቸው ፡ ሳይሆኑ ፡ የጌታን ፡ ፈቃድ ፡ አስ ተውለው ፡ ደስ ፡ እያሰኙት ፡ መኖር ፡ በዓለም ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መኖር ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ቀጥሎም ፡ ከቁ. ፳፩ ፡ እንሥቶ ፡ እስከ ፡ ም. ፮ ቁ. ፱ ፡ ድረስ ፡ ሐዋር ያው ፡ ከርስቲያኖች ፡ ከሆንን ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ በግል ፡ ግንኙነታችን ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ መገዛት ፡ እንደሚገባን ፡ ይነግረናል ።

ቁ. ፩ — ፳ ።

የምእመናን ፡ አዲስ ፡ አመላለስና ፡ አነጋገር ። (ተቀጣይ ።)

፩ ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ተወደዱ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡

፪ ፤ የምትከተሉ ፡ ሁኑ ፡ ከርስቶስም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ወደዳ ችሁ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ የመዓዛ ፡ ሽታ ፡ የሚሆንን ፡ መባንና ፡ መሥዋዕትን ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በፍቅር ፡ ተመላለሱ ።

፫ ፤ ለቅዱሳን ፡ እንደሚገባ ፡ ግን ፡ ዝሙትና ፡ ርኵስት ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ መመኘት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አይሰማ ፤

፬ ፤ የሚያሳፍር ፡ ነገርም ፡ የስንፍና ፡ ንግግርም ፡ ወይም ፡ ዋዛ ፡ የማይገቡ ፡ ናቸውና ፡ አይሁኑ ፡ ይልቁን ፡ ምስጋና ፡ እንጂ ።

፭ ፤ ይህን ፡ እወቁ ፤ አመንዝራም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ርኵስ ፡ ወይም ፡ የሚመኝ ፡ እርሱም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልክ ፡ በክ ርስቶስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ርስት ፡ የለውም ።

፮ ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ በማይታዘዙት ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ቊጣ ፡ ይመጣልና ፡ ማንም ፡ በከንቱ ፡ ንግግር ፡ አያ ታልላችሁ ።

፯ ፤ ፰ እንግዲህ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተካፋዮች ፡ አትሁኑ ፤ ቀድሞ ፡ ጨለማ ፡ ነበራችሁና ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በጌታ ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ።

፰፣፱፤ የብርሃኑ ፡ ፍሬ ፡ በበጎነትና ፡ በጽድቅ ፡ በእውነትም ፡ ሁሉ ፡ ነውና ፡ ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ እየመረመራችሁ ፡

፲፩ ፤ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ልጆች ፡ ተመላለሱ ፤ ፍሬም ፡ ከሌለው ፡ ከጨለማ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ አትተባበሩ ፡ ይልቁን ፡ ግን ፡ ግለ

፲፪ ፤ ጡት ፡ እነርሱ ፡ በስውር ፡ ስለሚያደርጉት ፡ መናገር ፡

፲፫ ፤ እንኳ ፡ ነውር ፡ ነውና ፤ ሁሉ ፡ ግን ፡ በብርሃን ፡ ሲገለጥ ፡

፲፬ ፤ ይታያል ፤ የሚታየው ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ነውና ። ስለዚህ ፡— አንተ ፡ የምትተኛ ፡ ንቃ ፡ ከሙታንም ፡ ተነሣ ፡ ክርስቶስም ፡ ያበራልሃል ፡ ይላል ።

፲፭ ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ጥበበኞች ፡ እንጂ ፡ ጥበብ ፡ እንደሌላ ቸው ፡ ሳይሆን ፡ እንዴት ፡ እንድትመላለሱ ፡ በጥንቃቄ ፡

፲፮ ፤ ተጠበቁ ፤ ቀኖቹ ፡ ከፉዎች ፡ ናቸውና ፡ ዘመኑን ፡ ዋጁ ።

፲፯ ፤ ስለዚህ ፡ የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተውሉ ፡

፲፰ ፤ እንጂ ፡ ሞኞች ፡ አትሁኑ ። መንፈስ ፡ ይሙላባችሁ ፡ እንጂ ፡

፲፱ ፤ በወይን ፡ ጠጅ ፡ አትስከሩ ፡ ይህ ፡ ማባከን ፡ ነውና ፤ በመ ዝሙርና ፡ በዝማሬ ፡ በመንፈሳዊም ፡ ቅኔ ፡ እርስ ፡ በር ሳችሁ ፡ ተነጋገሩ ፤ ለጌታ ፡ በልባችሁ ፡ ተቀኙና ፡ ዘምሩ ፤

፳ ፤ ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እምላካችንንና ፡ አባታችንን ፡ አመስግኑ ።

እንግዲያውስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከተወለዳችሁ ፡ እባታችሁን ፡ ምሰሉ ፡ [1] ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ወደዳችሁና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መባና ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲሆን ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አሳ ልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ እናንተም ፡ በፍቅር ፡ ተመላለሱ ።

በፍቅር ፡ ተመላለሱ ፡ እንጂ ፡ «እንድ ፡ ወንድ ፡ ላንዲት ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡» የሚለውን ፡ ሕግ ፡ የሚያፈርስ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከፍጹም ፡ ንጽሕናም ፡ ያልሆነው ፡ ነገር ፡ መጥፎ ፡ መመኘትም ፡ በመካከላችሁ ፡ ከቶ ፡ አይጠቀስ ፡ እትነጋገሩበትም ፡ ለቅዱሳን ፡ የማይገባ ፡ ነውና ። እንደዚሁም ፡ ቅዱሳን ፡ ሰው ፡ የሚያሳፍር ፡ ወይም ፡ የሚያዋርድ ፡ ነገር ፡ ያሉባልታ ፡ ቃል ፡ ቅሌትም ፡ ለቅዱሳን ፡ የማይገቡ ፡ ናቸውና ፡ አይ ሁኑ ። ከዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ንግግር ፡ ምስጋና ፡ የተሻለ ፡ ነው ። እርግጠኞች ፡ ሁኑ ፡ እንጂ ፡ አትሳቱ ፤ እነኝህ ፡ ቃቱ ፡ ነገሮች ፡ ማለት ፡ ምንዝርነትና ፡ ርኵሰት ፡ መመኘትም ፡ [2] የክርስቶስንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የእንዱን ፡ አምላክ ፡ መንግሥት ፡ [3] ከመውረስ ፡ ይከለክላሉ ። [4] ከዚህ ፡ ርኵሰት ፡ የተነሣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቊጣ ፡ በማይታዘዙቱ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ይመ ጣልና ፡ «ሞትንስ ፡ አትሞቱም !» [5] ወይም ፡ «እጋ ፡ ኃጢአትን ፡ ሁሉ ፡

1. ፩ቆሮ. ፲፩ ፡ ፩ ። ፪ሮሜ. ፲፪ ፡ ፩ ። ፫ዮሐ. ፫ ፡ ፩ ። ፬ይሁዳ ፡ ቁ. ፬ ። ፭ዕብ. ፲፫ ፡ ፭ ።
2. ግቴ. ፭ ፡ ፭፰ ። ፫. ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ፬ኤፋ. ፭ ፡ ፭ ። ፭ገላ. ፭ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ፮ገላ. ፩ ፡ ፲፱—፳፩ ።
3. ዘፍጥ. ፫ ፡ ፱ ።

ይሸፍን ፡ የለምን ?» [6] ከሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ከንቱ ፡ ንግግር ፡ ተጠበቁ ፡ አታ
ላዮች ፡ ናቸውና ። እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ከእነዚህ ፡ ሰዎች ፡
ጋር ፡ ተካፋዮች ፡ አትሁኑ ፤ [7] ምክንያቱም ፡ ቀድሞ ፡ እናንተ ፡ በጨለማ ፡
ውስጥ ፡ መሆናችሁ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ራሱ ፡ ጨለማ ፡ ነበራችሁ ፡ አሁን ፡
ግን ፡ በጌታ ፡ ከሆናችሁ ፡ ወዲህ ፡ ማለት ፡ ወንጌልን ፡ ሰምታችሁ ፡ ክር
ስቶስን ፡ ከተቀበላችሁ ፡ ወዲህ ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ። ከብርሃን ፡ የሚወ
ጣው ፡ ብርሃን ፡ የሚያፈራው ፡ በጎነትንና ፡ ቅንነትን ፡ እውነትንም ፡ የመ
ሰለ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ «ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ምንድር ፡
ነው?» ብላችሁ ፡ እየመረማችሁና ፡ [8] እነዚህን ፡ ፍሬዎች ፡ እያፈራችሁ ፡
እንደ ፡ ብርሃን ፡ ልጆች ፡ ተመላለሱ ። እንጂ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ከሆነ ፡ ከጨ
ለማ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ አትተባበሩ ። [9] ከጨለማ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ አለመተባ
በርም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በእንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ሲበራ ፡
ጨለማ ፡ እንደሚጠፋና ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገለጥ ፡
እንዲሁም ፡ እናንተ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ የሆናችሁ ፡ የብርሃን ፡ ልጆች [10] ፡
የጨለማን ፡ ሥራ ፡ በብርሃናችሁ ፡ ብትገልጡ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። እነርሱ ፡
ሥራቸው ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ በስውር ፡ በጨለማ ፡ ይሸሸጋሉ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡
ብርሃን ፡ አይመጡም ። [11] እነርሱም ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ሥራ ፡ መናገር ፡
እንኳ ፡ ነውር ፡ ነው ። ለብርሃናት ፡ እንደሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ ብት
ገልጡ ፡ ግን ፡ ከሰዋራው ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣል ፡ ጨለማ ፡ የነ
በረውም ፡ ብርሃን ፡ ይሆናል ፡ ስለዚህ ፡ መዝሙሩ ፡

«እንተ ፡ በጨለማ ፡ የምትተኛ ፡ ሆይ ፡ ንቃ ፡
ከሙታንም ፡ ቦታ ፡ ተነሣ ፡
ክርስቶስም ፡ ብርሃንን ፡ በላይህ ፡ ላይ ፡ ያበራልሃል ፡»

ይላል ።

እንግዲህ ፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ መሆናችሁ ፡ መጠን ፡ በጨ
ለማ ፡ እንዳሉቱ ፡ ሳይሆን ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ በራላቸው ፡ ሰዎች ፡ [12] እንደ ፡
ጥበበኞች ፡ አረማመዳችሁን ፡ በሰዎች ፡ ፊት ፡ በጥንቃቄ ፡ ጠብቁ ። ቀኖቹ ፡
በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰበብ ፡ ምክንያት ፡ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፡ ሰዓታች
ሁን ፡ እየተቈጣጠራችሁ ፡ ኑሩ ። ስለዚህ ፡ ልብና ፡ ግብ ፡ እንደሌላቸው ፡
ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እንደሚንከራተቱት ፡ ሞኞች ፡ ሳትሆኑ ፡ የጌታ ፡ ፈቃድ ፡
ምን ፡ እንደሆነ ፡ እያስተዋላችሁ ፡ በእርጋታ ፡ ሂዱ ። ሞኞቹ ፡ የወይን ፡
ጠጅ ፡ ሲሞላባቸው ፡ ሕይወትና ፡ ደስታን ፡ የሚያገኙ ፡ ይመስላቸዋል ፡
እርሱም ፡ ራስንና ፡ ንብረትን ፡ ማባከን ፡ ነው ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ተሞልቶባችሁ ፡ ኑሩ ። እናንተም ፡ ደስታችሁን ፡ ስትገልጡ ፡

6. ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፩ ። 7. ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፴፪ ። 8. ዮሐ. ፰ ፡ ፳፱ ።
9. ፪ቆሮ. ፮ ፡ ፲፩—፲፰ ። 10. ማቴ. ፩ ፡ ፲፱ ። ፩ዮሐ. ፩ ፡ ፪ ፡ ፩ ። 11. ዮሐ. ፫ ፡
፲፱—፳፩ ። ሕዝቅ. ፰ ፡ ፭—፲፪ ። 12. ዕብ. ፮ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፳፯ ፡ ፴፮—፴፫ ።

በሰካራሞች ፡ ጩኸት ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈሳዊ ፡ መዝሙርና ፡ ዝማሬ ፡ ከመ
ንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በሚመነጭ ፡ ቅኔ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በጉባኤ ፡ (በማ
ኅበር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡) ተነጋገሩ ። እንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ድምፃችሁን ፡
ሳታሰሙ ፡ [13] በልባችሁ ፡ ለጌታ ፡ ተቀኙና ፡ ዘምሩ ፤ ሁልጊዜም ፡ ስለ ፡
ሁሉ ፡ ነገር ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሱል ፡ [14] እግዚአብ
ሔርን ፡ አመስግኑ ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «የምትከተሉ ።» (ቊ. ፭ ።) ቃሉ ፡ በእውነት ፡ «የም
ትመስሉ» ነው ፡ በ፩ቆሮ. ፬ ፡ ፲፮ና ፡ በም. ፲፩ ፡ ፩ ፡ እንደዚሁም ፡ በፊ
ልጵ. ፫ ፡ ፲፯ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንድ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ የሚያደርገውን ፡
በመመልከት ፡ ራሱ ፡ ያንኑ ፡ ነገር ፡ እንደሚያደርግና ፡ አባቱን ፡ እንደሚ
መስል ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተመልክቶ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ፍለጋ ፡ መከተልና ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ አለ
በት ። በትያትር ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ተዋናይ ፡ ነገር ፡ ነው ። ያ ፡ ተዋ
ናይ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ እቋቋምና ፡ አነጋገር ፡ አደራረግም ፡ ያጠናና ፡ በኋላ ፡
በዚያ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እስኪጠራ ፡ ድረስ ፡ ሰውየውን ፡ እንደሚመስል ፡
እንዲሁም ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክርስቶስንም ፡ መምሰል ፡
ያሻዋል ።

ለ) «እንደ ... እንደ ።» (ቊ. ፪ ።) ሚትራችን ፡ ወሰናችንም ፡ እነሆ፤
እኛ ፡ ይቅር ፡ የምንለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ እንዳለን ፡ እኛም ፡ የም
ንወደው ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ወደደን ፡ ነው ። [15] ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሜትር !

ሐ) «መባና ፡ መሥዋዕት ።» (ቊ. ፪ ።) በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡
መባና ፡ መሥዋዕት ፡ እናነባለን ። [16] ዓይነተኛ ፡ አሳባቸው ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ በመሆናቸው ፡ ደስ ፡ ሊያሰኙት ፡ ነበረ ። [17] እነርሱ ፡
ግን ፡ ለጊዜው ፡ የሚሆኑ ፡ ምሳሌዎች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። የክርስቶስ ፡ ምሳ
ሌዎች ፡ ነበሩ ፡ እርሱም ፡ ፍጻሜአቸው ፡ ነበረ ። [18] ክርስቶስ ፡ መጥቶ ፡
ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ከእነዚያ ፡ መባዎችና ፡ መሥዋዕቶች ፡
ምንኛ ፡ ይልቅ ፡ አባቱን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሰኘ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ብሎ ፡ ይቅር ፡ አለን ።

መ) «ስለ ፡ እናንተ ።» (ቊ. ፪ ።) ክርስቶስ ፡ የመጣው ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ
ልን ፡ እንዲት ፡ መኖር ፡ እንደሚገባን ፡ ለማሳየት ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ መም
ሕር ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለማስ
ተማር ፡ ወይም ፡ እንኳ ፡ ታላቅ ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ አይደለም ። ይህንስ ፡
ሁሉ ፡ እደረገ ፡ ሆነም ። የመጣው ፡ ግን ፡ «ስለ ፡ እናንተ» ነው ። የመ

13. ፩ሳሙ. ፩ ፡ ፲፫ ። 14. ዮሐ. ፲፱ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ። ኤፌ. ፪ ፡ ፲፰ ። 15. ማቴ. ፲፰ ፡
፳፩ ፡ ፳፪ ። ዮሐ. ፲፫ ፡ ፴፬ ። 16. ዘሌዋ. ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ። 17. ዘፍጥ. ፰ ፡ ፳ ፡
፳፩ ። ዘጸአ. ፳፱ ፡ ፲፰ ። ዘሌዋ. ፩ ፡ ፱ ። 18. ዕብ. ፱ ፡ ፳—፳፩ ፡ ፲ ፡ ፲፩—፲፬ ።

ጣው ፡ ከኃጢአታችን ፡ ሊያድነን ፡ ነው ፤ የመጣው ፡ የጠፋውን ፡ ሊፈ
ልግና ፡ ሊያድን ፡ ነው ። [19]

ሠ) «እመንዝራም ።» (ቍ. ፭ ።) በዚህ ፡ ከፍል ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡
ዓይነት ፡ ኃጢአት ፡ ከሌላ ፡ ዓይነት ፡ የባሰ ፡ መሆኑ ፡ ነውን? ከመንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይከለክላልን? ፡ እይደለም ፤ ይህ ፡ ዓይነት ፡ ነፍስ ፡ ከመ
ግደል ፡ ውሸት ፡ ከመናገር ፡ ሰው ፡ ከመሳደብ ፡ ከትዕቢትም ፡ እንደሚ
ብስ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እይነግረንም ። [20] ሰው ፡ ከተመለሰ ፡ ንስሐም ፡
ከገባ ፡ ይህን ፡ ኃጢአት ፡ ከመሥራቱ ፡ የተነሣ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
እንደማይከለከል ፡ ከ፩ቆሮ. ፮ ፡ ፱—፲፩ና ፡ ከቁላ. ፫ ፡ ፭—፯ ፡ እንረዳለን ።
ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ እንደምናየው ፡ ሁሉ ፡
ዝሙትና ፡ ምንዝርነት ፡ ቀላል ፡ ነገሮች ፡ ከቶ ፡ እይደሉም ። በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠሉ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ፡ በሠሪዎችም ፡ ላይ ፡ ቍጣን ፡
ያስከትላሉ ። [21] ወንድና ፡ ሴት ፡ ሳይጋቡ ፡ ፍትወታቸውን ፡ እንዲያው ፡
እንዲፈጽሙ ፡ ልጆች ፡ እባት ፡ እልባ ፡ ሆነው ፡ እንዲወለዱ ፡ ጎብረተ ፡
ሰብም ፡ እንዲፈርስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ የተፈጠረውም ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ እንስሳ ፡ እንዲኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እይደለም ። ከርስ
ቲያን ፡ በሞራል ፡ ንጽሕና ፡ ሁሉ ፡ ለመኖር ፡ ታዝዞአል ፡ እንደዚህም ፡
ካልኖረ ፡ ፍርዱ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ። ከርስቲያን ፡ ወንድሜና ፡እህቴ ፡
ሆይ ፡ ተጠንቀቁበት! ይህ ፡ ነገር ፡ ዛሬ ፡ በሰው ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡
ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡
በሚፈረድበት ፡ ቀን ፡ የእርሱን ፡ ግምት ፡ እናያለን ። [22]

ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በግልጥ ፡ ይነገርበታል ፡
አዋቂ ፡ ሰዎችም ፡ «ደግ ፡ ነው ፡» ይላሉ ። የሐዋርያው ፡ እስተያየት ፡ ግን ፡
ሌላ ፡ ነው ። እርሱ ፡ «እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አይሰማ ፡ እትነጋገሩ
በትም ፡» ይላል ። ከተበላሸ ፡ ንግግር ፡ ከሞኝ ፡ ንግግር ፡ ሁለት ፡ ፍች ፡
ካለው ፡ ከመጥፎ ፡ የቀልድም ፡ ቃል ፡ ከርስቲያን ፡ ይጠንቀቅ ። ይህን ፡
የመሰለ ፡ ጫወታ ፡ በሚደረግበትም ፡ ዘንድ ፡ ከርስቲያን ፡ አይገኝ ፡ ይህ
ንም ፡ ከሚያደርገው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አይዛመድ ፡ ጓደኛውም ፡ አይሁን ። እግ
ዚአብሔር ፡ «ከመካከላቸው ፡ ውጡና ፡ የተለያችሁ ፡ ሁኑ » ይላል ። [23]

ረ) «እርሱም ፡ ጣያትን ፡ የሚያመልክ ፡ » (ቍ. ፮ ።) «ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡
እርሱን ፡ እፈልጋለሁ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ እደርገዋለሁ ፡» ብሎ ፡ ገንዘብ ፡
ለማግኘት ፡ ሆነ ፡ ፍትወት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚመኝ ፡ (የሚጐመጅ ፡) ሰው ፡
ጣያትን ፡ እንደሚያመልክ ፡ ነው ። [24] እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ያን ፡ የተመ
ኘውን ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ በፊት ፡

19. ማቴ. ፩ ፡ ፳፩ ። ሉቃ. ፲፱ ፡ ፲ ። ፩ጢሞ. ፩ ፡ ፲፭ ። 20. ማቴ. ፲፭ ፡ ፲፰—፳ ።
21. ዕብ. ፲፫ ፡ ፬ ። ፩ተሰ. ፬ ፡ ፫—፰ ። 22. ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፭ ።
23. ፪ቆሮ. ፮ ፡ ፲፬—፲፰ ። 24. ቈላ. ፫ ፡ ፭ ።

ቅዱሚያ ፡ ይሰጠዋል ፤ ጣዖቱ ፡ ነው ። ሐዋርያ ፡ ዮሐንስ ፡ «ልጆች ፡ ሆይ ፡
ከጣዖታት ፡ ራሳችሁን ፡ ጠብቁ ፡» ብሎ ፡ ያስጠነቅቀናል ። [25]

ሰ) «ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ እየመረመራችሁ ።» (ቍ. ፲ ።)
የጌታችን ፡ ዓላማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ የእንድ ፡ ከርስቲያንም ፡ ዓላማ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ለማስደሰት ፡ ይሁን ። [26] በእጠራጣሪ ፡ ወቅት ፡ ሁሉ ፡
«ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነውን ፡ ያ? » ብለን ፡ ራሳችንን ፡ መጠ
የቅ ፡ ያሻናል ። ለዚህም ፡ ማስተዋል ፡ ያስፈልገናል ። (ቍ. ፲፩ ።) እኛ ፡
እንደምናስበው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እይሆንም ፡ ይሆናል ፤ መጽሐፍ ፡
ቅዱስን ፡ ማንበብ ፡ ጸሎትንም ፡ ማድረግ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መታ
ደስ ፡ እርሱ ፡ የሚለውን ፡ ማዳመጥ ፡ ይኖርብናል ። [27] ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚ
ያሰኘውን ፡ ለይተን ፡ ስናውቅ ፡ ያንኑ ፡ ነገር ፡ መምረጥ ፡ ያሻናል ። እር
ሱን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ የሕይወታችን ፡ ዓላማ ፡ ይሁን ።

ሸ) «ግለጡት ።» (ቍ. ፲፩ ።) እውነት ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ብርሃን ፡ ተቀ
ብለናልና ፡ ራሳችን ፡ አሁን ፡ ብርሃናት ፡ ሆንን ። እንግዲያውስ ፡ ጨለ
ማውን ፡ እጥፍተን ፡ በጨለማ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ መግለጥ ፡ ተገቢ ፡
ሥራችን ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ እድርገን ፡ እንገልጠዋለን?
ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ይህ ፡ ነው ። ወጥተን ፡ የማይገባ ፡ (የጨለማ) ሥራ ፡
ወደሚሠራበት ፡ ሄደን ፡ እንቁምና ፡ «አይሆንም ! » ብለን ፡ እናውጅ?
ይህስ ፡ መልካምን ፡ ሳያደርግ ፡ ጥልን ፡ ያስነሣ ፡ የለምን? ሳያስነሣ ፡ አይ
ቀርምና ፡ በሌላ ፡ ዘዴ ፡ ብንገልጥ ፡ ይሻላል ። «እንደምን?» ቢሉ ፡ በም
ናደርገው ፡ አንዳንድም ፡ ጊዜ ፡ በማናደርገው ፡ ይሆናል ። እንናገርም ፡
ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳንዶችን ፡ ነገሮች ፡ ስናደርግ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡
የሚያደርጉትን ፡ እንዳንዶችንም ፡ ነገሮች ፡ ሳናደርግ ፡ ስንቀር ፡ በመካ
ከላቸው ፡ መብራቶች ፡ ሆነን ፡ እንመላለሳለን ፡ ምልክትም ፡ እንሆንላ
ቸዋለን ። [28] የቤት ፡ መብራት ፡ መቸም ፡ እይናገርም ፡ ሆኖም ፡ ያበራል ፡
ሁሉንም ፡ ይገልጣል ። እኛም ፡ እንደዚሁ ፡ እናድርግ ፡ የእኗኗራችንም ፡
ልዩነት ፡ ሲያዩ ፡ የእነርሱው ፡ ጨለማ ፡ ይታወቃቸውና ፡ «ምነው?»
ብለው ፡ ይጠይቁናል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ገልጠን ፡ መናገር ፡ እንችላለን ። እን
ባቢ ፡ ሆይ ፡ የእርስዎ ፡ አኗኗር ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ መብራት ፡ ነውን?
ከርስቶስ ፡ ካበራዎት ፡ እርስዎ ፡ ሌሎችን ፡ ማብራት ፡ ይገባዎታል ። እን
ዲህ ፡ ነው ፡ ወይ?

ቀ) «በስውር ፡ ስለሚያደርጉት ።» (ቍ. ፲፪ ።) ከፉ ፡ የሚሠሩት ፡
ከፋታቸውን ፡ በስውር ፡ የሚያደርጉት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው? ስለሚ
ያፍሩበት ፡ ሌሎችም ፡ እንዳያውቁባቸው ፡ እይደለምን? ሆኖም ፡ ሁሉም ፡
የሚገለጥበት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሊመጣ ፡ ነው ፡ በዚያንም ፡ ቀን ፡ በእግዚአ

25. ፩ዮሐ. ፭ ፡ ፳፩ ። 26. ዮሐ. ፰ ፡ ፳፱ ። ማቴ. ፲፮ ፡ ፳፫ ። ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፱ ። ዕብ.
፲፩ ፡ ፮ ። 27. ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ምሳ. ፫ ፡ ፭—፰። 28. ፩ጴጥ. ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

ብሔር ፡ ፊት ፡ እንደምን ፡ ይቆማሉ? በዚያን ፡ ቀን ፡ እያፈሩ ፡ መልስ ፡ አጥ
ተው ፡ ይቆሙ ፡ የለምን ? [29] ክፉትን ፡ እንደዚህ ፡ በስውር ፡ የሚያደርግ ፡
ሰው ፡ አምላኩን ፡ ለመገናኘት ፡ አሁኑኑ ፡ ቢዘጋጅ ፡ አይሻልምን ? [30]

በ) «የምትተኛ ፡ ሆይ ። » (ቀሥ. ፲፬ ።) በዚህ ፡ ቍራጭ ፡ መዝሙር ፡
ላይ ፡ አማኝ ፡ ክርስቲያንን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ፫ ፡ ምሳሌዎች ፡ ተቀላቅ
ለዋል ። ክርስቲያን ፡ ከእንቅልፍ ፡ የነቃ ፡ ነው ፡ (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።) ፡
ክሙታን ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፬ ።) ፡ ክጨለማ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡
ብርሃን ፡ የመጣም ፡ ነው ። (ኤፌ. ፭ ፡ ፲፬ ።)

ተ) «ዘመኑን ፡ ዋጁ ።» ቍሥ. ፲፮ ።) «ዋጁ» የሚል ፡ ቃል ፡ የገበያ ፡
ቃል ፡ ነው ። ሰው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ይሄድና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ሲያይ ፡ አን
ዱን ፡ ስንኳ ፡ ሳያስቀር ፡ ልቅም ፡ ልቅም ፡ አድርጎ ፡ ይገዛዋል ። እኛም ፡
መምሕራን ፡ ማድረግ ፡ የሚገባን ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ነው ።
ቀኖቹ ፡ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፡ እኛ ፡ በሚቻልበት ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ በጊዜ
ውም ፡ አለጊዜውም ፡ የክርስቶስን ፡ ቃል ፡ ማስተማር ፡ ይገባናል ። [31]

ቸ) «መንፈስ ፡ ይሙላባችሁ ፡ እንጂ ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ አትስከሩ ።»
ቍሥ. ፲፰ ።) «እንደ ፡ ሞኞች ፡ አትሁኑ ።» ተባለ ። ሞኞች ፡ የሚያደርገን ፡
ዋናው ፡ ነገር ፡ ስካር ፡ ነው ። የሰከረ ፡ ሰው ፡ አያስተውልም ፡ የሚናገረው
ንና ፡ የሚያደርገውን ፡ አያውቅም ፡ ራሱን ፡ መግዛት ፡ አይችልም ፡ ስክ
ሮም ፡ ሳለ ፡ በኋላ ፡ የሚያፍርበትንና ፡ የሚያዝንበትን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያደር
ጋል ። ስካር ፡ ሰውን ፡ ያዋርዳል ፡ ግፍ ፡ ያሠራል ፡ ጊዜ ፡ ያባክናል ፡ ሰውነ
ትንና ፡ አእምሮንም ፡ ያበሰብሳል ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ጎብረት ፡ ያጠፋል ፡
ክሥራ ፡ ያስወግዳል ፡ የልጆችን ፡ ኑሮ ፡ ያበላሻል ፡ ከወደ ፡ ፊትም ፡ ተ
ስፋ ፡ ሁሉ ፡ ያቋርጣል ። ይህንም ፡ ሁሉ ፡ ሲያስደርግ ፡ ስካር ፡ ራሱ ፡ አታ
ላይ ፡ ውሸታም ፡ ነው ። «ደስታን ፡ ኃይልን ፡ መጽናናትን ፡ ክብርንም ፡
እሰጣለሁ ።» ሲል ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ አይሰጠንም ፡ ፍሬውም ፡ የመራራ ፡
መራራ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በተቃራኒው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ መ
ልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ይሰጣል ፡ አትረፍርፎም ፡ ይሰጣል ።
ሐዋርያው ፡ «ይሙላባችሁ ።» ይላል ፡ ምክንያቱም ፡ አማኝ ፡ ክርስቲያን ፡
ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተቀበለ ፡ ቢሆንም ፡ በክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ መ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እልሞላም ። የሚሞላብን ፡ ሁሉመናችንን ፡ ለጌታ ፡ ስናስ
ገዛ ፡ ማለት ፡ ሰውነታችንን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዲሆን ፡ ስናቀርብ
ለት ፡ ነው ። [32] መሞላት ፡ የአንድ ፡ ጊዜ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሚደ
ጋገም ፡ ነው ። [33] መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እናሳዝን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ሳን

29. ሉቃ. ፲፪ ፡ ፮ ። ማቴ. ፭፪ ፡ ፲፪ ። ፩ዮሐ. ፪ ፡ ፳፰ ። 30. ዓሞ. ፬ ፡ ፲፪ ። ማቴ. ፭ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ። 31. ፪ጢሞ. ፬ ፡ ፪ ፡ ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ። 32. ፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፲፫ ። የሐዋ. ፪ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ። ሉቃ. ፲፩ ፡ ፲፫ ። ዮሐ. ፯ ፡ ፴፯—፴፱ ።
33. የሐዋ. ፪ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ፴፰ ።

ታዘዝለት ፡ ስንቀር ፡ ወይም ፡ ወደን ፡ ኃጢአት ፡ ስንሠራ ፡ እየጐደለብን ፡
ይሄዳል ፡ ያም ፡ እንቅፋት ፡ እስኪወገድ ፡ ድረስ ፡ መንፈስ ፡ ተመልሶ ፡ ሊ
ሞላን ፡ አይችልም ። ሐዋርያው ፡ «ተሞልታችሁ ፡ ኑሩ ፡» ይለናል ።

«መጠጥ ፡ ክልክል ፡ ነውን ?» ይሉኝ ፡ ይሆናል ። የተከለከለው ፡
ስካር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መጠጥስ ፡ ክልክል ፡ አይደለም ። ጌታና ፡ ሐዋር
ያት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጥተዋል ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ጥቂት ፡ እንዲጠጣ ፡
ተመክሮአል ። [34] ዳዊትም ፡ ያመሰግነዋል ። [35] እንዳይጠጡ ፡ የተከለከ
ሉት ፡ በልዩ ፡ አኳኋን ፡ ራሳቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የለዩ ፡ ናዝራውያን ፡
ብቻ ፡ ነበሩ ። [36] መጠጥ ፡ ግን ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ጥፋትና ፡ ወደ ፡
ብዙ ፡ ኀዘን ፡ ወደ ፡ ማባከንም ፡ ሊያደርስ ፡ ይችላል ። [37] መጠጥን ፡ ማስቀ
ረትና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሞላት ፡ ማግኘት ፡ ጕዳት ፡ ሳይሆን ፡ ታላቅ ፡
ጥቅም ፡ ነውና ፡ አማኝ ፡ ክርስቲያን ፡ መጠጥን ፡ ቢያስቀር ፡ አይሻል
ምን?

ጎ) «መዝሙርና ፡ ዝማሬ ፡ መንፈሳዊም ፡ ቅኔ ።» (ቍሥ. ፲፱ ።) የመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሞላት ፡ ወደ ፡ ዝማሬ ፡ ያደርሳል ። ክጥንት ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ወቅት ፡
ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ መዝሙር ፡ ይፈልቃል ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
(«እርስ ፡ በርሳችሁ ፡» ተባለ) መዝሙር ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ። የምንዘ
ምራቸው ፡ የዳዊት ፡ መዝሙራት ፡ ይሆናሉ ፡ እመቤታችንና ፡ ዘካርያስ ፡
ስምያንም ፡ የዘመሩትን ፡ መዝሙሮች ፡ ይሆናሉ ። [38] እኛም ፡ ዛሬ ፡
የምናወጣቸው ፡ ዘመናውያን ፡ መዝሙሮች ፡ ይሆናሉ ። ሁሉም ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ዶስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ናቸው ፡ በእነርሱም ፡ ምስጋናችንን ፡ እና
ቀርባለን ። ካህናትም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አስቀዳሽ ፡ ሁሉ ፡
ለጌታ ፡ ይዘምር ።

ነ) «ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ አመስግኑ ።» (ቍሥ. ፭ ።) እርስዎ ፡ አንባ
ቢው ፡ ይህን ፡ ሲያዩ ፡ «ምነው ፡ ሁልጊዜ ፡ ላመስግን? ቀኑ ፡ የክረምት ፡
ሲሆን ፡ ችግርና ፡ ፕሮብሌም ፡ በየዓይነቱ ፡ ሲይዘኝ ፡ በሽታ ፡ ሲጠናብኝ ፡
ሥራዬ ፡ ሳይሳካልኝ ፡ ቀርቶ ፡ ኀዘን ፡ ሲካበድብኝ ፡ ልዘምርን? ሁልጊዜ ፡
ልዘምር?» ይሉኝ ፡ ይሆናል ። እምን ፡ ታዝዘአል! ለአማኝ ፡ ክርስቲያን ፡
ዋና ፡ ማጽናኛው ፡ መዝሙር ፡ መዘመር ፡ ነው ። ይሞክሩት! ደግሞ ፡ የዳ
ዊት ፡ መዝሙር ፡ ቍጥር ፡ ፻፭ን ፡ ይመርምሩ ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ጨምረው ፡ «ስለ ፡ ሁሉ ፡ ላመስግን? ዋ! እንደምን ፡
እችላለሁ? መጥፎ ፡ ነገር ፡ ሲመጣብኝ?» ይሉ ፡ ይሆናል ። እምን ፡ ደግሞ ፡
ታዝዘአል! ያን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ያመስግኑ ፤ ምክንያቱም ፡ «እግዚአብ

34. ማቴ. ፭፭ ፡ ፭፭—፭፱ ። ፩ጢሞ. ፭ ፡ ፳፫ ። 35. መዝ. ፩፻፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።
36. ዘኍል. ፮ ፡ ፩—፬ ። 37. ሉቃ. ፲፭ ፡ ፲፫ ። 38. ሉቃ. ፩ ፡ ፷፮ ፡ ፷፯ ፤ ፪ ፡ ፳፭ ።

ሔርን ፡ ለሚወዱት ፡ እንደ ፡ አሳቡም ፡ ለተጠሩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለበጎ ፡ እንደሚደረግ ፡ እናውቃለን ፡» ተብሎ ፡ ተጽፎአል ። [39] ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ ያመስግኑ! [40]

ም. ፭ ፡ ፳፭—ም. ፮ ፡ ፱ ። የምእመናን ፡ የግል ፡ ግንኙነት ።

ቊ. ፳፭—፴፫ ።

፳፭ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ፍርሃት ፡ ተገዙ ።
፳፮ ፡ ሚስቶች ፡ ሆይ ፡ ለጌታ ፡ እንደምትገዙ ፡ ለባሎቻችሁ ፡
፳፯ ፡ ተገዙ ፤ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱም ፡ አካሉን ፡ የሚያድን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
፳፰ ፡ ባል ፡ የሚስት ፡ ራስ ፡ ነውና ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትገዛ ፡ እንዲሁ ፡ ሚስቶች ፡
፳፭ ፤ ፳፮ ፡ ደግሞ ፡ በሁሉ ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይገዙ ። ባሎች ፡ ሆይ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፤ በውሃ ፡ መታጠብና ፡ ከቃሉ ፡ ጋር ፡ እንጽዶ ፡ እንዲቀድሳት ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡
፳፯ ፡ ሰጠ ፤ እድፈት ፡ ወይም ፡ የፊት ፡ መጨማደድ ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሳይሆንባት ፡ ቅድስትና ፡ ያለ ፡ ነውር ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ክብርት ፡ የሆነችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለራሱ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፈለገ ። እንዲሁም ፡ ባሎች ፡ ደ
፳፰ ፡ ግሞ ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ሥጋቸው ፡ አድርገው ፡ የገዛ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ሊወዱአቸው ፡ ይገባቸዋል ። የገዛ ፡ ሚስቱን ፡
፳፱ ፤ ፴ ፡ የሚወድ ፡ ራሱን ፡ ይወዳል ፤ ማንም ፡ የገዛ ፡ ሥጋውን ፡ የሚጠላ ፡ ከቶ ፡ የለምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእካሉ ፡ ብልቶች ፡ ስለ ፡ ሆንን ፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እን
፴፩ ፡ ዳደረገላት ፡ ይመግበዋል ፡ ይከባከበውማል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ይተባበራል ፡ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ። ይህ ፡
፴፪ ፡ ምሥጢር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እላለሁ ። ሆኖም ፡ ከእናንተ ፡
፴፫ ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ ሚስቱን ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ ይውደዳት ፡ ሚስቱም ፡ ባልዋን ፡ ትፍራ ።

ሐዋርያው ፡ እማኝ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዴት ፡ መኖር ፡ እንደሚገባቸው ፡ ከቊ. ፩ ፡ እስከ ፡ ቊ. ፭ ፡ ድረስ ፡ ሲያመለክት ፡ ከቊ. ፳፩ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራፉ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፤ እንኳንም ፡ እስከ ፡ ም. ፮ ፡ ፱ ፡ ድረስ ፡ በግል ፡ ግንኙነታቸው ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲገዛ ፡ ያዛቸዋል ። እስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ሚስቶችና ፡ ስለ ፡ ባሎች ፤ ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ልጆችና ፡ ስለ ፡ ወላጆች ፤ በመጨረሻም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ባሪያዎችና ፡ ስለ ፡ ጌቶች ፡ ይናገራል ። የሚለውን ፡ እናጻምጥ ።

39. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፰ ። 40. ፩ተሰ. ፭ ፡ ፲፮—፲፰ ።

ክርስቶስን ፡ እያያችሁ ፡ ክርስቶስን ፡ ስለምታክብሩና ፡ ስለምታፍሩ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ ብላችሁ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተገዙ ። ሚስቶች ፡ ሆይ ፡ ለጌታ ፡ ልትገዙ ፡ ዝግጁዎች ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ ለባሎቻችሁም ፡ ተገዙ ። ምክንያቱም ፡ ክርስቶስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ አካሉንም ፡ የምትሆን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዳኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁም ፡ ባል ፡ የሚስት ፡ ራስ ፡ ነውና ። የባል ፡ ፋንታ ፡ ራስና ፡ አዳኝ ፡ መሆን ፡ ነው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትገዛ ፡ ሁሉ ፡ የሚስት ፡ ፋንታ ፡ በሁሉ ፡ ለባልዋ ፡ መገዛት ፡ ነው ። ባሎች ፡ ሆይ ፡ በእገዛዙ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደምትመስሉት ፡ በእወዳደዱ ፡ ደግሞ ፡ እየመሰላችሁት ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ውደዱ ። «እርሱስ ፡ እንደምን ፡ ወደደ ?» ብትሉም ፡ ፍቅሩን ፡ በሁለት ፡ ነገር ፡ ገለጠ ፡— ፩ኛ ፡ በጥምቀት ፡ ባሕርና ፡ አብሮ ፡ በተሰጡ ፡ የእምነት ፡ ምስክርነት ፡ ቃል ፡ በማንጻት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዲቀድሳት ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠቱ ፤ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ እጮኛ ፡ እጮቶአት ፡ ራሱ ፡ ሙሽራ ፡ (መርዓዊ ፡) እርስዋም ፡ ሙሽሪት ፡ (መርዓት ፡) እየሆኑ ፡ በተፈጸመ ፡ ውበትና ፡ ነውር ፡ በሌለበትም ፡ ንጽሕና ፡ ተሸልማ ፡ አጊጣ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እንዲያቀርባት ፡ በመፈለጉ ። [41] እንዲሁም ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ በማድረግ ፡ ባሎች ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ አካላቸው ፡ ቈጥረው ፡ ሊወዱአቸው ፡ ይገባቸዋል ። በእውነቱ ፡ ፩ ፡ ሥጋ ፡ ናቸውና ፤ [42] ሚስቱን ፡ የሚወድ ፡ ራሱን ፡ ይወዳል ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ሥጋ ፡ የሚጠላስ ፡ ማን ፡ ነው ? ኧረ ፡ እንድም ፡ የለ ! እኛ ፡ የአካሉ ፡ ብልቶች ፡ ስለ ፡ ሆንን ፡ [43] ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ አካሉን ፡ ይመግበዋል ፡ ይከባከበዋል ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ አይጠላውም ። «ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ይተባበራል ፡ (ይጣበቃል ፡) ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ» ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ነው ። [44] በዚህም ፡ ጥቅስ ፡ ውስጥ ፡ የተሸሸገ ፡ ምሥጢር ፡ አለ ፡ ምሥጢሩም ፡ ታላቅ ፡ ነው ። ሐዋርያው ፡ ጥቅሱ ፡ ክርስቶስንና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደሚያመለክት ፡ ያስባል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እማኝ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የገዛ ፡ ሚስቱን ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ ይውደዳት ፡ ሚስትዮዋም ፡ ባልዋን ፡ ትፈር ፡ ትገዛለትም ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተገዙ ።» (ቊ. ፳፩ ።) ለሌሎች ፡ ለመገዛት ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ጸጋ ፡ ነው! ሁሉ ፡ ነገር ፡ በራሳቸው ፡ አሳብ ፡ እንዲደረግና ፡ እንዲካሄድ ፡ የሰንቶች ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ነው ! እነኝህ ፡ ሰዎች ፡ እሻፈረኝ ፡ ይላሉና ፡ ክሌሎች ፡ ጋር ፡ ሊስማሙ ፡ አይችሉም ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሆነ ፡ በማኅበርና ፡ በቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ምንኛ ፡ ያስቸግራሉ ፤ ምን ፡ ያለ ፡ ብልሽትም ፡ በኅብረታችን ፡ ይፈጥራሉ ! ዘወትር ፡ የራሳችንን ፡ መፈለግ ፡ ይ

41. ራእ. ፲፱ ፡ ፯ ፡ ፰ ፤ ፳፩ ፡ ፪ ። ፪ቆሮ. ፲፩ ፡ ፪ ። ቈላ. ፩ ፡ ፳፭ ። ይሁዳ ፡ ቊ. ፳፬ ።
42. ዘፍጥ. ፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ። 43. ኤፌ. ፩ ፡ ፳፫ ። 44. ዘፍጥ. ፪ ፡ ፳፬ ።

ህማ ፡ የጌታ ፡ መንገድ ፡ አልነበረም ። እርሱ ፡ ሊያገለግል ፡ ራሱንም ፡ ለሌሎች ፡ ሊሰጥ ፡ መጥቶአል ፡ እንጂ ፡ እንዲያገለግሉት ፡ አልመጣም ። ይህ ፡ ነው ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ! እንደ ፡ እርሱ ፡ ምነው ፡ ባሰብን ፡ እርስ ፡ በርሳችንም ፡ ለመገዛዛት ፡ በፈቀድን ! [45]

ለ) «በሁሉ ።» (ቁ. ፭፬ ።) የሰውነት ፡ አባሎች ፡ (እካላት ፡) ለራስ ፡ በሁሉ ፡ እንደሚገዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ለክርስቶስ ፡ በሁሉ ፡ እንደምትገዛ ፡ እንዲሁም ፡ ሚስቶች ፡ ለባሎቻቸው ፡ በሁሉ ፡ ይገዙ ። መጠኑ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይህስ ፡ ለሴቶች ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ይታያቸዋልን ? ይህን ፡ የሚያደርጉት ፡ «ክርስቶስን ፡ እያዩ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ ብለው ፡» መሆኑን ፡ ያስቡ ። ሴቶች ፡ ሆይ ፤ ስለ ፡ እርሱ ፡ ብላችሁ ፡ አድርጉት ። «በትዳኝ ፡ ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ፡» ተባለ ። [46] ባሎችም ፡ ሆይ ፤ ሚስቶቻችሁ ፡ ፍጹም ፡ መታዘዝን ፡ እንደሚሰጡአችሁ ፡ ሁሉ ፡ እናንተም ፡ ፍጹም ፡ ታማኝነትንና ፡ ፍጹም ፡ ፍቅርን ፡ ልትሰጡአቸው ፡ ተጠንቀቁ ። ዕዳ ፡ አይኑርባችሁ ! ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጽፎአል ፡— «የመታዘዝን ፡ መጠን ፡ ስምተሃልን ? የፍቅርንም ፡ ስማ ! ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትታዘዘው ፡ ሚስትህም ፡ እንድትታዘዝልህ ፡ ትወዳለህን ? ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳሰበው ፡ ሁሉ ፡ አንተም ፡ ስለ ፡ ሚስትህ ፡ አስብ ። ሕይወትህንም ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ብለህ ፡ እንድትሰጥ ፡ እንድትቈራረጥም ፡ ቢያስፈልግ ፡ እንቢ ፡ አትበል ። ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደ ፡ እግሩ ፡ ሥር ፡ ያደረሳት ፡ በዛች ፡ ወይም ፡ በፍርሃት ፡ ይህንም ፡ በሚመስል ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ በብርቱ ፡ በማሰቡ ፡ ነው ።» አካሄዳችሁ ፡ በሚስቶቻችሁ ፡ ዘንድ ፡ እንደዚሁ ፡ ይሁን ። ደግሞ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ሚስትዮዋ ፡ የእርስዋን ፡ ፍጥታ ፡ ባለመፈጸምዋ ፡ ምክንያት ፡ ባልዮው ፡ ከእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ማለት ፡ ከመውደድና ፡ ከመጠበቅ ፡ ከመከባከብም ፡ አልተፈታም ፤ ባልዮውም ፡ የእርሱን ፡ ፋንታ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ሚስትዮዋ ፡ ከእርስዋ ፡ ፋንታ ፡ ማለት ፡ በሁሉ ፡ ከመገዛት ፡ አልተለቀቀችም ።

ሐ) «ውደዱ ።» (ቁ. ፭፭ ፡ ፭፮ ።) «ይህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ፍቅር ፡ ነው ?» ቢሉ ፡ ይህች ፡ መልእክት ፡ በተጻፈችበት ፡ በግሪኩ ፡ ቋንቋ ፡ ውስጥ ፡ «መውደድ» የሚሉ ፡ ፫ ፡ ግሦች ፡ አሉ ። መጀመሪያው ፤ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ እኛም ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ባልንጀራችንን ፡ የምንወድበትን ፡ ፍቅር ፡ ያመለክታል ። [47] ሁለተኛው ፡ ሐዋርያው ፡ ጴጥሮስ ፡ ጌታን ፡ የወደደበት ፡ የተፈጥሮ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ፍቅር ፡ ነው ። [48] ሦስተኛውም ፡ ወንድ ፡ ሴትን ፡ የሚወድበት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የጾታ ፡ ፍቅር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የታዘዘው ፡ ፍቅር ፡ መጀመሪያው ፡ ነው ።

45. ማቴ. ፭ ፡ ፳፭—፳፰ ። ፊልጵ. ፪ ፡ ፭ ።
46. ዮሐ. ፲፬ ፡ ፲፭ ።
47. ዮሐ. ፫ ፡ ፲፮ ። ማቴ. ፳፪ ፡ ፴፯—፴፱ ።
48. ዮሐ. ፳፩ ፡ ፲፭—፲፯ ።

ለራሱ ፡ የማያስበው ፡ ለማግኘት ፡ ሳይሆን ፡ ለመስጠት ፡ የሚሻው ፡ ክርስቲያንን ፡ የወደደበትና ፡ በ፩ቆሮ. ም. ፲፫ ፡ ላይ ፡ የተነገረለት ፡ ፍቅር ፡ ነው ። [49]

መ) «በውኃ ፡ መታጠብና ፡ ከቃሉ ፡ ጋር ።» (ቁ. ፳፮ ፡ ፳፯ ።) በዚህ ፡ ነገር ፡ መምሕራን ፡ በእሳባቸው ፡ ተለያይተዋል ። ሐዋርያው ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፍ ፡ መስተፃምርን ፡ አስቀርቶ ፡ «በውኃ ፡ መታጠብ ፡ በቃል» ብሎ ፡ ጽፎአል ። «በቃል ፡» ሲል ፡ ምን ፡ ማለቱ ፡ ነው ? «የወንጌል ፡ ቃል ፡ ነው ፡» የሚሉ ፡ አሉ ። የሚያነጻው ፡ በእውነቱ ፡ ውኃው ፡ (የጥምቀት ፡ ውኃ) አይደለም ፤ ውኃው ፡ በመንፈሳችን ፡ ውስጥ ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ የሚያሳይና ፡ የሚያስረዳ ፡ ሚዳዊ ፡ ምልክት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በእውነቱ ፡ የነጻንበት ፡ በወንጌል ፡ ቃል ፡ ነው ፡ የሚያሳምነንና ፡ የሚቀድሰን ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ ይላሉ ። [50] የውኃ ፡ መታጠብ ፡ አለ ፡ የቃልም ፡ መታጠብ ፡ አለ ፤ በቃል ፡ መታጠብ ፡ ነጽተናል ፡ በውኃ ፡ መታጠብ ፡ (በጥምቀት) መንጻታችን ፡ በምልክት ፡ ይገለጣል ፡ ይታተምማል ፡ ይላሉ ። ይህም ፡ ትርጉማቸው ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ መምሕራን ፡ ግን ፡ «አይደለም ፤ የሚናገርበቱ ፡ የእምነት ፡ ምስክርነት ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ምክንያቱም ፡ የሐዋ. ፰ ፡ ፴፮ ፡ እንደሚያመለክት ፡ ሁሉ ፡ ጥንት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲጠመቅ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ «እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እምናለሁ ፡» ብሎ ፡ የምስክርነትን ፡ ቃል ፡ ይሰጥ ፡ ነበርና ፡ «ቃል» የተባለ ፡ ይኸው ፡ የእምነት ፡ ምስክርነት ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ይላሉ ። [51] ይህም ፡ ትርጉም ፡ እንደዚሁ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ሊሆንም ፡ ይችላል ፡ እምነት ፡ ከሌለ ፡ ውኃው ፡ አይጠቅምምና ። እኔ ፡ ግን ፡ የውኃ ፡ መታጠብ ፡ የቃል ፡ መታጠብ ፡ ማጎተምና ፡ እውነተኛ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱ ፡ አሳቦች ፡ የሚዋሐዱ ፡ ይመስለኛል ።

ሠ) «ሰጠ ... ፈለገ ።» (ቁ. ፳፯ ፡ ፳፰ ።) ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሊቀድሳት ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ለራሱ ፡ ሊያቀርባት ፡ እስኪፈልግም ፡ ድረስ ፡ እንዲሁ ፡ ወደዳት ። አንባቢ ፡ ሆይ ፡ «ክርስቶስ ፡ ሰጠ ፡ ፈለገ ፡» ሲባል ፡ ይህን ፡ ለእርስዎ ፡ እንዳደረገ ፡ አስተውለዋልን ? ከዚህም ፡ ፍቅር ፡ የሚለየዎት ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ የለም ። [52]

ረ) «ማንም ፡ የገዛ ፡ ሥጋውን ፡ የሚጠላ ፡ ክቶ ፡ የለም ።» (ቁ. ፳፱ ፡ ፴ ።) ሥጋው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ንብረት ፡ ነውና ፡ በዚህችም ፡ ሕይወት ፡ ሳለ ፡ እንዲኖርበት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠ ፡ ነውና ፡

49. ፩ዮሐ. ፬ ፡ ፲ ።
50. ዮሐ. ፲፭ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ። የሐዋ. ፲፭ ፡ ፱ ። ሮሜ ፡ ፲፡፭ ፡ ፲፯ ። ፩ጴጥ. ፫ ፡ ፳፩ ።
51. ዮሐ. ፫ ፡ ፭ ። የሐዋ. ፳፪ ፡ ፲፮ ። ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ።
52. ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፴፭ ፡ ፴፱ ።

ሰው ፡ የገዛ ፡ ሥጋውን ፡ መውደድ ፡ ይገባዋል ፡[53] በተፈጥሮውም ፡ ይጠብቀዋል ። መኪና ፡ እንዳይድጠው ፡ መሸሹንና ፡ ወደ ፡ አይሮፕላን ፡ ሲገባም ፡ መፍራቱን ፡ በከረምትም ፡ ወራት ፡ ጉንፋንና ፡ የሳንባ ፡ በሽታ ፡ እንዳይዘው ፡ ልጅ ፡ ከሆነ ፡ ገሳን ፡ ትልቅ ፡ ሰውም ፡ የዝናብ ፡ ልብስን ፡ ማበጀቱን ፡ ስናይ ፡ ሰው ፡ የገዛ ፡ ሥጋውን ፡ እንደሚወድ ፡ እንረዳለን ። ሥጋችንን ፡ ከጉዳት ፡ ሁሉ ፡ መጠበቅ ፡ መመገብና ፡ መከባከብም ፡ የተገባ ፡ ሥራችን ፡ ነው ፤ ለሥጋችንም ፡ የምናደርገውን ፡ ሰሚስቶቻችንም ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል ።

እስኪ ፡ የእኔ ፡ ወንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ንብረት ፡ የሆነውን ፡ ሥጋህን ፡ ከሚጐዳው ፡ ሁሉ ፡ ትጠብቀዋለህን ፡ ወይስ ፡ ያን ፡ ሥጋህን ፡ የሚጐዱ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ አንዲኖሩ ፡ ትፈቅዳለህ ? እረ ፡ አይገባም !

ሰ) «ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ።» (ቊ. ፴፩ ።) ይህ ፡ እኮ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕቅድ ፡ ነው ። ወላጆቹ ፡ በዝምድና ፡ ከሁሉ ፡ የቀረቡ ፡ ናቸውና ፡ ትዳር ፡ ከመያዙ ፡ በፊት ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ ኃላፊነት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወደ ፡ ወላጆቹ ፡ ነው ። ትዳር ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ፡ በዝምድና ፡ ከሁሉ ፡ የቀረበችው ፡ ያች ፡ ሚስቱ ፡ ናት ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ይተባበራል ። ወላጆች ፡ የሆናችሁ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተገንዘቡ ። ልጆቻችሁ ፡ ካገቡ ፡ በኋላ ፡ እናንተ ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከል ፡ አትግቡ ። ልጁ ፡ ከወላጆቹ ፡ መለየት ፡ ወላጆቹም ፡ በልጃቸው ፡ ላይ ፡ መብታቸውን ፡ መካድ ፡ አለባቸው ። ይህ ፡ ነገር ፡ በልጆችም ፡ በወላጆችም ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ።

ሸ) «ይህ ፡ ምሥጢር ፡ ታላቅ ፡ ነው ።» (ቊ. ፴፪ ።) ሐዋርያው ፡ በዘፍጥ. ፪ ፡ ፳፬ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ነገር ፡ ሲያይ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስረጅነት ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ያያል ። አምን ፡ ጥቅሱ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ባልና ፡ ስለ ፡ ሚስት ፡ እንደሚናገር ፡ ታውቆአል ፤ ሆኖም ፡ በውስጡ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ የክርስቶስና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነገር ፡ ነው ። ጳውሎስ ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ ያያል ፡[54] ይህንም ፡ እያየ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የሆኑቱ ፡ ከቶ ፡ ሊለዩ ፡ አይችሉም ፡ ብሎ ፡ ያስባል ። ክርስቶስም ፡ መፋታት ፡ እንደማይገባ ፡ ለማስረዳት ፡ ይህንኑ ፡ ጥቅስ ፡ ጠቅሶአል ።[55] በክርስቶስና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ቀ) «ይውደዳት ... ትፍራ ።» (ቊ. ፴፫ ።) የሁለቱ ፡ ባለትዳሮች ፡ ኃላፊነት ፡ እነሆ ! ጳውሎስም ፡ ስለ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ መብታቸው ፡ አለመናገሩን ፡ እናስተውል ። የባልዮው ፡ ኃላፊነት ፡ ሊወድ ፡

53. ፩ቆሮ. ፮ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። መዝ. ፩፴፰ ፡ ፲፫—፲፮ ።
54. ኤፌ. ፩ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡ ፬ ። 55. ማቴ. ፲፱ ፡ ፬—፮ ።

የሚስቲቱም ፡ ልትፈራ ፡ ነው ። ባልዮው ፡ ራስ ፡ ነው ፡ ይሁንና ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ አግብቶአልና ፡ ኃላፊነቱን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ። መውደድና ፡ መጠበቅ ፡ መከባከብም ፡ አለበት ። ሚስቲቱም ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ከባል ፡ አታንስም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በገዛ ፡ ፈቃድዋ ፡ የሚስትነትን ፡ ማዕረግ ፡ ተቀብላለችና ፡ የዚያኑ ፡ ማዕረግ ፡ ኃላፊነት ፡ መፈጸም ፡ አለባት ። ባልዋን ፡ እያፈረች ፡ በሁሉ ፡ መገዛት ፡ አለባት ። ባልዮው ፡ ይውደድ ፤ ሚስቲቱም ፡ ትፍራ ። ተገቢው ፡ ነገር ፡ ይኸው ፡ ነው ።

(«ትፍራ ፡» የተባለው ፡ ቃል ፡ ተገቢ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ በቊ. ፳፩ ፡ ላይ ፡ «ፍርሃት ፡» ከተባለውም ፡ ቃል ፡ እኩል ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከፍቅር ፡ ጋር ፡ ፍርሃት ፡ ሊኖር ፡ አይችልምና ፡[56] የተነገረበቱ ፡ ፍርሃት ፡ በተለይ ፡ እፍረትና ፡ አክብሮት ፡ ነው ።[57]

56. ፩ዮሐ. ፬ ፡ ፲፰ ።
57. ዘሌዋ. ፲፱ ፡ ፫ ። ኢያሱ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። ምሳ. ፳፬ ፡ ፳፭ ። ማቴ. ፳፩ ፡ ፴፯ ። ፩ጴጥ. ፪ ፡ ፲፰ ።

ሐዋርያው ፡ በግል ፡ ግንኙነታቸው ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እርስ ፡ በርሳ
ቸው ፡ እንዲገዙ ፡ ሲመክራቸው ፡ ነው ። በምዕራፍ ፡ አምስት ፡ መጨረሻ ፡
ላይ ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ነገር ፡ አንሥቶ ፡ ስለ ፡ ሚስቶችና ፡ ስለ ፡ ባሎች ፡ ተና
ግሮአል ። ነገሩን ፡ ይቀጥልና ፡ በምዕራፍ ፡ ስድስት ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ስለ ፡ ልጆችና ፡ ስለ ፡ ወላጆች ፡ ለጥቆም ፡ ስለ ፡ ባሪያዎችና ፡ ስለ ፡
ጌቶች ፡ ይናገራል ። ይህን ፡ አድርጎ ፡ ሲያበቃ ፡ «በቀረውስ ፡» ይልና ፡
መልእክቱን ፡ ሊያቆም ፡ ይመድባል ። ከማቆሙ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በክርስ
ትና ፡ ተጋድሎአቸው ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡ እያደፋፈራቸው ፡ የእግዚአብሔ
ርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ እንዲለብሱ ፡ ያሳስባቸዋል ። ይህን ፡ ያደርግና ፡
ጸልዩልኝ ፡ እያለ ፡ ሰላምታም ፡ እያቀረበ ፡ «እሜን ፡» በተባለ ፡ ቃል ፡
መልእክቱን ፡ ይዘጋል ።

የምእመናን ፡ የግል ፡ ግንኙነት ። (ተቀጣይ ።)

ቊ. ፩—፱ ።

፩ ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ለወላጆቻችሁ ፡ በጌታ ፡ ታዘዙ ፡ ይህ ፡
፪ ፤ ፫ ፤ የሚገባ ፡ ነውና ። «መልካም ፡ እንዲሆንልህ ፡ ዕድሜ
ህም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲረዝም ፡ አባትህንና ፡ እናት
ህን ፡ አክብር» ፡ እርስዋም ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ያላት ፡ ፊተ
፬ ፤ ኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ። እናንተም ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፡ ልጆ
ቻችሁን ፡ በጌታ ፡ ምክርና ፡ በተግሣጽ ፡ አሳድጉአቸው ፡
፭ ፤ እንጂ ፡ አታስቈጡአቸው ። ባሪያዎች ፡ ሆይ ፡ ለክርስ
ቶስ ፡ እንደምትታዘዙ ፡ በፍርሃትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ በል
ባችሁ ፡ ቅንነት ፡ በሥጋ ፡ ጌቶቻችሁ ፡ ለሆኑ ፡ ታዘዙ ፤
፮ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚያደርጉ ፡ እንደ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ባሪያዎች ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ደስ ፡ እንደምታሰኙ ፡
፯ ፤ ለታይታ ፡ የምትገዙ ፡ አትሁኑ ። ለሰው ፡ ሳይሆን ፡
ለጌታ ፡ እንደምትገዙ ፡ በትጋትና ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ተገዙ ፤
፰ ፤ ባሪያ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ እያንዳንዱ ፡ የሚ
ያደርገውን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከጌታ ፡ በብድራት ፡
፱ ፤ እንደሚቀበለው ፡ ታውቃላችሁና ። እናንተም ፡ ጌቶች ፡
ሆይ ፤ ዛቻውን ፡ ትታችሁ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፡ በእ
ነርሱና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የሚገዛው ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ እ
ንዳለ ፡ ለሰው ፡ ፊትም ፡ እንደማያደላ ፡ ታውቃላችሁና ።

ልጆች ፡ ሆይ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንደመሆናችሁና ፡ ጌታን ፡ ደስ ፡ ለማ
ሰኘት ፡ ስትሉ ፡[1] እንደሚገባችሁ ፡ ሁሉ ፡ ለወላጆቻችሁ ፡ ታዘዙ ። ለል

1. ቊላ. ፫ ፡ ፲፰ ።

ጆች ፡ የሚሆን ፡ ቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ፡ «አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ።» የሚ
ለው ፡ የዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፤[2] ከማክበርም ፡ አንጹ ፡ ክቁል ፡
መታዘዝ ፡ ነው ። ትእዛዙንም ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ታላቅ ፡ የመልካምና ፡
የአጥጋቢ ፡ ሕይወት ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ተመድቦአል ። አባቶች ፡ ሆይ ፡
በእናንተ ፡ ወገንም ፡ ማድረግ ፡ የሚገባችሁ ፡ አለ ። ልጆቻችሁ ፡ እንዲታ
ዘዙላችሁ ፡ ከፈለጋችሁ ፡ እናንተ ፡ ልጆቹን ፡ በክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡
በተግሣጽም ፡ ማሳደግ ፡ አለባችሁ ፡ እንጂ ፡ ማናደድስ ፡ የለባችሁም ።

ባሪያዎች ፡ ሆይ ፡ ለክርስቶስ ፡ ልትገዙ ፡ ዝግጁዎች ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡
ሁሉ ፡ ለጌቶቻችሁ ፡ ታዘዙ ።[3] ለክርስቶስ ፡ የምታገለግሉት ፡ በፍርሃትና ፡
በመንቀጥቀጥ ፡ በልባችሁም ፡ ቅንነት ፡ ነውና ፡ ለጌቶቻችሁም ፡ እንደ
ዚሁ ፡ እድርጋችሁ ፡ አገልግሉ ።[4] ስትገዙም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡
እንደሚያደርጉ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያዎች ፡ ሆናችሁ ፡ ሥሩ ፡ እንጂ ፡
ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘትና ፡ የበላይ ፡ ዓይን ፡ ሲያርፍባቸው ፡ ብቻ ፡ እንደ
ሚሠሩ ፡ በመጥፎ ፡ መንፈስና ፡ በግድ ፡ የለኽነት ፡ እንደሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡
አትሁኑ ። ስትሠሩም ፡ ለሰው ፡ ሳይሆን ፡ ለጌታ ፡ እንደምትገዙ ፡ እየቈጠ
ራችሁ ፡ ደስ ፡ እያላችሁ ፡ በትጋት ፡ ሥሩ ፤[5] ይህንም ፡ የምለው ፡ ማዕረጉ ፡
(ሁኔታው ፡) ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ የሠራው ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡
መልካምን ፡ ይቀበላልና ፡ ነው ።[6]

እናንተም ፡ ጌቶች ፡ ሆይ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እንዲሠሩላችሁ ፡ ትፈ
ልጋላችሁን ? እንግዲያውስ ፡ በእናንተ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ያለውን ፡ ኃላፊ
ነት ፡ መፈጸም ፡ አለባችሁ ። የተለመደውን ፡ የጭካኔ ፡ ዛቻ ፡ አስቀርታ
ችሁ ፡ እነርሱ ፡ ለእናንተ ፡ እንዲያደርጉ ፡ የምትወዱትን ፡ እናንተም ፡
ለእነርሱ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ።[7] ምክንያቱም ፡ በእነርሱና ፡ በእናንተም ፡
ላይ ፡ የሚገዛ ፡ አንዱ ፡ ጌታ ፡ እንዳለ ፡ በዚያም ፡ በጌታችሁ ፡ ፊት ፡ ስት
ቆሙ ፡ እርሱ ፡ በትክክል ፡ እንደሚፈርድ ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንደማ
ያደላ ፡ ታውቃላችሁና ፡ ነው ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «ሚስቶችና ፡ ባሎች ፡ ልጆችና ፡ ወላጆች ፡ ባሪያዎችና ፡
ጌቶች ።» በዚህ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የሚስቲቱ ፡ የመገዛት ፡ ግዴታ ፡ ከባልዮው ፡
የመውደድና ፡ የመጠበቅ ፡ የመከባከብም ፡ ግዴታ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተቈራኘ ፡
እንዲሁም ፡ የልጅዮው ፡ የመታዘዝ ፡ ግዴታ ፡ አባትዮው ፡ የመልካም ፡
ማሳደግና ፡ ያለማስቈጣት ፡ ግዴታ ፡ ጋር ፡ የባሪያም ፡ የመታዘዝና ፡ የመ
ልካም ፡ ሥራ ፡ ግዴታ ፡ ከጌትዮው ፡ የእንዲሁ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ጋር ፡

2. ዘጸአ. ፳ ፡ ፲፪ ። 3. ም. ፭ ፡ ፳፪ ።
4. ቊላ. ፫ ፡ ፳፪ ። ፩ጴጥ. ፩ ፡ ፲፯ ፤ ፪ ፡ ፲፰ ። 5. ፩ቆር. ፯ ፡ ፳—፳፫ ።
6. ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፮—፲፩ ። ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፲ ። 7. ማቴ. ፯ ፡ ፲፪ ።

እንደ ፡ ተቈራኘ ፡ መገንዘብ ፡ የሚገባን ፡ ነገር ፡ ነው ። ከቶውንም ፡ ግዴታ ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ በኩል ፦ብቻ ፡ አይደለም ።

ለ) «ለወላጆቻችሁ ፡ ታዘዙ ።» (ቊ. ፮ ።) ልጆችም ፡ «ለምን ፡ ብለን ፡ እንታዘዝላቸዋለን ?» ቢሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በጳውሎስ ፡ አፍ ፡ ተናግሮ ፡ «ይህ ፡ የሚገባ ፡ ነውና ፡» ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጥቶአል ። ልጆችም ፡ ጨምረው ፡ «ለምን ፡ ይገባናል ?» ቢሉ ፡ የሚገባቸው ፡ ፩ኛ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ነውና ፡ (ዘጸአ. ፳ ፡ ፲፪ ።) ፪ኛ ፤ «ይህ ፡ ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነውና ፡ (ቈላ. ፫ ፡ ፳ ።) ፫ኛ ፤ ክርስቶስ ፡ ምሳሌ ፡ ትቶልናልና ፡ (ሉቃ. ፪ ፡ ፶፩ ።) ፬ኛ ፤ ልጆች ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ የወላጆቻቸው ፡ ባለ ፡ዕዳ ዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የተፈጥሮ ፡ ተገቢነት ፡ አለበትና ፡ ነው ። ማፈር ፡ መታዘዝም ፡ ለዓለም ፡ (ለምድር ፡) ጤና ፡ የሚሆኑ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ማፈርና ፡ መታዘዝ ፡ ከሌለ ፡ አስቀድሞ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ቀጥሎ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በመጨረሻም ፡ የሞላ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይጐዳል ፡ ትር ምስምስም ፡ ይሆናል ። መልካምና ፡ አጥጋቢ ፡ ሕይወት ፡ ከምድር ፡ ቀረ ፡ ማለት ፡ ነው ። ልጆች ፡ ሆይ ፡ ለወላጆቻችሁ ፡ በጌታ ፡ ታዘዙ !

ሐ) «የተሰፋ ፡ ቃል ፡ ያላት ፡ ፊተኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ።» (ቊ. ፪ ።) «ይህስ ፡ እንዴት ፡ ነው ? በፍቱ ፡ ቃላት ፡ በፀኛው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ የለም ፡ ወይ ?» ቢሉ ፡ ወይም ፡ «ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ሌላ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ የለምና ፡ ይህች ፡ «ፊተኛይቱ ፡» እንደምን ፡ ትባላለች ?» ቢሉ ፡ ቃሉን ፡ ብልጫ ፡ ባለው ፡ አሳብ ፡ እንጂ ፡ በቊጥር ፡ (በአጎዝ ፡) አለመተርጐም ፡ ነው ። ከማቴ. ፭፪ ፡ ፴፮ ፡ ፴፰ና ፡ ከማር. ፲፪ ፤ ፭፭ ፡ ከ፩ቆሮ. ፲፫ ፡ ፫ም ፡ ጋር ፡ ማነጻጠር ፡ ያሻል ። ይህች ፡ ትእዛዝ ፡ ለልጆች ፡ የምትሆን ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የሆነች ፡ በቁም ፡ ነገራምነትዋ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ቀዳሚነት ፡ ያላት ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ። ስለዚህ ፡ «ፊተኛይቱ ፡» ተባለች ።

መ) «አታስቈጡአቸው ።» (ቊ. ፬ ።) «አባቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በምን ፡ ያስቈጡአቸዋል ?» ቢሉ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሊያስቈጡአቸው ፡ (ሊያናድዱአቸው ፡) ይችላሉ ። ሕግና ፡ ትእዛዝ ፡ እያበዙ ፡ በየጥቃቅኑ ፡ ነገር ፡ ልጆቻቸውን ፡ የሚነዘንዙና ፡ በየነገሩ ፡ ሁሉ ፡ የሚቈጡ ፤ ልጆችም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ሊነግሩአቸው ፡ ወይም ፡ ሊያሳዩአቸው ፡ ጥያቄንም ፡ ሊጠይቁ ፡ ሲቀርቡ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ለመጫወት ፡ ጊዜ ፡ የሌላቸውና ፡ በንቀት ፡ ዓይንና ፡ በሸካራ ፡ ቃል ፡ የሚመልሱአቸው ፡ አባቶች ፡ አሉ ። ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ መግባባት ፡ የላቸውም ፡ ከቶውንም ፡ የፈገግታ ፡ ገጽ ፡ ሳያሳዩአቸው ፡ በኩስታራ ፡ ግምባር ፡ ያማርሩአቸዋል ። ታዲያ ፡ የልጆች ፡ ልብ ፡ ይዝልና ፡ ተበሳጭተው ፡ በአባታቸው ፡ ይናደዱ ፡ የለምን ?[8] ጥፋቱስ ፡ የማን ፡ ነው ? የወላጆች ፡ ነዋ !

8. ቈላ. ፫ ፡ ፳፩ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ወላጆች ፡ በተለይም ፡ አባቶች ፡ ፊት ፡ እያሳዩአቸውና ፡ ሰዓት ፡ እየሰጡአቸው ፡ በትህትናና ፡ በትዕግሥት ፡ በጌታ ፡ ምክርና ፡ በት ክክለኛ ፡ ተግሣጽ ፡ ያሳድጉአቸው ፡ እንደሆነ ፡ ልጆቹ ፡ ወላጆቻቸውን ፡ ያፍራሉ ፡ በደስታም ፡ ይታዘዙላቸዋል ።

አባቶች ፡ ሆይ ፡ ኃላፊነታችሁን ፡ (ግዴታችሁን ፡) አትርሱ ። ልጆቻችሁ ፡ ማጽናናታችሁንና ፡ «ጎሽ ፡ ልጄ !» እያላችሁ ፡ ማደፋፈራችሁንም ፡ እጅግ ፡ ይፈልጋሉ ። ዘወትር ፡ በቊጣ ፡ ብትመልሱአቸው ፡ የማን ፡ ነው ፡ ጥፋቱ ? እረ ፡ የእናንተው ፡ ነው ! በትር ፡ ለክፋት ፡ ቢኖርም ፡ ለመ ልካም ፡ ሥራ ፡ ከረሜላ ፡ የለም ፡ እንዴ ? ዘወትር ፡ እትቈጡባቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳንዴ ፡ አመለማኑአቸው ፡ ያንም ፡ ከረሜላ ፡ ለማሠኣቸው ። እን ዲታዘዘዙላችሁ ፡ ከፈለጋችሁ ፡ የራሳችሁን ፡ ግዴታ ፡ እታጓድሉባቸው ፡ ያውም ፡ ከሕጻንነታቸው ፡ ጀምሮ ።

ሠ) «ባሪያዎች ፡ ሆይ ።» (ቊ. ፭ ።) ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በክርስቶስ ፡ ዘመን ፡ የሚበዙቱ ፡ አውሮፓውያን ፡ የሆኑ ፡ ስልጣ ፡ ሚሊዮን ፡ ባሪያዎች ፡ በሮም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ቢኖሩም ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ በመነሣትና ፡ በሰብዓዊ ፡ ጕልበት ፡ የባርነትን ፡ ደንብ ፡ ለመገልበጥ ፡ (ለመሻር ፡) አላሰቡም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የባርነትን ፡ ደንብ ፡ የገለበጠው ፡ የእነርሱው ፡ ትምህርት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ አናሲሞስ ፡ የተባለ ፡ ባሪያ ፡ ነበረ ፡ ጳውሎስም ፡ ሕግን ፡ እያከበረ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መለሰው ። ሲመልሰው ፡ ግን ፡ «ተቀ ብለህ ፡ ለዘላለም ፡ እንድትይዘው ፡ ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ ለጊዜው ፡ ተለ ይቶሃልና ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አይሆንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለእኔ ፡ በተለየ ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ ከሆነ ፡ ለእንተማ ፡ ይልቅ ፡ በሥጋውም ፡ በጌታም ፡ ዘንድ ፡ ከባሪያ ፡ የሚሻል ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ እንዴት ፡ አይሆንም ፡» የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ አስይዞ ፡ ሰደደው ።[9] «ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አይሆንም ፡ እንደ ፡ ተወደደ ፡ ወንድም ፡ እንጂ» ! የባርነትን ፡ ደንብ ፡ ያጠፋው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ነው ። በም. ፭ ፡ ፭—፲፩ ፡ ላይና ፡ በም. ፭ ፡ ፲፩ ፡ ላይ ፡ «ሸ ፡» በተባለው ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ አስታውሱ ። ብርሃን ፡ ሲገባ ፡ ጨለማ ፡ ይሸሻል ፡ ተባለ ። (ብርሃን ፡ አስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ ባሪያዎቹ ፡ በታማኝነት ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሐዋርያው ፡ አዝዞአል ።) ይህም ፡ ስላ ፡ ባሪያዎችና ፡ ስለ ፡ ጌቶች ፡ የሆነ ፡ ሐዋርያዊ ፡ መምሪያ ፡ በየትም ፡ ዘንድ ፡ ቢገኙ ፡ በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ ለሠራተኞችና ፡ ለእሠሪዎች ፡ የሚሆን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ነው ።

ረ) እንግዲያውስ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እንዴት ፡ ነው ? ሐዋርያው ፡ በዚህ ፡ በግል ፡ ግንኙነት ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ እንደሚያመለክተን ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባሎቹ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡

9. ፊልሞ. ቊ. ፲፩ ፡ ፲፮ ።

ፍርሃት ፡ ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ ብለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚገዙበት ፡ ቤት ፡ ነው ። አንባቢ ፡ ሆይ ፡ የእርስዎ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነውን ?

ም. ፮ ፡ ፲—፳ ። ምእመናን ፡ በተጋድሎአቸው ፡ ይበረቱ ፡ ዘንድ ፡ የሐዋርያው ፡ መጨረሻ ፡ ምክር ።

፲ ፤ በቀረውስ ፡ በጌታና ፡ በኃይሉ ፡ ጽናት ፡ የበረታችሁ ፡
፲፩ ፤ ሁኑ ። የዲያብሎስን ፡ ሽንገላ ፡ ትቃወሙ ፡ ዘንድ ፡ እንዲቻላችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ልበሱ ።
፲፪ ፤ መጋደላችን ፡ ከደምና ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አይደለምና ፡ ከአለቆችና ፡ ከሥልጣናት ፡ ጋር ፡ ከዚህም ፡ ከጨለማ ፡ ዓለም ፡ ገዦች ፡ ጋር ፡ በሰማያዊም ፡ ሥፍራ ፡ ካለ ፡ ከክፋት ፡ መንፈሳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ። ስለዚህ ፡ በክፋው ፡ ቀን ፡ ለመቃወም ፡ ሁሉንም ፡ ፈጽማችሁ ፡ ለመቆም ፡ እንድትችሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡
፲፬ ፤ ፲፭ ፤ ሁሉ ፡ አንሡ ። እንግዲህ ፡ ወገባችሁን ፡ በእውነት ፡ ታጥቃችሁ ፡ የጽድቅንም ፡ ጥሩር ፡ ለብሳችሁ ፡ በሰላም ፡ ወንጌልም ፡ በመዘጋጀት ፡ እግሮቻችሁ ፡ ተጫምተው ፡ ቁሙ ፤
፲፮ ፤ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ጨምራችሁ ፡ የሚንበለበሉትን ፡ የክፉውን ፡ ፍላጻዎች ፡ ሁሉ ፡ ልታጠፉ ፡ የምትችሉበትን ፡
፲፯ ፤ የእምነትን ፡ ጋሻ ፡ አንሡ ፤ የመዳንንም ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ የመንፈስንም ፡ ሰይፍ ፡ ያዙ ፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡
፲፰ ፤ ቃል ፡ ነው ። በጸሎትና ፡ በልመናም ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ በመንፈስ ፡ ጸልዩ ፤ በዚህም ፡ አሳብ ፡ ስስ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡
፲፱ ፤ እየለመናችሁ ፡ በመጽናት ፡ ሁሉ ፡ ትጉ ፤ ደግሞ ፡ የወንጌልን ፡ ምሥጢር ፡ በግልጥ ፡ እንዳስታውቅ ፡ አፌን ፡ በመክፈት ፡ ቃል ፡ ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ስምኑ ፤
፳ ፤ ስለ ፡ ወንጌልም ፡ በሰንሰለት ፡ መልእክተኛ ፡ የሆንሁ ፡ መናገር ፡ እንደሚገባኝ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ በግልጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ለምኑ ።

በቀረውስ ፡ «በጌታ ፡» በመሆንና ፡ በእርሱ ፡ ኃይል ፡ ጽናት ፡ [10] ብርታትን ፡ እየተቀበላችሁ ፡ ኑሩ ። ዲያብሎስ ፡ በሽንገላው ፡ ፈትኖ ፡ ሊጥላችሁ ፡ ይታገላልና ፡ [11] የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ካልለበሳችሁ ፡ ትቃውሙት ፡ ዘንድ ፡ አይቻላችሁምና ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ በሉ ፡ ልበሱት ። እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የምንጋደለው ፡ ከሰውና ፡ ክግዙፍ ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ሳይሆን ፡ በአየር ፡ ካሉ ፡ መንፈሳውያን ፡ (ረቂቃን ፡) በየማዕረጋቸው ፡ [12] ከጨለማ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖችም ፡ ጋር ፡ ነው ። [13] ስለዚህ ፡ መጋደላ

10. ም. ፩ ፡ ፲፰—፳፩ ። ም. ፫ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። 11. ም. ፬ ፡ ፲፱ ። ግሥ. ፬ ፡ ፩—፲፩ ።
12. ም. ፩ ፡ ፳፩ ። 13. ሉቃ. ፳፪ ፡ ፶፪ ። ዮሐ. ፲፬ ፡ ፴ ። ቈላ. ፩ ፡ ፲፫ ።

ችሁ ፡ ጽኑ ፡ መሆኑን ፡ እየተገነዘባችሁ ፡ ትግል ፡ በሚበረታበቱና ፡ ፈተና ፡ በሚጸናበቱ ፡ ቀን ፡ ለመቃወምና ፡ [14] ተግባራችሁን ፡ ፈጽማችሁ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ አድራጊዎች ፡ ሆናችሁ ፡ ለመቆም ፡ እንድትችሉ ፡ እጃችሁን ፡ ዘርጉና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ [15] ሁሉ ፡ አንሡ ። እንግዲያውስ ፡ የዲያብሎስን ፡ ሽንገላ ፡ ልትቃወሙ ፡ የምትችሉት ፡ በእውነት ፡ ነውና ፡ ወገባችሁን ፡ በእውነት ፡ መታጠቂያ ፡ [16] አበርትታችሁ ፡ በደረታችሁ ፡ ላይ ፡ የቅንነትን ፡ ጥሩር ፡ ለብሳችሁ ፤ በእግራችሁም ፡ የሰላም ፡ ወንጌልን ፡ ለመሰበክ ፡ [17] የዝግጁነትን ፡ ጫማ ፡ አድርጋችሁ ፡ ቁሙ ። [18] ሰውነታችሁንም ፡ በሞላ ፡ የሚሸፍንና ፡ በቅጥራን ፡ ተነክረው ፡ በእሳት ፡ ተቀጣጥለው ፡ የሚወረወሩትን ፡ የለይጣንን ፡ ፍላጻዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚያጠፋውን ፡ ታላቁን ፡ የሃይማኖትን ፡ (የመታመንን ፡) ጋሻ ፡ አንሡ ። የክብር ፡ ተስፋ ፡ የተባለውን ፡ ያን ፡ የተፈጸመ ፡ መዳን ፡ ተስፋ ፡ [19] እንደ ፡ ራሰ ፡ ቍር ፡ አድርጋችሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሰይፍ ፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ [20] በእጃችሁ ፡ ያዙ ። የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ለበሳችሁ ፡ ዘወትር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሳሳቢነትና ፡ ረድኤት ፡ ጸልዩ ፡ ጸሎታችሁም ፡ በየዓይነቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ጸሎት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ልመና ፡ ይሁን ። [21] በዚህ ፡ ረገድ ፡ የክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ለሆኑት ፡ ሁሉ ፡ እየለመናችሁ ፡ ሳትታክቱ ፡ ሳታቋርጡም ፡ ተግታችሁ ፡ ጸልዩ ። [22] ለእኔም ፡ ጸልዩ ። የወንጌልን ፡ ምሥጢር ፡ [23] ምንም ፡ ሳላስቀር ፡ ግልጥ ፡ አድርጌ ፡ እንዳስታውቅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አፌን ፡ ክፍቶ ፡ ቃል ፡ ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ለምኑ ። [24] ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተላከሁ ፡ መልእክተኛ ፡ ብሆንም ፡ [25] በሰንሰለት ፡ ታስሬአለሁ ፤ ሆኖም ፡ መልእክቴን ፡ መናገር ፡ እንደሚገባኝ ፡ ደፍሬ ፡ እንድናገር ፡ ለምኑልኝ ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «የበረታችሁ ፡ ሁኑ ።» (ቍ. ፲ ።) ፡ «እንደምን ፡ ልበርታ ?» ቢሉ ፡ ራሳችንን ፡ ልናበረታ ፡ አለመቻላችንን ፡ ይወቁ ። ብርታትን ፡ የምናገኝ ፡ «በጌታ ፡» ነው ። «በጌታ ፡» ስንሆንና ፡ «በጌታ ፡» ስንኖር ፡ ከእርሱም ፡ ኃይል ፡ ስንካፈል ፡ [26] እንበረታለን ። እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በፊታችን ፡ ያለውን ፡ ዲያብሎሳዊ ፡ ውጊያ ፡ ስናይ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ «በእርሱ ፡ እንችላለን ! » በሚል ፡ መንፈስ ፡ በጌታ ፡ መበርታት ፡ ያሻናል ። [27] የኃይሉ ፡ ጽናትም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ፈተና ፡ ብርቱ ፡ ነው ። እንግዲያውስ ፡

14. ፩ኤፕ. ፭ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ያዕ. ፬ ፡ ፯ ። 15. ኢሳ. ፶፱ ፡ ፲፯ ። 16. መዝ. ፶ ፡ ፮ ።
17. ም. ፮ ፡ ፲፭ ። 18. ኢሳ. ፶፱ ፡ ፮ ። 19. ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፩—፳፫ ። ፩ተሰ. ፭ ፡ ፭ ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። 20. ዕብ. ፬ ፡ ፲፪ ። ፪ጢሞ. ፫ ፡ ፲፮ ። ፪ኤፕ. ፭ ፡ ፳፩ ።
21. ፊልጵ. ፬ ፡ ፮ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ። 22. ሉቃ. ፲፫ ፡ ፭ ። ፩ተሰ. ፭ ፡ ፲፮ ። ፩ኤፕ. ፭ ፡ ፲፱ ። የሐዋ. ፭ ፡ ፲፱ ። 23. ም. ፫ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፱ ። 24. ግሥ. ፲ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ። የሐዋ. ፬ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ፤ ፭ ፡ ፳፰—፳፱ ፡ ፳፯ ። 25. ፪ቆሮ. ፭ ፡ ፭ ።
26. ዮሐ. ፲፭ ፡ ፭—፮ ። 27. ፊልጵ. ፬ ፡ ፲፫ ። ፪ጢሞ. ፩ ፡ ፯ ።

በጌታና ፡ በኃይሉ ፡ ጽናት ፡ በርትተን ፡ ዲያብሎስን ፡ ልንቃወም ፡ እን
ውጣ ። [28] ከመሂዳችን ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡
ሁሉ ፡ እንልበስ ።

ለ) «የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ልበሱ ።» (ቊ. ፲፫ ።)
«ለምን ፡ ብዬ ፡ ዕቃ ፡ ጦርን ፡ ልልበስ ?» ቢሉ ፡ መዋጋት ፡ አስብዎታ !
የክርስቶስ ፡ ከሆኑ ፡ ዲያብሎስ ፡ ሳይነግብዎት ፡ አይቀርም ። በሚቻለው ፡
ሁሉ ፡ ይፈትንዎታል ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እስረኛ ፡ ሆኖ ፡ በእጠባቡ ፡
የተቀመጠውን ፡ ወይም ፡ የቆመውን ፡ ሮማዊ ፡ ወታደር ፡ ያያል ። ሰሰ
ልፍ ፡ ተዘጋጅቶአል ። የሮም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሰጠውን ፡ ዕቃ ፡
ጦር ፡ ሁሉ ፡ ሰብሶአል ። የወታደር ፡ ልብሱ ፡ ነው ። በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ እን
ዱንም ፡ ሊያስቀር ፡ አይችልም ። እያንዳንዱም ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊው ፡
ነው ። ጠላቱ ፡ ራሱን ፡ ደረቱን ፡ ወገቡን ፡ እግሩንም ፡ ለመምታት ፡ ይሞ
ክራልና ፡ ወታደሩ ፡ ዕቃ ፡ ጦሩን ፡ ሁሉ ፡ ይዞአል ። ወገቡን ፡ የሚያጸና ፡
መታጠቂያውን ፡ ደረቱን ፡ የሚሸፍን ፡ ጥሩሩን ፡ በቅልጥፍና ፡ የሚያራ
ምደውን ፡ ጫማ ፡ ታላቁን ፡ ጋሻ ፡ ራስ ፡ ቊሩን ፡ ሰይፉን ፡ ሁሉን ፡ ይዞ
አል ። እንዲሁም ፡ ከርስቲያን ፡ ዲያብሎስን ፡ ለመክላከል ፡ ብሎ ፡ የሮማ
ዊው ፡ ወታደር ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ የሚያመለክተውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕቃ ፡
ጦር ፡ ማለት ፡ እውነትን ፡ ቅንነትን ፡ ወንጌል ፡ መስበክን ፡ በጌታ ፡ ማመ
ንንና ፡ መታመንን ፡ የመዳን ፡ ተስፋን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ማወቅና ፡
ማስተዋልን ፡ መያዝ ፡ ያሻዋል ። ዲያብሎስ ፡ የሚቻለውን ፡ ክፍል ፡
ሁሉ ፡ ማለት ፡ ራሳችንን ፡ (አሳባችንን) ፡ ደረታችንን ፡ (ልባችንን) ፡
ወገባችንን ፡ (መጽናታችንን) ፡ እግራችንን ፡ (መቋሚያችንንና ፡ መን
ቃታችንን) ፡ ሁሉን ፡ ይፈትናል ። የሚያስፈራ ፡ ጠላት ፡ ነው ። «እረ ፡
ግድ ፡ የለም ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ ወታደራዊ ፡ ልብስ ፡ ለእኔ ፡ አስፈላጊ ፡ አይ
ደለም ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ አውቄበታለሁ ! » ፡ በማለት ፡ የለም ። «እንደ ፡
ቆመ ፡ የሚመስለው ፡ እንዳይወድቅ ፡ ይጠንቀቅ !» እንደ ፡ ተባለ ፡ ነው ። [29]
መምረጥ ፡ የለብንም ፡ ሁሉም ፡ አስፈላጊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃልና ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሁሉንም ፡ ስጥቶናል ፡ በሁሉም ፡ መጠቀም ፡ አለብን ። ዲያ
ብሎስም ፡ ሊውጠን ፡ ፈልጎ ፡ ዘወትር ፡ ይዞራልና ፡ [30] ከቶ ፡ ልንሰንፍ ፡
ተዘልለንም ፡ ልንቀመጥ ፡ አንችልም ።

ሐ) «በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ የክፋት ፡ መንፈሳውያን ፡ ሠራዊት ።»
(ቊ. ፲፪ ።) ፡ መጋደላችን ፡ ከደምና ፡ ከሥጋ ፡ ከሆኑትና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ከሚገኙት ፡ ጋር ፡ ሳይሆን ፡ ከመንፈስ ፡ ከሆኑትና ፡ በአየር ፡ ከሚገኙት ፡
ጋር ፡ ነው ። ከደምና ፡ ከሥጋ ፡ አይደሉምና ፡ «መንፈሳውያን ።» ናቸው ፤
ሆኖም ፡ የክፋት ፡ መንፈሳውያን ፡ ናቸውና ፡ መናፍስት ፡ እንችለዋለን ።
የዲያብሎስ ፡ ጭፍሮች ፡ የዐመፁ ፡ መላእክት ፡ አጋንንት ፡ ናቸው ። በቀ

28. ማቴ. ፮ ፡ ፩ ። 29. ፩ቆሮ. ፲ ፡ ፲፪ ። 30. ፩ጴጥ. ፭ ፡ ፰ ።

ዳሚው ፡ ግሪክ ፡ እንደዚሁም ፡ በግዕዝ ፡ «ሠራዊት ፡» የሚል ፡ ቃል ፡
የለም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነኝህ ፡ «መንፈሳውያን ፡» በብዛት ፡ ይጠራሉና ፡
ሠራዊት ፡ ቢባሉ ፡ ክፉ ፡ አይደለም ።

መ) «በሰላም ፡ ወንጌል ፡ በመዘጋጀት ፡ እግሮቻችሁ ፡ ተጫም
ተው ፡ ቁሙ ።» (ቊ. ፲፭ ፡ ፲፮ ።) ክርስቲያናዊ ፡ ወታደር ፡ ወንጌልን ፡
ሊሰብክ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ዝግጁ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። የሚሰብክውም ፡
«የሰላም ፡ ወንጌል» ፡ እርሱም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡
በኢየሱስ ፡ አማካይነት ፡ ስላም ፡ መግባቱን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዘነጋም ። [31]
ያ ፡ ወታደር ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ዝግጁ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ መብራቱ ፡
እየጠፋ ፡ ግስቱ ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ጉልበቱም ፡ እየደከመ ፡ ይሄዳል ። በመን
ፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ ከስንፍና ፡ ራሳችንን ፡ እንጠብቅ ። የሰላምን ፡ ወንጌል ፡
ለመስበክ ፡ ተጫምተን ፡ ተዘጋጅተን ፡ እንቁም ።

ሠ) «የሚንበለበሉ ፡ ፍላጻዎች ።» (ቊ. ፲፯ ።) በዚያ ፡ በሮም ፡
መንግሥት ፡ ዘመን ፡ ጦረኞቹ ፡ በፍላጻዎቻቸው ፡ ላይ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡
ጭድ ፡ ይጠመጥሙና ፡ ያን ፡ ጭድ ፡ በቅጥራን ፡ ነክረው ፡ ያቀጣጥሉና ፡
በጠላት ፡ ላይ ፡ ይወረውሩ ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ ሐዋርያው ፡ የሚጠቅሰው ፡
ሞላላ ፡ የሆነና ፡ ሰውነትን ፡ በሞላ ፡ የሚሸፍነው ፡ ጋሻ ፡ የሚንበለበሉትን ፡
የፍላጻዎች ፡ በፍጥነት ፡ ለማጥፋት ፡ በእንድ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቆዳ ፡ ተሠ
ርቶ ፡ ነበር ።

ረ) «የመንፈስ ፡ ሰይፍ ።» (ቊ. ፲፯ ።) ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ክዲያብሎስ ፡ በተፈተነ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሰይፍ ፡ መጠቀሙን ፡ እና
ስተውል ። [32] ዲያብሎስ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ቢፈትነው ፡ ጌታ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ የመ
ጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ጥቅስ ፡ በመጥቀስ ፡ ተቃወመው ፡ ሊመልሰውም ፡ ቻለ ።
በዚህ ፡ ሰይፍ ፡ ጌታ ፡ ተጠቀመ ፡ ሐዋርያትም ፡ ተጠቀሙ ፡ እኛም ፡ እን
ጠቀምበት ። [33] ዲያብሎስንም ፡ የምንወጋበት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሰ
ጠን ፡ መሣሪያ ፡ ነውና ፡ እንወቀው ። ማን ፡ ወታደር ፡ ነው ፡ መሣሪያውን ፡
ሳያውቅ ፡ ሳይፈትንም ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ የሚሄድ ? ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡
ቅዱስን ፡ እንመርምር ፡ ጥቅሱንም ፡ እናጥና ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ ሲመ
ጣብን ፡ ጥቅስ ፡ እናውጣና ፡ በመንፈስ ፡ ሰይፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
እንክላከለው ። ሐሰትን ፡ የሚቃወም ፡ ብርሃንንም ፡ የሚያገባ ፡ ከዲያብሎ
ስም ፡ አርነት ፡ የሚያወጣ ፡ ይሽው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

ሰ) «በጸሎትና ፡ ባልመናም ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ በመንፈስ ፡ ጸልዩ ።»
(ቊ. ፲፰ ።) ጸሎት ፡ እኮ ፡ ክጠቅላይ ፡ የጦር ፡ መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ጋር ፡
መገናኛ ፡ የስልክ ፡ መስመራችን ፡ ነውና ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ ለሁላ
ችን ፡ የሚሆን ፡ ቁም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ። ወታደሮች ፡ ብንሆንም ፡ ያለ ፡

31. ሉቃ. ፪ ፡ ፲፬ ። 32. ማቴ. ፬ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፲ ።
33. ሉቃ. ፲ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ። የሐዋ. ፲፯ ፡ ፪ ፡ ፫ ።

ጸሎት ፡ ዲያብሎስን ፡ እናሸንፈውም ። ሐዋርያው ፡ በጸሎትና ፡ በልመና ፡ ሁሉ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ በመጽናት ፡ ሁሉ ፡ እየተጋን ፡ እንድንጸልይ ፡ ይመክረናል ። ዘወትር ፡ በጸሎት ፡ ስሜት ፡ እንድንኖር ፡ ማለቱ ፡ ነው ። «በመንፈስ ፡» መጸለይስ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ? [34] እጋገራችን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። እንድንጸልይ ፡ የሚያነሣሣን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ጸሎታችንን ፡ የሚያጣራ ፡ ተገቢ ፡ መንፈስና ፡ ተገቢ ፡ ቃልም ፡ የሚሰጠን ፡ እርሱ ፡ ነው ። [35] ስለዚህ ፡ «በመንፈስ ፡» መጸለያችን ፡ ነው ። ጸሎት ፡ መጸለይ ፡ ግን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ልምምድም ፡ ያስፈልጋል ። መጽሐፈ ፡ ጸሎት ፡ ምንጊዜም ፡ ይጠቅማል ፡ በተሰይ ፡ ጀማሪዎች ፡ ስንሆን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ መጸለይን ፡ ስንለምድ ፡ ያስ ፡ መጽሐፍ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሚሰማ ፡ ቃል ፡ እንዳንድም ፡ ጊዜ ፡ እንዲያው ፡ በልባችን ፡ ልንጸልይ ፡ እንችላለን ። [36] ለጸሎትም ፡ ትጋት ፡ ያስፈልጋል ፤ ዘወትር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ባለማቋረጥ ፡ መጸለይ ፡ ያሻናል ። [37]

ሸ) «ስለ ፡ እኔ ፡ ለምኑ ።» ፡ (ቊ. ፲፱ ።) ፡ ሐዋርያ ፡ እንኳ ፡ ቢሆንም ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጸልዩለት ፡ ዘንድ ፡ ይፈልጋል ! እንዲጸልዩለትም ፡ የሚፈልገው ፡ ስለ ፡ እስራት ፡ ሁኔታው ፡ ሳይሆን ፡ እንደሚፈታም ፡ ሳይሆን ፡ ሰሥራው ፡ ነው ፡ እንደሚገባ ፡ ሁሉ ፡ እንዲናገር ፡ ነው ። የወንጌልን ፡ ምሥጢር ፡ በግልጥነት ፡ ወይም ፡ በድፍረት ፡ እንዳይናገር ፡ ሰግቶአልና ፡ «ጸልዩልኝ ።» ይላል ። [38] እኛስ ? ስለ ፡ ቀሳውስትና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ሰባኪያን ፡ እንጸልያለንን ? ጸሎታችን ፡ እስፈላጊያቸው ፡ ነው ፡ እኮ ! ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመንፈሳዊ ፡ መሪያቸው ፡ ያልጸለዩ ፡ እንደሆነ ፡ ያ ፡ መሪያቸው ፡ ይደከማል ፡ ሥራውንም ፡ እንደሚገባ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በጸሎታቸው ፡ ከደገፉት ፡ አገልጋዩ ፡ ቂስ ፡ መልእክቱን ፡ እንደሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማል ። ታዲያስ ፡ እኛ ፡ ለመንፈሳውያን ፡ መሪዎቻችን ፡ እንጸልያለንን ? ያልጸለይንላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ባለመሥራታቸው ፡ የምንወቅስበት ፡ መሠረት ፡ የለንም ።

ቊ. ፳፩—፳፭ ።

፳፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ እንዳለሁ ፡ ኑሮዬን ፡ እንድታውቁ ፡ የተወደደ ፡ ወንድምና ፡ በጌታ ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ቲኪቆስ ፡ ሁሉን ፡ ያስታውቃችኋል ፤

፳፪ ፤ ወሬአችንን ፡ እንድታውቁና ፡ ልባችሁን ፡ እንዲያጽናና ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የምልከው ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

፳፫ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ከእምነት ፡ ጋር ፡ ለወንድሞች ፡ ይሁን ።

34. ይሁዳ ፡ ቊ. ፳ ። 35. ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ። ፩ቆሮ. ፪ ፡ ፲—፲፪ ። 36. ፩ሳሙ. ፩ ፡ ፲፪—፲፯ ። 37. ሉቃ. ፲፰ ፡ ፩—፰ ። 38. ፪ተሰ. ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፳፬ ፤ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ባለመጥፋት ፡ ከሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ጸጋ ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

እኔ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ሰምቻለሁ ፡ አሁንም ፡ እናንተ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ [39] ስለ ፡ ጤናዬና ፡ ስለ ፡ ሁኔታዬ ፡ እንድትሰሙ ፡ በክርስቶስ ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ በጌታም ፡ ሆኖ ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ቲኪቆስን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልልክ ፡ ነኝ ፡ የምልከውም ፡ ወሬአችንን ፡ በመስማት ፡ ልባችሁ ፡ ከስጋት ፡ እንዲያርፍ ፡ ነው ።

ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚመጣ ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ለክርስቲያን ፡ ወንድሞች ፡ ይሁን ። ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማይጠፋ ፡ ፍቅር ፡ ከሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ጸጋ ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

ማስገንዘቢያ ። ሀ) «እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ እንዳለሁ ፡ እንድታውቁ ።» (ቊ. ፳፭ ።) ሐዋርያው ፡ ሰምእመናን ፡ ምእመናንም ፡ ሰዋሐርያው ፡ ይሰጋሉ ። በመካከላቸው ፡ የፍቅር ፡ ማሰሪያ ፡ አለና ፡ አንዱ ፡ የሌላውን ፡ ሁኔታ ፡ ሊያውቅ ፡ ይፈልጋል ። ዛሬም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አንዱ ፡ የሌላውን ፡ ሁኔታ ፡ ካለወቀ ፡ በሚገባ ፡ እንደምን ፡ ሊጸልይለት ፡ ይችላል ? ሁለተኛም ፡ አስተማሪው ፡ ሲርቅ ፡ አማኝ ፡ ልጁ ፡ ሊደክም ፡ ይችላል ። መልእክተኛ ፡ ግን ፡ ደርሶ ፡ «በርታ ፡ ይሉሃል !» ካለ ፡ የአማኙ ፡ ልብ ፡ ምንኛ ፡ ይጽናናል ! ስለዚህ ፡ ስንራራቅ ፡ መተሳሰብና ፡ ወሬአችንን ፡ መላላክ ፡ ይገባናል ። [40]

ለ) «ቲኪቆስ ።» (ቊ. ፳፩ ።) ይህ ፡ ሰው ፡ ዛሬ ፡ ቱርክ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ እስያ ፡ ከተባለ ፡ አውራጃ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ሐዋርያውም ፡ በቮኛ ፡ የወንጌል ፡ ጉዞው ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ቲኪቆስ ፡ አብሮት ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ተገኝቶ ፡ ሐዋርያውን ፡ ሸኘ ። [41] አሁንም ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ ከተማ ፡ እስር ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ቲኪቆስ ፡ ከዚያው ፡ አለ ፡ ሐዋርያውም ፡ እናሲሞስን ፡ ወደ ፡ ፊልሞና ፤ መልእክቶቹንም ፡ ወደ ፡ ቈላስይስና ፡ ወደ ፡ ኤፌሶንና ፡ ወደ ፡ ዙሪያዋ ፡ ሊልክ ፡ ሲፈልግ ፡ ቲኪቆስን ፡ መልእክተኛው ፡ አድርጎአል ። [42] ቲኪቆስም ፡ ወደ ፡ ቀርጤስ ፡ ደግሞ ፡ ተልኮ ፡ ይሆናል ። [43] ለጳውሎስ ፡ የተወደደ ፡ ወንድምና ፡ በጌታ ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ነበረ ።

ሐ) «ከእምነት ፡ ጋር ።» (ቊ. ፳፫ ።) ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ እምነት ! የእርሱ ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ከእኛ ፡ እምነት ፡ ጋር ፡ እንዲዋሐድ ፡ ያስፈልጋል ። [44] እግዚአብሔር ፡ እኔን ፡ እንደሚወድ ፡ ማመን ፡ በእውነት ፡ አስቸጋሪዬ ፡ ነው ። ታላቁ ፡ እምላካችን ፡ ትል ፡ የምመስል ፡ እኔን ፡ [45] ይወደኛልን ? ይወደኛል ፡

39. ም .፩ ፡ ፲፩ ። 40. ፊልጵ. ፪ ፡ ፲—፳ ። 41. የሐዋ. ፳ ፡ ፬ ። 42. ቈላ. ፬ ፡ ፯—፱ ። ፪ጢሞ. ፬ ፡ ፲፪ ። 43. ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ። 44. ዕብ.፬ ፡ ፪ ። 45. ኢሶ፡ ፵፩ ፡ ፮ ። ኢሳ. ፵፩ ፡ ፲፬ ።

ሆኖም ፡ ካላመንሁኝ ፡ ሰላሙና ፡ ፍቅሩ ፡ አይደርሰኝም ። ሐዋርያው ፡ «ከእምነት ፡ ጋር ፡» ማለቱ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

መ) «ባለመጥፋት ።» (ቊ. ፳፬ ።) «እረ ፡ ፍች ፡ አይሰጥም ! ምን ፡ ማለቱ ፡ ይሆን ?» ቢሉ ፡ ቃሉስ ፡ በእውነት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፡ ቢሆንም ፡ ሐዋርያው ፡ የጻፈው ፡ እርሱን ፡ ነው ። ይህም ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ በ፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፪ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ይመጣል ፡ እዚያም ፡ ላይ ፡ በአማርኛ ፡ ትርጉማችን ፡ «ባለመበለበስ ፡» ተብሎ ፡ ተተርጉሞአል ። እንግዲያውስ ፡ ፍቺው ፡ «በማይጠፋ ፡ አካኋን ፡» ነው ። እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ የሚወድበት ፡ ፍቅር ፡ የዘላለም ፡ ነውና ፡ እኛ ፡ እንዲሁ ፡ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መውደድ ፡ ይገባናል ። (ሆኖም ፡ በራእይ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ «የቀደመውን ፡ ፍቅርህን ፡ ትተሃል ፡» የተባለበቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የኤፌሶን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆኑን ፡ ስንገነዘብ ፡ ሐዋርያው ፡ የሰነ ዘረው ፡ የማሰጠንቀቂያ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ እንረዳ ለን ።)

ሠ) «ጸጋ ፡» (ቊ. ፳፬ ።) «ይህ ፡ ጸጋ ፡ ምንድር ፡ ነው ?» ቢሉ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ሲያነሣ ፡ መልካሚቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ስትሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ለሁላችን ፡ ፍቅር ፡ እንድንት ፡ ሲሰጠን ፡ ነው ። [46] ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማይጠፋ ፡ አካኋን ፡ ከሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ጸጋ ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

አንጣሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ እስጀምሮ ፡ በጸጋው ፡ ላስጨረሰን ፡

ለእግዚአብሔር ፤

ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ለዘላለም ፤ አሜን ።

---

46. ዘኍል. ፮ ፡ ፳፮ ። ዕዝ. ፯ ፡ ፮ ፡ ፱ ። የሐዋ. ፱ ፡ ፴፫ ።